**መቐለ ዩኒቨርሲቲ**

**የሕብረተሰብ ሳይንስና ቋንቋዎች ኮሌጅ**

**የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሑፍ ትምህርት ክፍል (አማርኛ)**

# የማዳመጥ ክሂል ተግባራትና ክንዉኖች የተማሪዎቹ የማዳመጥ ክሂል ለማዳበር ያላቸዉ ተገቢነት ፍተሻ (በ10ኛ ክፍል መማሪያ መፅሐፍ ተተኳሪነት)

**በ**

**ልእልቲ ንጉስ ወልደሃና**

**ጥቅምት2018 ዓ.ም**

**መቐለ፤ትግራይ፤ኢትዮጵያ**

**መቐለ ዩኒቨርሲቲ**

**የሕብረተሰብ ሳይንስና ቋንቋዎች ኮሌጅ**

**የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሑፍ ትምህርት ክፍል (አማርኛ)**

# የማዳመጥ ክሂል ተግባራትና ክንዉኖች የተማሪዎቹን የማዳመጥ ክሂል ለማዳበር ያላቸዉ ተገቢነት ፍተሻ (በ10ኛ ክፍል መማሪያ መፅሐፍ ተተኳሪነት)

**በ**

**ልእልቲ ንጉስ ወልደሃና**

**ጥቅምት2018 ዓ.ም**

**መቐለ**

**፤ትግራይ፤ኢትዮጵያ**

# የማዳመጥ ክሂል ተግባራትና ክንዉኖች የተማሪዎችን የማዳመጥ ክሂል ለማዳበር ያሳቸዉ ተገቢነት ፍተሻ (በ10ኛ ክፍል መማሪያ መፅሐፍ ተተኳሪነት)


መቐለ ዩኒቨርሲቲ

የሕብረተሰብ ሳይንስና ቋንቋዎች ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሑፍ ትምህርት ክፍል (አማርኛ)

በ

ልእልቲ ንጉስወልደሃና

አማካሪዎች፡-

በለጠ ሕሉፍ(ዶ/ር)

መ/ር ተስፋይ ሞላ


አማርኛን በማስተማር የሁለተኛ (ኤም. ኤ.) ዲግሪ ለማግኝት በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ፅሑፍ

ጥቅምት 2018 ዓ.ም

መቐለ፤ትግራይ፤ኢትዮጵያ

**መቐለዩኒቨርሲቲ**

**የሕብረተሰብሳይንስናቋንቋዎችኮሌጅ**

**የኢትዮጵያቋንቋዎችናስነ-ፅሑፍትምህርትክፍል (አማርኛ)**

የማዳመጥ ክሂል ተግባራትና ክንዉኖች የተማሪዎቹን የማዳመጥ ክሂል ለማዳበር ያላቸዉ ተገቢነት ፍተሻ (በ10ኛ ክፍል መማሪያ መፅሐፍ ተተኳሪነት) ፤ ርእስ በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ <u>በልእልቲ ንጉስ ወልደሃና</u> የቀረበው ይህ ጥናት የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና ወጥነት ስለማሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል፡፡

**የፈተና ቦርድ አባላት**

**አማካሪ ........................................ ፊርማ .........................ቀን ................**

**የውጭ ፈታኝ ................................. ፊርማ .........................ቀን ................**

**የውስጥ ፈታኝ ................................ ፊርማ .........................ቀን ...............**

## ማረጋገጫ

የማዳመጥ ክሂል ተግባራትና ክንዉኖች የተማሪዎቹን የማዳመጥ ክሂል ለማዳበር ያላቸዉ ተገቢነት ፍተሻ (በ10ኛ ክፍል መማሪያ መፅሐፍ ተተኳሪነት)፤በሚል በሚል ርእስ በመቅለ ዩኒቨርሲቲ የሕብረተሰብ ሳይንስና ቋንቋዎች ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሑፍ ትምህርት ክፍል (አማርኛ) የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትም በትክክል የተጠቀሱና ዋቢ የተደረጉ መሆኑን እንዲሁም መቀለ ዩኒቨርሲቲ የጥናቱ ህጋዊ ባለቤት መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

**ስም፡-**ልእልቲ ንጉስ ወልደሃና

**ፊርማ፡-** ___________

**ቀን፡-** ____________

## ምስጋና

በቅድሚያ ጤናውን፣ኃይልና ብርታቱን በመስጠት ይህ ስራ ለዚህ ደረጃ እንዲደርስ ሰዓቱንና ዕለቱንሁሉ ባርኮ ለሰጠኝ ለልዑል እግዚአብሔር አመሰግናለሁ፡፡ በመቀጠል በመማር ማስተማሩ ላስተማሩኝ መምህሬ፤ ለዚህ ጥናት

ከጅማሮእስከ ፍፃሜው ድረስ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ምክራቸውን ስለገሱኝ ለዋና አማካሪዬ ለዶክተር በለጠ ሕሉፍ እጅግ ላቅ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡በማንኛውም ጊዜ ለምጠይቃቸው ጥያቄዎች ሁሉ በፈቃደኝነት እና በቅልጥፍናምላሽ በመስጠት በማማከር ብሎም በትጋትእንድሰራ ስለአበረታቱኝ በጣም አመስግናለሁ፡፡ በመቀጠል ለረዳት አማካሪዬለዶክተር ተስፋይ ሞላ ያለውን ችግር በምን መልኩ ማስተካከል እንዳለብኝ ስለአማከሩኝ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

ሁሌም ቢሆን ስለ እራሱ ምቾት ሳይሆን ስለ እኔ ስኬትና ውሎ መግባት ለሚያስበው ውዱባለቤቴ መ/ር ተስፋይ ሐጎስ ሁሌም ከልብ አመሰግናለሁ፤ ይህ ሁሉያለሱ አይሳካም ነበር፡፡ የማይጨው መሰናድኦ ትምህርት ቤት የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበውን የፅሑፍ መጠይቅ በቅንነትና በሐቀኝነትበመሙላታቸው እጅግ በጣም አመሰግናለሁ፡፡ ከዛም በተጨማሪም ባልደረቦቼ የሆኑት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በቡዱን ውይይት ለሰጡኝ ገንቢ መረጃ ከልብ በመነጨ ስሜት በጣም አመሰግናለሁ፡፡

## የይዘት ሠንጠረዥ


ማረጋገጫ v

ምስጋና v

የይዘት ሠንጠረዥ vii

አጠቃሎ x

ምዕራፍ አንድ መግቢያ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት 2

1.3 የጥናቱ ዓላማ 3

1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ 4

1.5 የጥናቱ ወሰን 4

ምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳናት 5

2.1 ንድፈ ሐሳባዊ ሥራዎች 5

2.1.1 የማዳመጥ ምንነት 5

2.1.2 በማዳመጥ ክህሎት ላይ የተሰሩ ንድፍ ሀሳቦች እና አተገባበሮች፡- 5

2.1.3 በማዳመጥ ክሂል ተግባራት ክንውኖች የተሰሩ ስራዎች ፡- 7

2.2 ቋንቋ መማሪያና መሳርያዎች 8

2.2.1 የአስረኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ 9

2.3. የማዳመጥ ክሂል ትምህርት ምንድን ነው? 10

2.4 የማዳመጥ ተግባር ንድፍ መርሆዎች 11

2.5 ማዳመጥን የማስተማር አዳዲስ መንገዶች 14

2.6 የማዳመጥ ክሂል የማስተማሪያ የትምህርት ተግባራት 15

2.6.1የማዳመጥ ክሂል ማስተማሪያ የትምህርት ተግባራት አመራረጥ 15

2.7 የማዳመጥ ክሂል ማስተማሪያ የትምህርት ይዘት 17

2.7.1 የማዳመጥ ክሂል የትምህርት ይዘት አመራረጥ 18

2.8 የማዳመጥ ተግባራት ቅንብር 21

2.9 የማዳመጥ ክሂል የማስተማርያ መሣሪያዎች 22

2.9.1 በመቅረጸ ድምፅ የተዘጋጁ 22

2.9.2 ቀጥተኛ ቃላዊ ገለፃዎች 22

2.9.3 የስነ-ፅሑፋዊ ሥራዎች 23

2.9.4 በስእል ካርታ ስንጠረዝ መጠቀም ........................................................................ 23
2.10 ቀደምት ጥናቶች ቅኝት ........................................................................ 24
ምዕራፍ ሦስት የጥናቱ ንድፍና የአጠናን ዘዴ 26
3.1 የጥናቱንድፍ........................................................................ 26
3.2 የናሙና አመራረጥ ዘዴ ........................................................................ 26
3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ........................................................................ 26
3.3.1 የሰነድ ፍተሻ........................................................................ 26
3.3.2 የፅሑፍ መጠይቅ ........................................................................ 27
3.3.3 የቡድን ውይይት መንገድ........................................................................ 27
3.4 የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች........................................................................ 28
ምዕራፍ አራት የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ 28
4.1 የመረጃ ትንተና........................................................................ 29
4.1.1 የሰነድ ፍተሻ........................................................................ 29
4.1.2 በቡድን ውይይት መንገድ የተገኘ ውጤት ........................................................................ 35
4.1.2.1 የማዳመጥ ትምህርት ክፍሎቹ ጠንካራ ጎኖች ........................................................................ 35
4.1.2.2 የማዳመጥ ትምህርት ክፍሎቹ ደካማ ጎኖች ........................................................................ 36
4.1.3. የመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ ........................................ 36
4.1.3.1 በቅድመ ማዳመጥ ያሉ ተግባራትና ክንዉኖች የተማሪዎችን ክሂል ለማዳበር ያላቸዉ ተገቢነት ........... 37
ሰንጠረዥአንድ ፥ በቅድመ ማዳመጥ ያሉ ተግባራትና ክንዉኖች የተማሪዎችንክሂልለማዳበርያላቸዉተገቢነት
37
4.1.3.2 በማዳመጥ ጊዜ ያሉ ተግባራትና ክንዉኖች የተማሪዎችን ክሂል ለማዳበር ያላቸዉ ተገቢነት ................ 39
ሰንጠረዥ ሁለት በማዳመጥ ጊዜ ያሉ ተግባራትና ክንዉኖች የተማሪዎችን ክሂል ለማዳበር ያላቸዉ ተገቢነት............... 39
4.1.3.3 በድህረ ማዳመጥ ደረጃ ያሉ ተግባራትና ክንዉኖች የተማሪዎችን ክሂል ለማዳበር ያላቸዉ ተገቢነት .... 41
ሰንጠረዥሦስት ፥ በድህረ ማዳመጥ ያሉ ተግባራትና ክንዉኖች የተማሪዎችን ክሂል ለማዳበር ያላቸዉ ተገቢነት........... 41
4.1.3.4 ከመምህራኑ ፅሑፋዊ መጠይቅ የተገኘው አጠቃሳይ ቁጥራዊ ውጤት ........................................ 42
ሰንጠረዥአራት፡- ከመምህራን መጠይቅ የተገኘው አጠቃሳይ ቁጥራዊ (ስታስቲካላዊ) ውጤት................................ 42
ምዕራፍ አምስትማጠቃለያ፣መደምደሚያ፣ አስተያየት 43
5.1 ማጠቃለያ ........................................................................ 43
5.2 መደምደሚያ........................................................................ 46
5.3 አስተያየት........................................................................ 46
ዋቢጽሁሮች 48
አባሪዎች 51

**አጠቃሉ**

*የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በ10ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማርያ መፅሐፍና መርሃ ትምህርት ውስጥ የተካተቱ የማዳመጥ ክሂል ተግባራትና ክንውኖች የተማሪዎችን የማዳመጥ ክሂል ለማዳበር ያላቸው ተገቢነት መፈተሽ ነበር፡፡ ይህ ጥናት ገላጭዳሰሳ (descriptive survey) የምርምር ንድፍን የተከተለ ሲሆን መጠናዊ (quantitative) እና ዓይነታዊ (qualitative) የምርምር ዘዴዎችን በመጠቀም በ2015 ዓ.ም በታተመው የ10ኛክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍና የማዳመጥ ትምህርት ይዘቶች ለይቶ በማውጣት የቀረቡት ተግባራትና ክንውኖችው የተማሪዎችክሂል ከማዳበር አኳያ ያላቸውን ብቃትመፈተሽ ነበር። በመጀመሪያ አጥኚዋ በመማሪያ መፅሐፉ ላይ ከተለያዩ ሙሁራን የመገምገሚያ ማዕቀፎች (Frameworks) አውጥታ በመፅሐፉ የሰነድ ፍተሻ (document analysis) አካሂዳለች፡፡ በመቀጠል ደግሞ የማዳመጥ ክሂል ተግባራትና ክንውኖች ጋር በተያያዘ ከአማርኛ መምህራን በተደረገ የቡድን ውይይት መንገድ (Focus Group Discussion) የተገኙ መረጃዎች ተተንትነው ቀርቧል፡፡ ከዚያም የማዳመጥ ክሂል ተግባራት ክንውኖች የተማሪዎቹን ክሂል ለማዳበር ያላቸውን ተገቢነት በተመለከተ በማይጨው ከተማ ካሉት ሦስት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል እንደናሙና በተወሰዱት ስድስት የ10ኛ ክፍል አማርኛ መምህራን የፅሑፍ መጠይቅ በማሰራጨት የተገኘው መረጃ ተተንትኖ ቀርቧል። በመጨረሻ የ10ኛ ክፍል አማርኛ መምህን ከተለያዩ ትምህርት ቤቶች የተውጣጡ 5 መምህራን በቡድን ውይይት መንገድ መፅሐፉ የተካተቱት የማዳመጥ ክሂል ተግባራት ክንውኖች ጠንካራና ደካማ ጎኖችን የገመገሙ ሲሆን፣ የተገመገሙት ነጥቦች ደግሞ ተተንትናው ቀርቧል። በዚህ መሰረትም አጥኚዋ ባደረገችው የሰነድ ፍተሻና በፅሑፍ መጠይቅ በመማሪያ መፅሓፉ ያሉት የማዳመጥ ክሂል ተግባራትና ክንውኖች የተማሪዎቹን የማዳመጥ ክሂል በማዳበር ያለቸው ተገቢነት መልካም እንደሆነ ነው ።ይኸውም መልከም እንደሆነ ነው። ምክንያቱም በአብዛኞቹ ምዕራፎች የቀረቡት የማዳመጥ ክሂል ተግባራት ክንውኖች የተማሪዎቹን ፍላጎት ፣ የክፍል ደረጃ ፣ ዕድሜ ባህላዊ ዳራና መስህብነት በተመለከተ ከነበረው መፅሓፍ ብተሻለ መንገድ የቀረበ መሆኑን ጥናቱ ያመለክታል። ከዚያም በተጨማሪ ከመምህራን ፅሑፋዊ መጠይቅ የተገኘው መረጃም እንደሚያመልክተው በ10ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሓፍ ውስጥ ያሉት የማዳመጥ ክሂል ተግባራት ክንውኖች መምህራን አልፎ አልፎ እስማማሉህ የሚል ነው። ከዚህ የተነሳ እንደ አጥኚዋ ድምዳሜ በ10ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መፅሐፍ የተካተቱት የማዳመጥ ክሂል ተግባራት ክንውኖች መማሪያ በአብዛኞቹ ተማሪዎቹን ክሂል ለማዳበር ተገቢነት ያላቸው እንኳ ቢሆኑ መሻሻል ያለባቸው ነገሮች ዳግሞ በሁሉም ምዕራፎች በንግግርና ንባብ መልክ የቀረቡ በመሆናቸው ከዚህ ወጣ ባለ መልኩ ብቀርቡ ይሻል እንደነበር ነው።*

*ይኸውም ከሚደመጡ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ተያያዥነት ያላቸው ስዕላዊ መገለጫዎችና በካሴት ወይም በሬድዮ የተቀረፁ ድምፆችን ወደ ክፍል ይዞ በመግባት የተማሪዎችን የማዳመጥ ክሂል ለበለጠ ለማዳባር ተገቢነት ይኖረው ነበር። በመጨረሻም በሦስቱም የምርምር መተንተኛ ዘዴዎች አማኝነት የተገኘው መረጃና የውጤት ማብራሪያ መሠረት ተገቢ መደምደሚያና አስተያየት ተሰጥቷል።*

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ማዳመጥ መሰረታዊ ከሆኑት አራት የቋንቋ ክሂሎች መካከል አንዱሲሆን ይህ ክሂልም የመቀበያ ክሂል በመባል ይታወቃል።የመቀበያ ክሂል የተባለበት ምክንያት ደግም አዳማጮች በሌላ ሰው የተነገረውን ወይም የተነበበውን ቃላዊመረጃ የሚቀበሉበት ሂደት ሲሆን የተማሪዎች አእምሯዊ ግንዛቤ እንዲጎለብት የሚያደርግና በዓለም ዙርያ ስላሉ ሁነቶችና ክስተች ምንነትና ማንነት መረጃ የሚቀበሉበት መንገድ በመሆኑ ነው። ስለዚህ ማዳመጥ ቃላትን ከመስማት የበለጠ ትኩረትን የሚሻ ከመሆኑም በተጨማሪ በአዕምሮ ፍቺና ትርጓሜ እየሰጡ መሄድንም የሚመለከት ነው። ማዳመጥ አንድ የተሳከ መልክት የመቀበል ሂደት ሲሆን የተሳከው ሐሳብ በስርዓታዊ ቅደም ተከተል በተፈጠረ መዋቅር መሰረት ስሜት ገላጭ የሆነ መልዕክትን መፍጠር መቻል ደግሞ የአዳምጦ መረዳት ሚና ነው። ስለዚህ አንድን የቀረበ ንግግር ወይም ጽሑፍ ስናዳምጥ ቃላትን ከመስማት ባለፈ ሲተሳሰፍ የተፈለገውን ቀጥተኛም ሆኖ አገባባዊ መልዕክት መረዳትና የተረዱትንም ስንባብና ስፅሁፋዊ ክሂላቸው መዳበር እንደ ዋነኛ መሳሪያ የሚጠቀሙበት ነው(Cardinal፤2013)።

ከላይ የተገለፁት ነጥቦች የሚያመለክቱት ማዳመጥ አንድን መረጃ ከሌላ ሰው ሐሳብ የምንቀበልበት ሲሆን ዋነኛ ግቡ መገንዘብ እንደሆነ ነው። ማዳመጥ ከመስማት የላቀ ትኩረት መስጠት የሚሻ ተግባር እንደሆነ አዳምጦ መረዳት ማለት በጽንስ ሐሳብ ደረጃ ሲታይ ንቁ ሂደትን የሚከተል ሲሆን በተመረጡ ቃላዊ ግብዓቶች ላይ በማተኮር ከቀረበው ንግግር ወይም ጽሁፍ ትርጉም መፈለግና ምን ዓይነት እውቀት ማግኘት እንደፈለጉ ውሳኔ ላይ የሚደርሱበት ነው(Gilakjani &Ahmadi፤2011)።ይህን ሐሳብ መነሻ በማድረግ አዳምጦ መረዳትን ተማሪዎች ሲጠቀሙ ዓላማቸው ወይም ደግሞ ከቀረበው ሐሳብ መረዳት የፈለጉትን ነገር ቀድመው መገንዘብ አለባቸው።ምክንያቱም ለተማሪዎች አዳምጦ የመረዳት ችሎታ ማደግ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል።ስዚህ ነው ማዳመጥ መረዳትን ስመልመድ ጠቃሚ የሚሆነው (Hamouda፤2013)፡፡

ማዳመጥ ለሰው ልጅ የህይወት እንቅስቃሴ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው።Islam(2012) እና Miller (2003)ዋቢ አድርገው እንደጠቀሱት የሰው ልጅ በቀን ከሚያደርገው የተግባቦት ሂደት ውስጥ 50% በላይ የሚሆ ነው በማዳመጥ ሲሆን 25% ደግሞ በመናገር ሌላው 16% በማንበብ ሲሆን ቀሪው 9% በመፃፍ ነው ይላሉ። ይህ ቁጥር የሚያሳየው ማዳመጥ ለሰው ልጅ የዕለት ከዕለት በሚያደርገው የተግባቦት ሂደት ላይ ከፍተኛ ሚና እንዳለው ነው። ከዚህም በተጨማሪ ማዳመጥ ለንግግር ግብዓት በመሆኑ የሰው ልጅ በሰፌው የሚጠቀመው ክሂል ለመሆን ማሳያ ነው።

Lestari (2017) እንደገለጹት ማዳመጥ ለተማሪዎች የተግባቦት ሚናን እንዲፈጥሩ የሚያግዝ ክሂል ሲሆን በቀለማዊ የትምህርት ተግባራት ብቻ ሳይሆን ለቀጣይም የህይዎት እንቅስቃሴ ኣስፈላጊ ነው።Renukadevi (2014) በበኩላቸው ማዳመጥ ዘርፈ ብዙ ሚናን የሚጫዎት ክሂል ነው። ከዚህም ውስጥ ስአብነት ብናነሳ ለቋንቋ ተማሪዎች እንዴት እንደሚናገሩ፣የቃላት ጥብቀትን፣የቃላትፍችንናአገባብ፣መልዕክትንመረዳት፣ድምፅንከቅላፄጋር በማዛመድ ማጥበቅና ማላላት እና የድምፅ አወጣጥን ተማሪዎች እንዲማሩ የሚያደግ ነው።ከዚህም በተጨማሪ ማዳመጥ ለተማሪዎች በቀስም ትምህርት ሂደታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ መንገድ የሚከፍት ክሂል ነው። በቀስም ትምህርታቸው ውጤታማ መሆን ከቻሉ

ደግሞ መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች ለአደምጦ መረዳት ትኩረት እንዲሰጡ ያደርጋቸዋል(Darweesh፣2014)። Ahmadi (2011) እንደገለፁት አዳምጦ መረዳት የግንዛቤ ሂደትንና ስነ ልሳናዊ ህግጋትን በሚከተል የሰነ ልሳን ክፍሉችን ማለትም ድምፅን፣ቃላትንና የሰዋስው መዋቅርን፣ እንዲሁም የማዳመጥ መመሪያዎችንና ደረጃዎች መተግበር ነው ። ከላይ የተገለፁት ቁምነገሮች ስለማዳመጥ ክሂል ለሰው ልጅ ያለው ፋይዳ በተመለከተ ሲሆን፣ በተጨማሪ በማዳመጥ ክሂል ዙሪያ ከዚህ በፊት በጥናት ደረጃ የተጠኑ ክፍተቶች ለምሳሌ ፡- በታዲዮስ በቦሮ በ 2015 ዓ.ም የታተመው የ10ኛ ክፍል አማርኛ ማስተማሪያ የትምህርት ይዘቶች አመራረጥና አቀራረብ መገምገም የሚል የጥናቱ ርዕስ ነው ። በጥናቱ ከታዩት ክፍተቶች መካከል በ10ኛ ክፍል መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የማስተማሪያ ይዘቱ የትምህርት ዓላማ ከግብ በሚያደርሱ መልኩ ሙሉ በሙሉ ተመርጧል ለማለት እንደማይቻል ተገልፃል። ምክንያቱም ለአብነት ያህል በገጽ 21 ላይ የቀረበውን የማዳመጥ የማስተማሪያ የትምህርት ይዘት ዓላማ በተለያዩ መገናኛ ብዙኋን ስቶች እና እድገት ዙርያ የቀረቡ ሀሳቦችን እንዳመጠው የተናጋሪዎችን ሀሳብ ይገመግማሉ ። ይህንን አላማ ለመፈፀም የተመረጠው አውድ ተመጣጣኝ መሜ ያለየው ውጋዮህ ንጋቱ የሚል መሆኑን ነው ።

– አላማውና ለማዳመጥ የቀረበው የፅሑፍ ቅንጫቢ የማይጣጣሙ ሆኖው መቅረባቸውን ጥናቱ ተጠቁሟል ። በሁለተኛ ደረጃ በጥናቱ የታየው ክፍተት ከ10ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ የማዳመጥ ክሂል ማስተማሪያ የትምህርት ይዘቶች የተማሪዎችን ፍላጎት ያገናዘበ እንደሆነ ቀጥሎ መመልከት ይሆናል። በመማሪያ መፅሓፉ ውስጥ ሊደመጡ የሚችሉ ግብአቶች በ9 ምዕራፎች ተከፋፍለው የሚገኙ ሲሆን፣ በእያንዳንዱ ምዕራፍ አንድ አንድ ማዳመጥ ክሂል ማስተማሪያ የትምህርት ይዘት የቀረቡ መሆናቸው ተገልፃል። የተመረጡት አገልግሎት ላይ የዋሉት አውዶች የተማሪዎችን ፍላጎት ያማከሉ ናቸው ወይ የሚለውን ለመመለስ በምዕራፍ የቀረቡት የጽሑፍ ቅንጫቢዎች ስንመለከት የተማሪዎችን ፍላጎት አሟልቷል ። ከተጠቀሱት ጥናቶች ለመታዘብ እደተቻለው የማዳመጥ ክሂል ትምህርት ትኩረት ያልተሰጠው መሆኑን ይመከታል ለዚህ ጥናት መነሻ የሆኑትም እነዚህ ከተለያዩ ዘርፎች ስለማዳመጥ ክሂል ትምህርት ያለው ድክመት የተጠቀሱ አስታየቶች ሲሆኑ ይህ ጥናትም በጥናቶቹ እንደታየው ከዚህ ቀደም ይሰጥ የነበረው የማዳመጥ ክሂል ትምህርት የትኩረት ማነስ አጥኚዋም በምታስተምርበት ትምህርት ቤት ውስጥ በ10ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ የተካተቱት የማዳመጥ ክሂል ተግባራትና ክንውኖች የተማሪዎችን ክሂል ከማጎልበት ኣኳያ ያላቸውን ተገቢነት ምን ይመስላል ። የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችል ጥናት ነው።

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የማዳመጥ ክሂል ቋንቋን ለመማር በጣም ጠቃሚ ከሆኑት ክሂሎች ውስጥ አንዱ እንደሆነ ቀደም ሲል በጥናቱ ዳራላይተጠቁሟል፡፡ሆኖም ግን በርካታ ተማራማሪዎች ይህ ክሂል ―የተረሳ ነገር ግን ቁልፍ የሆነ የቋንቋ ክሂል“ በማለት ይገልፁታል፡፡ እንደGilakjani & Sabouri (2016) አገላለፅ ተማሪዎች በሚያዳምጡበት ጊዜ በርካታመሰረታዊ የሆኑ አዳምጦ የመረዳት ችግር ይታይባቸዋል፡፡ምክንያቱም ደግሞ በዩኒቨርሲቲና ከዚያም በታችባሉት የክፍል ደረጃዎች ትኩረት የሚሰጠው በመፃፍ፣በማንበብና በቃላት ፍቺ ላይ ያተኮረ ትምህርትመሆኑ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ማዳመጥ በብዙ የመማሪያ መፃሕፍትም ሆነ በበርካታ መምህራን ዘንድ ትኩረት ያልተሰጠውክሂል ስለሆነ ነው ይላሉ፡፡ ካዛም በተጨማሪ እንደBrown (2000) አገላለፅ ማዳመጥ ለተግባቦት (communication) ቁልፍ መሳሪያ የሆነ እና ከ19ኛው ክፍለዘመን አጋማሽ ወዲህ በስርዓተ ትምህርት በመካተት ለትምህርት እየቀረበ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ ከዚህምተማሪዎች ሐሳባቸውን በንግግር ከማቅረባቸው በፊት በርካታ መጠን ያላቸው የማዳመጥ መረጃዎችን ትኩረትመስጠት እንዳለባቸው የሚጠበቅ እንደሆነ

በመግለፅ ነገር ግን ተማሪዎችም አዳምጠው መረዳት ከቻሉቀሳቄን፣ማጥበቅን፣ድግግሞሽን እና የቃላት ምድብን ለይቶ ለመጠቀም የበለጠ ግንዛቤ እንዲኖራቸውያደርጋል፡፡

ስለሆነም በዚህ ርእሰ ጉዳይ ዙርያ ብዙ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ ከነዚህ መካከል ዋናው ምሳሌና በቀጥታ ከዚህ ጥናት ተያያዥነት ያለው በጎዱ ምንውዬ በ2014 ዓ.ም *—በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪዎች የማዳመጥ ብልሀት አጠቃቀም ከአዳምጦ የመረዳት ችሎታቸው ጋር ያለው ተዛምዶ፣ በሰዴ ሙጃ ወረዳ በሙጃ ሮቢትአጠቃሳይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ10ኛ ክፍል ተተኳሪነት*ብሚል ርእስየተሰራና በጅማ ዩኒቨርሰቲ በአማርኛ ማስተማር ሁለተኛ ዲግሪ ለማግኘት እንደ ማሟያነት የቀረበ ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ የኔ ጥናት ከተጠቀሰው ጥናት የሚለየው ነገር ዋናውትኩረቱ በማዳመጥ ክሂል ተግባራትና ክንዉኖች ለተማሪዎች የማዳመጥ ክሂል ለማዳበር ያሳቸዉ ተገቢነት ፍተሻ (በ10ኛ ክፍል መማሪያ መፅሐፍ ተተኳሪነት) ነው፡፡

ስለዚህ ከሳይ የተጠቀሱት ክፍተቶች ግምት ውስጥ በማስገባት አጥኚዋ በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ እንድታጠና ያነሳሰዋትሌሎች ተጨማሪ ምክንያቶችም ነበርዋት፡፡አንደኛ በማይጨው መሰናዶ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ10ኛክፍል ተማሪዎች በምታስተምርበት ጊዜ በማዳመጥ ክሂል ዙርያ የቀረቡትተግባራትና ክንውኖች በተመለከተየራስዋ የሆነ የግል ትዝብት ስለወሰደች ነበር፡፡ በሌሳ አገሳለፅ በክፍል ውስጥ ሲተገበሩና ሲከወኑ የማዳመጥ ክሂል ተግባራትና ክንውኖች የተማሪዎች ዓቅም ከመገንባት ኣኳያ ያለው የተገቢነት ክፍተት ስሳየች ነበር፡፡ ሁለተኛየጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ደግሞ10ኛክፍል ለመሰናድኦ ትምህርት ደረጃ መሸጋገርያ ስለሆነ ተማሪዎች በዚህ ደረጃ በቂ የሆነ የአዳምጦ መረዳት ክሂል ማዳበር ስሳለባቸው ከወዲሁ ያለውን ክፍተቶች በማጥናት የችግሩ መንስኤዎችና የመፍትሄ ሐሳቦች መስጠት አስፈሳጊ ነው ብሳ አጥኚዋ ስሳመነችበት ነበር፡፡ በሌሳ አገሳለፅ ለዚህ ጥናት መነሻ የሆነው የቀረቡት የማዳመጥ ክሂል ተግባራት ክንውኖች በክፍል ውስጥ ሲተገበሩና ሲከናወኑ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ክሂሉን ከመገንባት ኣኳያያሳቸውንተገቢነትምንእንደሚመስል ለመፈተሽ ነው።

ከዘም በተጨማሪ አጥኚዋ በምታስተምርበት ትምህርት ቤት ውስጥ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ የማዳመጥ ክሂል ተግባራት ክንውኖች በክፍል ውስጥ የአተገባበርና የአከናዋወን ችግር ስለሚያጋጥም ያዳመጡትን ፅሑፍ ተመልሰው በትክክል መግለፅ ስለሚቸገሩ ትዝብት በመውሰድዋ ነበር።

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በ10ኛ ክፍል ኣማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሓፍ ውስጥ የተካተቱ የማዳመጥ ክሂል ተግባራት ክንውኖች ለተማሪው ክሂል ለማዳበር ያሳቸውን ተገቢነት መፈተሽ ሲሆን ፣ ከዚህ በታች ንዑሳን ኣሳማዎች ተገልፃል ።

1.በመማሪያ መፅሓፉ ሲደመጡ የቀረቡት ተግባራትና ክንውኖች ተማሪዎቹ አዳምጠው ለመለማመድ የሚያስችሉ መሆናቸውን መግለፅ ።

2.በመማሪያ መፅሓፉ የቀረቡት የማዳመጥ ክሂል ተግባራት የተማሪዎችን የማዳመጥ ክሂል ለማጎልበት ተገቢ በሆነ መልኩ ተዘርዝርዋል ወይ ?

3. በ10ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መፅሐፍ የቀረቡት በማዳመጥ ክሂል ተግባራትና ክንውኖች ተማሪዎችን ያዳመጡትን ቁምነገር ተመልሰው በቃል ወይም በፅሑፍ መግለፅ።

4. በመፅሐፉ የቀረቡት የማዳመጥ ክሂል ይዘቶች የቅድመ ማዳመጥ ፣ የማዳመጥ ግዜና የድህረ ማዳመጥ ተግባራት ክንውኖች በተገቢው መንገድ መቅረባቸውን እና አለመቅረባቸው መግለፅ ።

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት ለቋንቋ መማር ማስተማር እድገት ማለትም በማድመጥ ክሂል ተማሪዎች ከዚህ በፊት የነበራቸውን ክፍተት ለማስታካከል የጎላ ድርሻ ሲኖረው ይችላል ። ስለሆነም ለሚከተሉት ባለድርሻ ኣካላት ጠቀሜታ ይኖሩታል ።

1. የኣማርኛ ቋንቋ ተማሪዎች ከዚህ በፊት በማዳመጥ ክሂል ተግባራት ክንውኖች ሲተገበሩ ወይም ሲከወኑ የነበሩባቸውን ችግሮች ምን እንደነበር እንዲረዱ ፣ ለሚሰጣቸው የማዳመጥ ተግባራት ክንውኖች በክፍል ውስጥ እንዴት በተገቢው መንገድ መተግበር እንደሚቻል ከዚያም የትኛው ኣገባብ ተጠቃሚው ክሂሉን ማዳበር እንደሚችሉ እገዛ ያደርጋል ።

2. ለኣማርኛ መምህራን ደግሞ ከፍተኛ ኣስተዋፅኦ ሲያደርግ ይችላል ። መምህራን የተማሪዎችን የማዳመጥ ክሂል ተግባራት ክንውኖች በምን ዓይነት ኣገባብ ብያስተምሩ ተማሪዎች ክሂሉን ሲያዳብሩት የሚችሉበትን መንገድ ከጥናቱ እንዲገነዘቡና ከዚያም የመማር ማስተማር ሂደቱ በተሻለ ሁኔታ እንዲያስተምሩ ሲያግዛቸው ይችላል ።

3. ለስርዓት ትምህርት ኣዘጋጆች የማዳመጥ ክሂል ተግባራት ክንውን ቀጣይ በሚያዘጋጁበት ወቅት ትኩረት ሰጥተው እንዲያዘጋጁ ጥናቱ መረጃ ይሰጣል ።

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ በ2015 ዓ.ም የታተመው የ10ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መፅሐፍ የተካተቱት የማዳመጥ ክሂል ተግባራት ክንውኖችን የተማሪዎችን የማዳመጥ ክሂል ከማጎልበት ያላቸውን ተገቢነት መፈተሽ ያተኮረ ሲሆን ፣ ኣጥኚዋ ደግሞ 9ኛና 10ኛ ክፍል የምታስተምር ኣሁንም ቢሆን በዚያው ትምህርት ቤት እያስተማረች ያለች መምህርት ናት ። አጥኚዋ ለተከታታይ 11 ዓመታት በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ያጋጠማት ችግር ቢኖር በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች ተመሳሳይ የሆነ ክፍተት ቢያጋጥማት እንኳ ለጥናቱ አመቺነትና አስተማማኝነት እንዲኖረው በማሰብዋ ከ9ኛ ክፍል ይልቅ 10ኛ ክፍል ተመራጭ አድርጋዋለች ። ከዚያም በተጨማሪ 11ኛ እና 12ኛ ክፍል አማርኛ ስለ ማይማሩት መምረጥ ኣልተቻለም። የኣስረኛ ክፍል ተማሪዎች ግን ከኣንደኛ መንፈቅ አመት ጀምረው እስከ ሁለተኛ መንፈቅ አመት ትምህርቱ ሳይቆራረጥ ይሰጣቸው ስለነበር የበለጠ ተመራጭ ሁኗል ። ከዚያም ባሻገር አጥኚዋ ለጥናቱ የሚሆኑ መረጃዎች በቀላሉ ለማግኘትም ቢሆን መልካም ነው። ሌላው የክፍል ደረጃው እንዲመረጥ ምክንያት የሆነው የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ከ9ኛ ክፍል ጀምረው መርጠው የሚማሩት በመሆኑ የችግሩ መንስኤና መፍትሄ ለማግኘት ቀላል ሲያደርው ስለሚችል ነው።

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ርዕስ ስር የጥናቱ ደጋፊ የሆኑ ንድፈ ሐሳብዊ ማህቀፎች የምሁራን ሐሳብ ማጠናከሪያ በማድረግ የቀረቡ ሲሆን ፣ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ከጥናቱ ጋር ዝምድና ያላቸው ቀደምት ጥናቶች ከሀገር ውስጥና ከሃገርማዶ ተጠቅሰው ታድሰውበታል ። ከዚያም በተጨማሪ የጥናቱ ፅንስ ሀሳባዊ ማዕቀፍ ተብራርቶ ቀርቧል ።

### 2.1 ንድፈ ሐሳባዊ ሥራዎች

በዚህ ርዕስ ሥር በዋናነት ተጠቃለው የቀረቡት ንድፈ ሐሳባዊ ሥራዎች ፣የማዳመጥ ምንነት ፣በማዳመጥ (Listening) ክህሎት ላይ የተሰሩ ንድፍ ሀሳቦች እና (Theoretical From Work) አተገባበሮች ፣ በማዳመጥ ክሂል ተግባራት ክንውን የተሰሩ ሥራዎች ፣ የማዳመጥ ትምህርት ዓላማ ፣ የማዳመጥ ክሂል በብልሃት ማስተማር ለምን ያስፈልጋል ? የኣዳምጦ መረዳት ክንውን ደረጃዎች ፣ የማዳመጥ ተግባር ንድፍ መርሆዎች … የሚሉት ናቸው።

#### 2.1.1 የማዳመጥ ምንነት

የማዳመጥ ክሂል ከኣራቱ ክሂሎች ኣንዱ ሲሆን፣ማዳመጥ ለሌሎች ክሂሎች ማደበር ወይም ማበልፀግ ዋና መሰረት ነው ። ይህ ማለት ደግሞ ለመናገር የሚደመጥ ነገር ቀድሞ መኖር ኣለበት።የማዳመጥ ክሂል ለተማረና ላልተማረ ማህበረሰብ እኩል ሲያገለግል የሚችል ሲሆን ፣ክሂሉ ለማደበር ግን የኣድማጩን ትኩረት ወሳኝ ነው።ከተለያዩ ኣቅጣጫዎች የሚመጡትን ድምፃች ወይም ፅሑፎች የሚቀርቡትን ተግባራት ትኩረት ሰጥቶ ቁምነገሮችን የማዳመጥ የግለሰቡን ጉዳይ ይሆናል ። ምክንያቱም ማዳመጥ ማለት በተለያየ መንገድ የሚሰማ ነገር ሲኖር፣ያ የሚሰማውን ከድምፅ እስከ ፅሑፍ የሚደመጡ ነገሮች ኣድማጩ ትኩረት ሰጥቶ የሚተላለፈውን መልእክት በኣእምረው ሲይዝ ወይም ሲጨብጠው ማለት ነው። ከዚያም የያዘውን ፍሬ ሐሳብ ለሌላ ኣካል መግለፅ ወይም መልእክቱን በትክክል ማስተላለፍ ከቻለ ነው።

#### 2.1.2 በማዳመጥ ክህሎት ላይ የተሰሩ ንድፍ ሀሳቦች እና አተገባበሮች፦

በማዳመጥ (Listening) ክህሎት ላይ የተሰሩ ንድፍ ሀሳቦች እና (Theoretical From Work) አተገባበሮች ብዙ ናቸው። እነዚህ ከተለያዩ የትምህርት ፋናዎች ስነ-ባህል፣ሰነ-ልቦናዊ ፣ሳይኮሎጂካልና የማሰብ ሂደት (Cognitive) መሠረት ላይ የተመሰረቱ ናቸው። ከነዚህ በጣም ታሳቂ ተግባራዊ እና ንድፍ ሀሳባዊ ኣቀራረቦች የሚከተሉትን ማቅራብ ነው።

1 የኮግኒቲቭ ሂደት ሞዴል (Cognitive Processing Models of Listening)

እነዚህ ሞደሎች ማዳመጥን እንደ አእምሮ ሂደት ያዩታል ። ያደመጠውን ይቀበላል፣ይሞላል፣ይቆጣጠራል እና ትርጓሜ ያደርጋል። የዚህ ሞዴል ተግባራት ትክክለኛ ማስተዋል አየር መገናኛ (bettom- up processing) ኣስቀድሞ እውቀት (top-down processing)

2 ንባብና አዳምጦ የተያያዙ ሞደሎች (Interactive models) እነዚህ ሞደሎች የአዳማጭን ሂደት ከሳምንት መረጃዎች ጋር በመቀሳቀል ያቀርባሉ።

Bottom-up processing: ከጽምፅ ወደ ቃል ፣ ከቃል ወደ ሓረግ ይሄዳል።

Top-Down Processing: ከአስቀድመና ስሜት እና እውቀት ይመራል።

ደጋፊዎቹ ካርል ሮጆርስ ( በምክር እና በሰዎች ግንኙነት)

3 ማዳመጥ እንደ ማህበራዊ ግንባታ (የግንባታ እይታ) ከገንቢ እይታ ማዳመጥ ድምፃችን መቀበል ብቻ ሳይሆን ከተናጋሪው እና ከዐውድ ጽሑፉ ጋር በመግባት ትርጉም መገንባት ነው። ከሳይ የተገለፁት ሓሳቦች እንደቁልፍ ባህሪያት የሚሆኑት፡- ትርጉሙ የተገነባው በአድማጩ ንቁ ተሳትፎ ነው።

4 የማዳመጥ ግንዘቤ ሞደሎች በቋንቋ ትምህርት፡-

-በሁለተኛ ቋንቋ ማግኛ (SLA)፣ ማዳመጥ የቋንቋ መማርን የሚደግፍ ቁልፍ ችሎታ መሆኑን ነው። እዚህ ያሉት ሞዴሎች ተማሪዎች በማዳመጥ ጊዜ እንዴት አዲስ ቋንቋን እንደሚያስኬዱ ያተኩራሉ።

ቁልፍንድፍ ሓሳቦች፡-

Pkrashen's input መሳምት፡- ማዳመጥ ለቋንቋ እውቀት ኣስፈላጊ የሆነ ግንዘቤን ይሰጣል። የአንደርሰን የእውቀት (ኮግኒቲቭ) እድገት ሞዴል፣ የማዳመጥ ግንዘቤን ሶስት ደረጃዎችን ያካትታል ፣ እነሱም ፡- ማስተዋል ፣ መተንተን እና አጠቃቀም ናቸው ።

የቨንደርግሪፍትሜታ ኮግኒቲቭ ማዳመጥ ሞዴል የማዳመጥ ሂደት ማቀድ ፣ መከታተል እና መገምገም ሳይ ኣፅንኦት ይሰጣል።

5.የግብኣትና መስተጋብር ሞደሎች፡-

–ሞዴሎች በመገናኛ አውዶች ውስጥ ማዳመጥን የሚገልፁ መሆናቸው ነው ።

–ግብአት ማዳመጥ ፡- መረጃን በሚገባ መንገድ መገንባት ወይም መሳዋወጥ ሳይ የሚያተኩር ሲሆን፣ በይነተናኝ ማዳመጥ ደግሞ ማህበራዊ መግባባትን መገንበት እና መተሳሰብን ማሳየት ሳይ ልዩ ትኩረት ያደረገ መሆኑን።

6.የስነ–ልቦናዊ የማዳመጥ ሞደሎች

–አድማጮች ድምፃችን በቃሳት– ቃሳትን ወደ ሰዋስዋዊ መዋቅሮች – መዋቅሮችን ወደ ትርጉም ይቀየራል።

7፥ስማዳመጥ ሁስንተናዊ አቀራረብ፣ በዚህ ዘመናዊ አቀራረቦች ብዙ ንድፈ ሓሳቦችን በአንድ ሳይ ዘመናዊ አቀራረቦች ብዙ ንድፈ ሓሳቦችን በአንድ ሳይ መጠቀምን የሚጠቀሙ መሆናቸውን ነው።

ከዚህ በላይ የቀረቡት የማዳመጥ ችሎታ ንድፍ ሐሳቦችና ሞዴሎች ሲሆኑ፣ ከአንደኛ እስከ ሰባተኛ ተራ ቁጥር ከተዘረዘሩት ነጥቦች፡- ከታች ወደ ላይ የሚል ነው። ይኸውም ከድምፅ→ ሐረጋት →ቃላት→ ዓቱነገር እያለ የማያድግ ሲሆን፣ ተማሪዎች ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚያግዝ አካሄድ ነው። ቀጥሎ ደግሞ ከላይ ወደታች ወይም ከከባድ ወደ ቀላል የሚሄድ ሲሆን ፣ በዚህ ሞዴልም ቢሆን ለማዳመጥ ክሂል ማጎልበት የራሱ የሆነ ድርሻ ኣለው። ምክንያቱም በተለያዩ አካሄድ ተማሪዎቹ እንዲለማመዱ ዕድል መስጠት ራሱ ትምህርት በመሆኑ ነው። ከዚያም በተጨማሪ ማዳመጥ እንደ ማህበራዊ ግንባታ ሲል፡- ከዚህ በፊት በተለያዩ ሙሁራን እንደተገለፀው ማዳመጥ ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች የበለጠ ሰዎች በማህበራዊ ኑሮአቸው ውስጥ የሚገለገልበት ክሂል ነው። ይህ ሲባል ማዳመጥ ድምፃችን በመቀበል ብቻ ሳይሆን የሚተላለፈውን መልእክት በትኩረት በማዳመጥ በሰዎች አእምሮ የሚቀረፁ ከዚያም ባሻገር የመተርጎም ስራም እንደሆነ ነው። ስለሆነም ማዳመጥ የአድማጩ ልዩ ትብብር የሚሻ ክሂል መሆኑን መገንዘብ ተችሏል።እንዲሁም ማዳመጥ የቋንቋ መማርን የሚደግፍ ቁልፍ ችሎታ በመሆኑ እንደዚህ ያሉት ሞደሎች ተማሪዎች በማዳመጥ ወቅት እንዴት አዲስ ቋንቋ እንደሚያስኬዱ ያተኩራሉ።ስለዚህ ማዳመጥ ለቋንቋ እውቀት አስፈላጊ የሆነ ግን እንደሚሰጥ ነው። ምክንያቱም የሁሉም ቋንቋ ክሂሎች ዋና ምሶሶ የሆነው ማዳመጥ ነው። በማንኛውም የቋንቋ ትምህርት ውስጥ መጀመሪያ ቀድሞ የሚመጣው ይኸው ክሂል ነው።የሚደመጥ ነገር ካለ ሌሎቹ ክሂሎች ማለት መናገር ፣ማንበብና መፃፍ ተከታትለው ይመጠሉ። ማዳመጥ ከላይ ከተገለፁ ነጥብ በተጨማሪ መረጃን በሚገባ መንገድ መገንባት ላይ ትልቅ ድርሻ እንዳለው ከቀረበው ፅሑፍ መረዳት ይቻላል ። በመሆኑም ማዳመጥ ከላይ የተዘረዘሩት ፋይዳዎች የሚስጥ በመሆኑ በትምህርት ቤት ውስጥ ተማሪዎችም ሆኑ መምህራን ለክሂሉ ልዩ ትኩረት ሰጥተው በመስራት ለሌሎቹ ክሂሎች አቅም መፍጠር እንደሚቻል ነው።

በስድስተኛ ደረጃ የቀረበው ሞዴል የስነ–ልቦናዊ የማዳመጥ ሞዴሎች የሚለው ነው ።

አድማጮች ድምፃችን በቃላት →ቃላትን ወደ ስዋስዋዊ መዋቅር→ መዋቅሮች ወደ ትርጉም የሚቀየር በመሆኑ ተማሪዎች ከዚህ ሞዴል የሚጠቀሙት ነገር ከቃላት እስከ ትርጉም መቀየር የሚሰራበት ሂደት በመሆኑ የማዳመጥ ችሎታቸው ለማዳበር ፋይዳ ስላለው በሚገባ ብለማመዱ የተሻለ የማዳመጥ ችሎታ እንዲኖራቸው የሚረዳ ነው።

በመጨረሻ ለማዳመጥ ሁለንተናዊ አቀራረብ የሚለው ሲሆን፣ በዚህ ዘመናዊ አቀራረቦችንና ንድፍ ሐሳቦችን በአንድ ላይ የሚቀርብበት ሂደት በመሆኑ ተማሪዎችን የበለጠ የማዳመጥ ችሎታ እንዲኖራቸው እድል ሊከፍት ይችላል።

### 2.1.3 በማዳመጥ ክሂል ተግባራት ክንውኖች የተሰሩ ስራዎች ፡-

በማዳመጥ ክሂል ተግባራት ክንውን ከተሰሩ ስራዎች መካከል ለምሳሌ ፡- የአቴነሽ ተገኝ (1986) በኣዲስ ኣበባ ዩኒቨረስቲ በ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን ላይ ኣትኩሮ የተሰራ ጥናት ሲሆን ፣የዚህ ጥናት ርዕስም በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶች ትንተናና ግምገማ የሚል ነው ። በዚህ ጥናት ከተዳሰሱት ነጥቦች መካከል ፣ በመርሀ ትምህርቱ የማዳመጥ ክሂል ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶች ከተማሪዎች ፍላጎት አንፃር ሲታዩ በጣም አነስተኛና የተለያዩ የማዳመጥ አይነቶችን ያላካተቱ መሆናቸውን ተገልፃል። ከዚያም በተጨማሪ ይዘቶቹ የትኛውን ክሂል ለማዳበር እንደተፈለገ በግልፅና በዝርዝር እንደሚያሳዩ ተገልፃል ። ይዘቶቹም ሆኖ ከይዘቶቹ አንፃር የቀረቡት የክፍል ውስጥ ልምምዶች የተገለፁበት ቋንቋ ግልፅነት የጎደላቸው በመሆኑና ከዚህም ጋር የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን

የሚያዳብሩ ይዘቶች እንደተፈለገ  ለሻሚ ትርጉም እንደሚሰጡ  በጥናቱ ኣመልክቷል ። ሌላው በዚህ ስር የታዩት ክፍተቶች ይዘቶቹ ከመርሀ ትምህርቱ የቀረቡበት ቀደም ተከተል የክብደት ዳረጃቸው የጠበቀ  እንደልሆነ ነው ።

በኣጠቃላይ በዘጠነኛ ክፍል የኣማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥ ክሂል ተገቢውን ትኩረት እንዳላገኝ ተገልፃል ። ከዚም  በተጨማሪ  በማዳመጥ ክሂል በአጠቃላይ ኣላማና በዝርዝር  ዓላማ እንዲሁም በይዘት ምርጫ ደረጃ ከመናገር ክሂል ጋር ተደርቦ መቅረቡ ተገቢነት እንደሌለው ከጥናቱ መገንዘብ ይቻላል።

ቀጥሎ በአየለች ጩቃላ በማዳመጥ ክሂል ተግባራት ክንውን ዙርያ የተጠና ጥናት ነው። የዚህ ጥናት ርእስ በ8ኛ ክፍል ኣማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚመሩ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በ8ኛ ክፍል የቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት ክንውኖች የክፍል ውስጥ ኣተገባበር ግምገማ የሚል ሲሆን ፣በዚህ ጥናት ውስጥ እንደክፍተት የተነሱት ነጥቦች ፡-

 የማዳመጥ  ክህሎት አተገባበርን ስኬታማ ለማድረግ የመምህራን ሚና  ወሳኝ መሆኑ ይታወቃል።  ቢሆንም ተጠኚ መምህራን በዚህ ጥናት ላይ የሚጠብቀውን ሚና በኣግባቡ እንዳልታጡ በጥናቱ ውስጥ ለማወቅ ተችሏል።

ጠቅለል ባለመልኩ  የ8ኛ ክፍል  የኣማርኛ ቋንቋ  ተጠኚ መምህራን  በክፍል ውስጥ የሚደመጥ ክህሎትን  በሚፈለገው መጠን ትኩረት ስጥተው የሚተገብሩ ሳይሆን ኣልፎ ኣልፎ እንደማይተገበሩትና  ድክመት እንደሚታይበት  የጥናቱ  ውጤት ያሳያል። ሌላው በዚህ ጥናት ውስጥ  የታዩ ችግሮች  ወይም ተግዳሮቶች  መምህራን የተማሪዎችን  ወይም  የተጠኚዎችን የችሎታ  ሁኔታ አለመፈተሽ ፣ ከመማሪያ መፅሐፍ  ውጪ ተስማሚ  የሆኑ ይዘቶችንና  ክንውኖችን  በማዘጋጀት በትግበራው ወቅት አለመጠቀማቸው።

የተማሪ መማሪያ መፅሐፉንና የመምህሩን መማሪያ መፅሐፉን እንደብቸኛ ማስተማሪ ኣማራጭ መጠቀማቸው፣

ተጠኚ ተማሪዎቹ ለቋንቋው ትምህርት ያላቸው ኣሉታዊ ኣመለካከት፣

የቋንቋውን  ትምህርት  ለመማር ፍላጎት ማጣት ፣ በቋንቋው ትምህርት የሚያስመዘግቡት  ውጤት ዝቅተኛ በመሆኑ የቋንቋው ትምህርት የመጥላት ፣ መምህሩንም አብሮ የመጥላት ስሜት ማሳየት ፣

የተለያዩ ምክንት  በመፍጠር ከመማሪያ  ክፍል ጥለው መውጣት፣ የቡድን ውይይት ሲሰጣቸው ከርእስ ውጪ ወደ ግለ ሐሳባቸው በመሰብና፣ለክህሎቱ ትኩረት ኣለመስጠት በጥናቱ ሂደት የታዩ ተግዳሮቶች  እንደሆነ በጥናቱ ለማወቅ ተችሏል።

## 2.2 ቋንቋ መማሪያና መሳርያዎች

ቋንቋ ለማስተማር የሚያገለግሉ መሣሪያዎች የሚባሉት፡- የተማሪው መማሪያ መፅሐፍ፣መርሃ ትምህርትና የማስተማሪያ መሳሪያዎች ሲሆኑ ፣እነዚህ መሣሪያዎች ተጣጥመው መቅረብ የግድ ይሆናል።ከልሆነ ግን የመማር ማስትማር ሂደቱ ይደናቀፋል። ምክንያቱም ሦሶቱ የማስተማሪያ ግብኣቶች ለተማሪው ኣመቺ በሆነ መልኩ ካልተዘጋጁ የሚሰጠው የትምህርት ሂደት ሊጓተት ይችላል ።

ስለዚህ ከላይ የተገለፁ ችግሮች እንዳይከሰቱ የተማሪውን መፅሐፍ ከመምህሩ መመርያ መፅሐፍ ጋር ጥብቅ የሆነ ግንኙነት ያለው መሆን ተገቢ ነው።ምክንያቱም ለመምህሩ በቂ የሆነ ዕውቀት  ወይም ዓቅም እንዲያካብት (እንዲኖረው) ስለሚያግዙት በሚያካሂደውን የመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ኣስተማሪው በልበ ሙሉነት ትምህርቱን እንዲያስረምር ከማድረጉ ባለፈ ክሂሉን በኣጭር ጊዜ እንዲጨበጥ ከፍተኛ ድርሻ ኣለው።ከዚያም  በተማሪው መፅሐፍ ውስጥ ግልፅነት የሌላቸው ይዘቶች በመመሪያ መፅሐፉ በበለጠ ግልፅ በሆነ መልኩ ስለሚቀርብ መምህሩ ሳይጨናነቅ በድፍረት ለማስተማር ከማገዙም በተጨማሪ ለተማሪዎቹ በቂ የሆነ ዕውቀት እንዲቀስሙ ያደርጋል።

ከዚያም የማስተማርያ መሣሪያዎች ደግሞ በመፅሐፉና በመምህሩ መመርያ ያሉ ይዘቶች ወደ ክፍል ገብተን የምንተገብራቸው በነዚህ ስለሆነ ከማስተማሪያ መፅሐፍና ከመምርያ መምህሩ ጋር ተያያዥነት ያላቸው መሆኑ ትምህርቱ ኣጓጊና ማራኪ እንዲሆን ከፍተኛ እገዛ ኣለው።ምክንያቱም የማስተማሪያ መሣሪያዎች ለቀረቡት ይዘቶች በተግባር እንዲተገበሩ የሚያግዙ በመሆናቸው ሦስቱም ነገሮች የተጣጣሙ መሆን ከላይ እንደተገለፀው ትምህርቱ  ውጤታማ ከማድረጉ ባሻገር የትምህርቱ ሂደት ኣስደሳችና ማራኪ ስለሚያደርግ መጣጣም /መያያዝ/ ወሳኝ ነው። የተያያዙና የተጣጣሙ ግብኣቶች ለተማሪዎቹ ምቹነት ስለሚፈጥሩ፣ተማሪዎች ሳይሰለቹ የተሰጣቸውን መልመጃ ሁሉ በብቃት ይሰራሉ። ስለዚህ ስኬታማ የመማር ማስተማር እንዲፈጠር መጀመርያ የተማሪው መማሪያ መፅሐፍ፣የመምህሩ መምርያና የማስተማሪያ መሣሪያዎች የተያያዙ እና የተጣጣሙ መሆን ኣለባቸው።በዚህ መልክ የተደራጁ ከሆነ ዳግም ለተማሪዎቹ ምቹ የመማር ማስተማር ሂደት እንዲኖርያረጋሉ።ከዚያም የሚካሄደው ትምህርት ኣጓጊ እና ማራኪ ከመሆኑ የተነሳ ተማሪዎችን የሚያሳትፍ ነው።ይህ ብቻ ሳይሆን ማዳበር የተፈለገው ክሂልም በተፈለገው ጊዜ ማዳበር እንደሚቻል ኣያጠራጥርም።

የአስረኛ ክፍል የተማሪው መማሪያ መፅሐፍ እንደ ሁሉም የቋንቋ መፅሐፍት ኣስር ምዕራፎች የያዘ ሲሆን፣የምዕራፉ ይዘቶች ከመርሃ ትምህርቱ ጋር እኩል ይዘቶች ያሉት ነው። የአስረኛ ክፍል የተማሪው መማሪያ መፅሐፍ ከመርሃ ትምህርቱ ወይም ከመምህሩ መመሪያ መፅሐፍ ጋር ተዛምዶ ያለው ነው።በመሆኑም በመረሐ-ትምህርቱ ያሉ ጥንካሬዎችና ድክመቶችም በመማሪያ መፅሐፉም  ይታያሉ ማለት ነው።የተማሪው መማሪያ መፅሐፍ በየ ዘመናቱ ይለወጣል።ከዚያም መፅሐፍ ለብዙ ዓመታት ኣገልግሎት ሲሰጥ በመምህራንና በሙሁራን የተለያየ ግምገማ በመፅሐፉ ካደረጉ በሃላ በግምገማው መሰረት በተሻለ መልኩ ይዘጋጃል ማለት ነው። መፅሐፉ ሲዘጋጅ ዳግም ወጪ ይጠይቃል። ስለዚህ በተለያየ ግዚ ወጪ እየወጣ የሚታተም በመሆኑ፣መፃሐፉን እንዳይበላሽ ተማሪዎች በእጃቸው ያለውን መፅሐፍ በጥንቃቄ እንደይዙመሞከርና መቆጣጠር የሁሉም ሓላፊነት መሆን ኣለበት። ከዚያም በተጨማሪ የተማሪው መመሪያ መፅሐፍ እያንዳንዱ ተማሪ ከተሰጠ ወይም ከተደረሰ የመማር ማስተማር ሂደቱ እንዲፈጥን ከማድረጉም ባሻገር ተማሪዎች እንዲሳተፉ ያደርጋል። በመሆኑ ትምህርቱ የተሳካና ኣስደሳች እንዲሆን ያግዛል።

### 2.2.1 የአስረኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ

የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ ለመምህሩ ይሁን ለተማሪው በጣም ኣስፈላጊ ቁስ ነው።ምክንያቱም የመማር ማስተማር ሂደቱ በተፋጠነ መልኩ እንዲ ካሄድ ያደርጋል። ከዚያም የሚሰጠው ትምህርት ውጤታማ እንዲሆን ያግዛል።በተጨማሪም በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የትምህርት ይዘቶች ተካተው ይገኛሉ። ስለዚህ ኣንድ መምህር ለማስተማር ከሚያስፈልጉት ቁሶች ኣንዱ የተማሪ መፅሐፍ ነው።በመሆኑም የዓመቱ ትምህርት እንዴት ማስተማር እንዳለበትና መቼ? ማስተማር እንዳለበትበመጀመርያ እቅድ ያወጣል።የዕቅድ ዓይነቶች ዓመታዊ፣ወርሓዊ፣ሳምንታዊና ዕለታዊ በማለት ተከፋፍለው

ይወጣሉ።እነዚህ ዕቅዶች የሚወጣው ከተማሪው መማሪያ መፅሐፍና ከመርሃ ትምህርቱ ጋር በማጣጣም ነው።ስለዚህ የተማሪው መማሪያ መፅሐፍ ለመምህሩ የትምህርት ሂደት ከየት ተነስቶ የት ቦታ ማቆም እንዳለበት ኣቅጣጫ የሚያሳይ ነው።ከዚያም መምህሩ ክፍል ውስጥ ገብቶ ከማስተማሩ በፊት የመፅሐፉን ይዘት ምን እንደሚመስል ለመገንዘብ ያስችለዋል።ስለሆነም ለሌሎች ኣጋዥ ወይም ዋቢ መፅሐፎች ለመጠቀም ያግዘዋል ማለት ነው። ከላይ የተገለፁት ሓሳቦች የተማሪ መማሪያ መፅሐፍ ለመምህሩ የሚሰጡት ኣገልግሎት ሲሆኑ፣ቀጥሎ ዳግሞ ለተማሪው ያለው ፋይዳ መግለፅ ይሆናል። ከላይ እንደተገለፀው መማሪያ መፅሐፍ ለተማሪዎች ከፍተኛ እገዛ ያለው ግብኣት ነው። ምክንያቱም ተማሪዎች የተማሪው መማሪያ መፅሐፍ በኣቅራባያቸው ካለ ከክፍል ውጭ ይሁን ከክፍል ውስጥ እርስበርስ ሊለማመዱበት ይችላሉ። በዚያው ልክ ደግሞ ተማሪዎች ኣቅማቸውን ከፍ እንዲል ያግዛቸዋል። መማሪያ መፅሐፉ ለሁሉም ተማሪ ካልደረሳቸው ግን የመማር ማስተማር ሂደቱ ኣስልቺ ሊያደርገው ይችላል። በኣሁኑ ወቅት የኣማርኛ ትምህርት እንደ የትምህርት ዓይነት ትኩረት እየተሰጠው ባለመሆኑ የተማሪ መማሪያ መፅሐፍ አስፈላጊ ቢሆንም በክፍል ውስጥ ኣንድ መፅሐፍ እንካን ማግኘት ኣልተቻለም። ይሁን እንጂ  ለትምህርት ዓይነቱ ኣናሳ ግምት መሰጠቱ ከነበረው ችግር እንደገና ተጨማሪ ችግር ሆኖ ይታያል። ምክንያቱም ከዚህ በፊት እንደ ችግር ነው ብዬ ለጥናት ያቀረብኩት የማዳመጥ ክሂል ለማዳበር እንቅፋት የሆኑትን ነገሮችን ነበር። ኣሁን ግን ክሂል ለማስተማር በመፅሐፉ ይዘት ቢወጣም የተሰጠው ጊዜ ጥቂት በመሆኑ፣የማዳመጥ ክሂልም ለማስተማር ዕድል ተዘግቷል።

ከላይ ለመግለፅ እንደተመከረው የኣስረኛ ክፍል መማሪያ መፅሐፍ ኣስፈላጊነት በተመለከተ በወሳኝ መልኩ የተገለፁ ሓሳቦች ቅላል ኣድርጎ ለመግለፅ ያክል፣የመማሪያ መፅሐፉ ኣስፈላጊነት ነው።ምክንያት መምህሩም የመማር ማስተማር ሂደቱ የሚመራው በመማሪያ መፅሐፉ በመሆኑ ያለ መማሪያ መፅሐፍ ትምህርት ማስተማር አይቻልም ።

## 2.3. የማዳመጥ ክሂል ትምህርት ምንድን ነው?

የማዳመጥ ክሂል ከአራቱ ክሂሎች አንዱ ሲሆን ማዳመጥ እንደ መናገር በእያንዳንዱ ማህበረሰብ ውስጥ  ያለ፣ተማሪዎች ከማሕበረ ሰቡ ጋረ በመሆን የሚያገኙት ቢሆንም ክሂሉ ከሌሎች ክሂሎች ቀድሞ የሚገኝና ለክሂሎቹ ዋና መሰረት ስለሆነ ተማሪዎቹ ከማሕበረሰባቸው ይዘውት የሚመጡ ወይም የለመዱትን የማዳመጥ ክሂል በበለጠ እንዲዳብር በትምህርት ቤት ውስጥ በሙያው የሰለጠነ መምህር ተመድቦለት ፣መማርያ መፅሐፍ ተዘጋጅቶለት፣ቦታና ጊዜ ተበጅቶለት በሥርዓት ሲሰጥ የማዳመጥ ትምህርት ሊባል ይችላል።

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው አንድ ክሂል በትምህርት ቤት ውስጥ መስጠት ተማሪዎቹ ንቁ ተሳታፊዎች እንዲሆኑ፣ እንዲሁም ሐሳባቸው ለሌሳ አካለ በትክክል ማስተሳለፍ ወይም መግለፅ እንዲችሉ  በተጨማሪም ከአጋሮቻቸው ጠቃሚና ገንቢ ሐሳብ ለመቀበል እንዲችሉ ለማድረግ ነው።

ስለሆነም የማዳመጥ ክሂል በትምህርት መታገዝ ለሌሎች ክሂሎች እንዲዳብሩና እንዲበለፅጉ ማድረጉ መልካም ነው ምክንያቱም ተማሪዎች በማንኛውም የቋንቋ ክሂለ የነጠቁ ቢሆኑም የበለጠ ለሚማሩት የትምህርት ዓይነት ሁሉ ጥሩ አቀባበል እንዲኖራቸው አወንታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል።ቀጥሎ የማዳመጥ ትምህርት ምንድን ነው የሚለውን የዘርፉ ምሁራን የተለያየ ሐሳብ አቅርበዋል ።

Grant (1989፤19-20)እንደገለጹት የማዳመጥ ትምህርት ተማሪዎች የተለያዩ ድምፃችን ለመለየት እንዲችሉ፣በተግባር የሚለማመዱበት ሂደት ነው። ይሁን እንጂ በርካታ የዘርፉ ምሁራን የዚህ ክህሎት ትምህርት ተገቢ ትኩረት የተሰጠው

አይደለም ለዓብነት ብንጠቅስ፣Kiary(1996:32) —በበርካታ አገሮች አዳምጦ መረዳት የተማሪዎችን ችግር ነው“ ይላሉበበኩላቸው የክፍል ውስጥ የማዳመጥ ትምህርት የአፈፃፀም ሂደትን በተመለከተ በሚከተለው መንገድ ያብራራሉ። የክፍል ውስጥ የማዳመጥ ትምህርት ሂደቶች /ክንውኖች/ ተፈጥሯዊ የማዳመጥ ተግባራት የሚያሟሉ ናቸው። የማስተማሪያ መጻህፍት ይዘቶችንም ከተለያዩ መፃህፍትና ፅሑፎች የተቋቋሙ ተማሪው ለምን እንደሚያዳምጥ ምን እንደሚፈልግ ለማወቅ የሚያዳምጧቸው በማለት ገልፀዋል።

እንደUnder Wood (1989:4) አመለካከትም ቀደም ባሉት ግዚያት የማዳመጥ ክሂሎች ትምህርት የሚያስፈልገው ተደርጎ አይቆጠርም ነበር።ማስተማር ማለት የመማር ሂደትን መደገፍ ነው። ብለን ከተረዳንና የመምህሩ ሚናእንደረዳትነት ከወሰድነው የማዳመጥ ትምህርት አስፈላጊነት እንረዳለን ይላሉ።

Rixo (1983:1) —የማዳመጥ ክህሎት በማሕበራዊ ሂወትና ልምድ የሚገኝ ስለሂነ ትምህርት አያስፈልገውም።ብለው የሚያምኑ ጥቂቶች እንዳልነበሩ ጠቁመዋል“ ማዳመጥ መልእክት ወደ ጆሮ መድረስ ሳይሆን የደረሰውን መልእክት መረዳትና መተርጎምን የሚያካትት ነው። ስለዚህ ትምህርት የሚባለውም ተማሪዎችን በዚህ መልክ የማዳመጥ ክሂሎችን ለማለማመድ በክፍል ውስጥ የሚያከናውኑት ተግባር ነው (Under Wood፤1989:4)።

ከዚህ በላይ ከተገለፁት ሃሳቦች የምንረዳው ነገር ካለ የማዳመጥ ትምህርት ከሌሎች ክሂሎች በበለጠ ቢሰጥ ይጠቅማል። ምክንያቱምማዳመጥ ከኣራቱ ክሂሎች ኣንዱና በማንኛውም ማህበረሰብ ውስጥ በማህበራዊ ኑሮው በተደጋጋሚ ወቅት የሚገለገልበትና ከፍተኛ ቦታ የያዘ በመሆኑ፣በትምህርት ቤት ውስጥ ቢሰጥ የበለጠ ሊያድግ የሚችል መሆኑንና ለሌሎች ክሂሎችም ምሶሶ ወይም መሰረት ስለሆነ ሙሁራኑ እንደየደረጃቸው እንዲያድጉ በትምህርት መታገዝ የግድ እንዲሆኑ ይገልፃሉ።

የማዳመጥ ክሂል ከሌሎች ክሂሎች ክፍተኛ ቦታ የያዙ ቢሆንም እስከ ኣሁን ድረስ ግን በቋንቋ ትምህርት ትኩረት ያላገኙ በመሆኑ፣በዚያ የተነሳ ተማሪዎች በክሂሉ በቂ የሆነ ኣቅም የሌላቸው መሆኑን ከክፍል ውስጥ የምናደርገው ሚዛንና ፍተሻ ያለው ችግር መገንዘብ ተችሏል ።ስለሆነም ለማዳመጥ ክሂል ያለው ኣናሳ ትኩረት ለማሻሻል መፍትሔ የሚሆነው በዘመናዊ የማስተማሪያ ዘዴዎች ወደ ክፍል ውስጥ ይዞ በመግባት ለተማሪዎቹ በሚማርክ መልክ ትምህርቱን ማቅረብ ይሆናል።

ስለዚህ የማዳመጥ ክሂል በታሰበ ሁኔታ ለማስተማር ወይም ክሂሉን ለማዳበር የማስተማሪያ ዘዴዎችና መመሪያዎች በሚደመጡ ይዘቶች በኣግባቡ ለመከወን ወይም ለመተግበር ምን ምን መመሪያዎችና ምን ዓይነት የማስተማርያ ዘዴዎችን ተጠቅመን የመማር ማስተማር ሂደቱን መተግበር ወይም መከወን እንዳለብን በሚገባ ማወቅ ተገቢ ነው።

## 2.4 የማዳመጥ ተግባር ንድፍ መርሆዎች

የማዳመጥ ተግባር ንድፍ መርሆዎች ከሚለው ርዕስ ጉዳይ መረዳት የሚቻለው ፣ በመጀመሪያ አንድ የሚደመጥ ርዕሰ ጉዳይ ወይም ተግባር የራሱ የሆነ ንድፍ መርሆዎች አሉት ። ይኸውም በአንድ ተግባር ውስጥ ተማሪዎች ለሚሰሙት ነገር ወይም ለሚያዳሙጡት ፍሬ ሓሳብ ምላሽ ለመስጠት የእያንዳንዱ ተማሪ የራሱ የሆነ የአቀባበል ሥርዓት ወይም ግንዛቤ ምን ያህል አቅም እንዳለው የሚያሳይ ይሆናል ። ከዚያም ምላሽ የመስጠት ዕድልን ለማካተት አስፈላጊነት ባሻገር ፣ ዑር(1984) ትኩረትን ወደ 6 ተጨማሪ ገፅታዎች ያስገባ መሆኑን ነው። ይህም ሲባል በማዳመጥ ተግባር እቅድ ውስጥ መታየት እንዳለበት ተገልፃል ።

1.አስቀድሞ የተዘጋጀ ዓላማ፡- በመጀመሪያ በአንድ አድማጭ በእውነተኛ ህይወት መስተጋብር ውስጥ ማለት በህይወቱ በዕለተ ዕለት እንቅስቃሴው የሚተገብራቸው ስራዎች ሁሉ በሚደመጠው ነገር ውስጥ መገኘት እንዳለበት ፣ ከዚያም ባሻገር ለአንድ አድማጭ የሚደመጥ ነገር ሲቀርብለት ከትክክለኛ ህይወት መነሳት እንዳለበት ነው። አድማጩም ቢሆን ላዳምጣሉህ የሚል ዓላማ ኑሮት የሚቀርብለትን የሚዳመጥ ንባብ ወይም ንግግር በንቃት ማዳመጥ ሲችል ነው። በተጨማሪም ምላሽ መስጠት የሚደመጠውን ነገር ውጤታማ እንደሆን ማድረግ ነው።

2.ቀጠይነት ያለው የተማሪ ምላሽ፣ ተማሪዎች ከተለያዩ ተግባራት ቁምነገር ሲጨብጡ ወይም ሲያዳምጡ ይችላሉ ። ስለዚህ በአብዛኛው የእውነተኛ ህይወት ማዳመጥ በአድማጩ በኩል ፈጣን ምላሽን እንዲገኝ ያግዛል። ግን በክፍል ውስጥ ብዙ የማዳመጥ እንቅስቃሴዎችን ጽሑፉ ከተደመጠ በኋላ ምላሾችን እንዲሁም ሰፉ ንባብ እና የመፃፍ ገጽታዎችን ያጠቃልላል።እንዲሁም አንድ አስተማሪ የአንድን ክፍል የተናገራቸውን ምላሾች መፈተሽ ከባድ ሲሆን ይችላል። ሆኖም ግን በድምፅ ችሎታዎች ሳያተኩር ሌሎችን ሲያካትት እና የአንድን ሙሉ ክፍል ስኬት መከታተልን ለማመቻቸት ቀጠይነት ያለውና ፈጣን ምላሾች ለመስጠት የሚያስችሉ ተግባራትን እንዲጠቀሙ ኡር( 1984 ) ይመክራል ።

ቀላል ምስሎችን ስዕላዊ መግለጫዎችን ፍርግርግ ካርታዎችን እና የአካላዊ እንቅስቃሴ መጠቀም የዚህ ምሳሌዎች ናቸው።

3. ተነሳሽነት ፡- መምህራን ተግባራትን ሲያስተምሩ ሲያቅዱ የተማሪዎችን ለቋንቋ ትምህርት ተነሳሽ የሚያደርጉት መስጠት ተገቢ እንደሆነ ተገልፃል።

መምህራን የቋንቋ ትምህርት ሲያስተምሩ ተማሪዎችን ሲያነቃቁ ወይም ሲያነሳሱ የሚችሉትን ተግባራት መርጠው ማካተት አለባቸው ። ይህ ሲሆን የሚችለው ግን እቅድ አውጪዎች የሚያቀርቡት ተግባራቱ ሳቢ፣ አዝናኝና ማራኪ አድርገው እንዲያወጡ አስፈላጊ መሆኑን ተገልፃል ። ለምሳሌ፡- በሁሉም እድሜ ክልል ውስጥ ያሉት ተማሪዎች እንቋቁልሽ መፍታትና ጨዋታ መሰል ባህርያት በሁሉም የክፍል ደረጃ ተጠቅሞ በማስተማር የተማሪዎችን ተነሳሺነት ከፍ እንዲል በማድረግ ውጤታማ የመማር ማስተማር ሂደት መፍጠር እንደሚቻል ነው። ስለዚህ የሚደመጠው ርዕስ ምርጫ ለተማሪዎቹ የሚማርካቸው ከሆነ በክፍል ውስጥ የተነሳሽነት መንፈስ እንዲገለብት በር ይከፍታል ።

4. ስኬት ፡- —ተግባራት ስኬትን ያማከለ መሆን አለበት“ ሲል ዑር (1984) ገልፃል ። ከሙሁሩ አገላለፅ መገንዘብ የሚቻለው ስኬታማ ለመሆን የሚሰጡ ተግባራት በጣም ከባድ ወይም ቀላል መሆን እንደሌለባቸው ነው ። ስለዚህ ስኬታማ መሆን የሚቻለው የተግባሩ ዓላማ የመስማት ችሎታ ማሰልጠን ወይም ማስተማር እንጂ መፈተሽ አዳልሆነ መረዳት ይቻላል። ስለዚህም ተደጋጋሚ ውድቀት ከስልጠና አንፃር ብዙም ውጤታማ እንድንሆን አጋዥ መሆኑ ነው። ምክንያቱም ሰው ከስህተቱ መማር እንደሚችል ያስረዳናል። ስለዚህ ውጤታማ ለመሆን በተደጋጋሚ መስራትና መለማማድ እንዳለብን ነው። በተደጋጋሚ መስራት ወይም መለማማድ ስህተትህን ለማረም አጋዥ ነው።

5.ቀላልነት ፡- ከ ዓላማ አንፃር ተግባሮችን በተቻለ መጠን ቀላል ቢሆኑ የተሻለ እንደሆነ ነው። ምክንያቱም፡- የመለማማጃ ተግባራት ሲቀርቡ ከተነደፈው ዓላማ ጋር የተሳሰረና የተቀራኘ መሆን፣ ከዚያም የሚሰጡት ተግባራት ለምን ዓላማ እንደሚሰጡ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶባቸው ከሆነ ለተማሪዎቹ ቀላል ሲሆኑ ይችላሉ።

-በአጠቃላይ ቀላልነት የሚለው የመለማመጃ ተግባራት አቀራረብ ከተማሪዎቹ የክፍል ደረጃ የወረደ ማለት ሳይሆን ተማሪዎቹ እንዲለማመዱ ዕድል በሚሰጥ መልኩ መቅረብ ሲችል ነው ። ተማሪዎች አብዛኛው ጊዜ ተግባራት ቀለል ባለ መንገድ ሲቀርብላቸው ንቁ ተሳታፊዎች እንዲሆኑ ያደርጋል ። ምንም ሳይጨናነቁ ተዝናንተው ሓሳባቸውን ከቻሉ በራስ መተማመን ስሜት በውስጣቸው ያካበቱት ነፃነት መግለፅ በልበ ሙሉነት ስሜት ይሰማቸዋል። ስለሆነም ለሚሰሩት ነገር የራስ መተማመን እንዲኖራቸው ዕድል ይከፍታል ። ስለዚህ ቀላል ተግባራት በመስጠት ወይም በማቅረብ የተማሪዎቻችን ክሂል ለማዳበር ይቻላል ማለት ነው ።

6.ግብረ መልስ ፦ በመናገር እና በማዳመጥ ተግባራት ውስጥ መምህራን ግብረ መልስ ለመስጠት ማቀድ አለባቸው። ምክንያቱም ግብረ መልስ በጊዜም ተማሪዎች ካላገኙ ያለፈውን ስህተት ሲደግሙት ይችላሉ። ከዚያም ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ስህተቶችን እንዲረሱት ዕድል ሲከፍት ስለሚችል መጠንቀቅ ተገቢ ነው።

ከዚያም በተጨማሪ መምህራን ለተማሪዎችን በጊዜው ማለት በሰዓቱ ግብረ መልስ ካልሰጠናቸዉ የመስራት ፍላጎታቸው ይቀንሳል ።በመሆኑም ለክሂሉ ማዳበር አሉታዊ ተፅና ሰለሚያሳድር ግብረ መልስ በጊዜ መስጠት አስፈላጊ መሆኑን ትኩረት ሲደረግለት ይገባል ።

በአጠቃላይ የማዳመጥ ተግባራት ንድፍ መርሆዎች ከሚለው የተሰነዘረው ቁምነገር መገንዘብ የሚቻለው በአንድ የሚደመጥ ፅሑፍ ወይም ተግባር የራሱ የሆነ ንድፍ መርሆዎች እንዳሉት ተገልፃል። ይኸውም በአንድ ተግባር ውስጥ ተማሪዎች ለሚሰሙት ቁምነገር ምላሽ ለመሰጠት የእያንዳንዱ ተማሪ የራሱ የሆነ የአቀባበል ሥርዓት ወይም ግንዛቤ ምን ያህል አቅም እንዳለው የሚያሳይ መሆኑን ነው ። እንዲሁም ምላሽ የመስጠት ዕድልን ከማካተት አስፈላጊነት ባሻገር ፣ ዑር (1984) ትኩረትን ወደ 6 ተጨማሪ ገፅታዎች ያስገባ መሆኑን ነው ። ይህም በማዳመጥ ተግባር እቅድ ውስጥ መታየት እንዳለበት መገንዘብ ይቻላል ። ይኸውም አስቀድሞ የተዘጋጀ ዓላማ ፦ በመጀመሪያ አንድ አድማጭ በእውነተኛ ህይወት መስተጋብር ውስጥ ማለት በህይወቱ በዕለተ ዕለት እንቅስቃሴው የሚተገብራቸው ስራዎች ሁሉ በሚደመጠው ነገር ውስጥ መገኘት እንዳለበት ከዚያም በተጨማሪ አድማጩ አንድ የሚደመጥ ነገር ሲቀርብለት ከትክክለኛ ህይወት መነሳት መቻል ፣ አድማጩም ቢሆን ለሚቀርብለት የሚደመጥ ፅሑፍ ይሁን ንግግር ዓላማ ኑሮት ማዳመጥ ሲቻል እንደሆነ መገንዘብ የግድ ይሆናል ።

ሌላው ከተጠቀሰው ሓሳብ ቀጣይነት ያለው የተማሪዎች ምላሽ የሚለው ሲሆን፣ ተማሪዎች ከተለያዩ ተግባራት የተለያየ ቁምነገር ሲጨብጡ ወይም ሲረዱ ይቻላሉ ። ስለዚህ ከፅሑፍ ይሁን ከድስኩር ያከበቱት ሓሳብ ወይም ያዳመጡት መልእክት ተመልሰው ምላሽ መስጠት ሲችሉ ነው።

እንዲሁም ተማሪዎች ቀጣይነት ያለው ምላሽ በተገቢው መንገድ እንዲሰጡ መምህራን ሲያስተምሩ ቀላል ያሉ ተግባራትን መርጠው መስጠት ፈጠነው ምላሽ እንዲያቀር ቡ ያግዛል። ለምሳሌ፦ ስዕላዊ መገለጫዎችን፣ ፍርግርግ ካርታዎችንና የአካላዊ እንቅስቃሴ ምላሾችን መጠቀም የሚሰጠውን መለማጃ ተግባራት ቀላል እንዲሆኑ የሚያግዙ መሆናቸውን ከፅሑፉ መረዳት ይቻለል። በመቀጠል ተነሳሽነት በተመለከተ ነው። መምህራን ተግባራትን ለማስተማር ሲያቅዱ የተማሪዎችን የቋንቋ ትምህርት የሚያነሳሱና የሚያነቃቁ ርዕሰ ጉዳዮችን መርጠው መስጠት ተገቢ እንደሆነ ተገልፃል። እንዲሁም በ4 ደረጃ የተገለፀው ስኬትን በተመለከተ የቀረበ ሓሳብ ሲሆን ፣ እነደ ሙሁራ አገላለፅ ስኬታማ

ያለው የማዳመጥ ሂደት እንዲኖር ከተፈለገ የሚቀርቡ የሚደመጡ ተግባራትን ስኬትን ያማከለ መሆን አለበት ። ሲል አፅንኦት ይሰጣል ። የማዳመጥ ተግባራት ሲቀርቡ በጣም ከባድና በጣም ቀላል እንዳይሆኑ መጠንቀቅ ተገቢ ነው። ስለዚህ ተግባራቱ ከተማሪዎች አቅም የተመጣጠኑ የተማሪዎችን የማዳመጥ ፍላጎት የሚያነሳሱ ከሆነ የሚደመጠው ተግበር ስኬታማ ሲሆን እንደመችል መገንዘብ ይቻላል ። በመቀጠል ቀላልነት የሚለው ሲሆን ፣ የሚደመጡ ተግባራት ከተማሪዎች ዕድሜና የክፍል ደረጃ በቀላሉ ለተማሪዎቹ በሚረዳቸው መልክ ማቅረብ መቻል ነው። ይህ ሲባል ግልፅነትና ለተማሪዎቹ ሲያሳትፉ የሚችሉ ከውስብስብነት የፀደ ከሆነ የተማሪዎችን የመስራት ፍላጎት ስለሚያበራታቱ እንደልብ ማዳመጥና የሚተላለፈውን መልእክት ለተማሪዎቹ በቀለሉ በአጭር ጊዜ ሲጨብጡ በሚችሉት መንገድ ማቅረብ መቻል ነው ። መጨረሻ የቀረበው ግብረ መልስ የሚለው ነው።

ግብረ መልስ በማዳመጥ ተግባር ይሁን በመናገር ተግባራት ውስጥ መምህራን በተቻለ መጠን ግብረ መልስ ለመስጠት ማቀድ አለባቸው። ከልሆነ ግን ግብረ መልስ ለረጅም ጊዜ ካልተሰጠ ስህተቶችን ለማረም እንቅፋት ይሆናሉ። ከዚያም ባሻገር ተማሪዎች የመስራት ተነሳሽነታቸው እንዲቀንስ ያደርጋል ።

→ ስለዚህ ከስህተት መማር እንደሚቻል ግምት ውስጥ በማስገባት መምህራን ጊዜ ሳይወስዱ ግብረ መልስ በመስጠት ተማሪዎች ስህተታቸውን ተሉ እንዲያርሙ ማድረግ ተገቢ ነው ።

ማጣቀሻዎች Lund , R. J. (1990) ሁለተኛ ቋንቋ ማዳመጥን ለማስተማር ታክሶኖሚ. የውጭ ቋንቋ ዘገባዎች ፣23 (2)፣ ገጽ 105-115። ኡር ፣ፔኒ (1984) የማዳመጥ ግንዛቤን ማሰተማር ። ካምብሪጅ ፡ የካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ

## 2.5 ማዳመጥን የማስተማር አዳዲስ መንገዶች

የማዳመጥ ክሂል ለማስተማር ከተማሪዎችን የክፍል ደረጃና የማዳመጥ ችሎታ ማነስ ጋር ክሂሉን ለማስተማር ኣስቸጋሪ ነው።ምክንያቱም የእኛ ተማሪዎች ኣማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው በመሆኑ ፣የሚቀርብላቸው የሚዳመጥ መለማመጃ ተግባራተ በኣግባቡ ኣዳምጠው ያዳመጡትን ፍሬ ሐሳብ ወይም ጭብጥ የመተርጎም ፣የመተንተንና በትክክል ለመግለፅ ይቸገራሉ።ይህ ችግር በማስተምርበት ክፍል ማለት በዘጠነኛ እና ኣስረኛ ክፍል ከኣስራ ኣምስት ኣመታት በላይ ኣስተምርያለሁ።

ከላይ የጠቀስኩት ኣመታት ሳስተምር ያጋጠመኝ እክል ወይም ችግር ቢኖር ተማሪዎች ለቀረበላቸው የሚደመጡ መልመጃ ይዘቶች በትክክል ኣዳምጠው ተመልሰው መግለፅ ይቸገሩ እንደነበሩ ራሴያየሁት ነገር ነው። ስለዚህ የተገለፁት ችግሮች መፍትሄ ይሆናል ብዬ የሚገመተው በኣዳዲስ የማስተማርያ ዘዴዎች ወይም መንገዶችን መጠቀሙ የበለጠ ስኬታማ ሲያደርገን ይችላል። ምክንያቱም ተማሪዎቹ እንደ ትግርኛ ተናጋሪ እንደመሆናቸው መጠን ከላይ የተዘረዘረው ሐሳብ መነሻ እንኳን ቢሆን በሌላ ደረጃም ሲታይ ከተለመደው የማስተማር ዘዴ መልክ የሚደመጡ ነገሮችን ማቅረብ ፣ሌላው ችግር በመሆኑ ኣዳዲስ መንገዶች ወይም ዘዴዎች ብንጠቀም የመማር ማስተማር ሂደቱ ኣትጊና ማራኪ ይሆናል።

ለምሳሌ ፦በንባብ መልክ ከማቅረብ ይልቅ የተሳያዩ ኣሳታፊ የሆኑ ይዘቶችን መርጦ በድምፅ (ቀርፃ) በክፍል ውስጥ ማቅረብ ከተቻለ ከነበረው የማስተማሪያ ዘዴ ወጣ ያለ ወይም ኣዲስ መንገድ በመሆኑ ፣ተማሪዎቹ እንዲነቃቁ በር የሚከፍት ኣካሄድ ነው። በመሆኑም የማዳመጥ ክሂል ዳግም ለሌሎች ክሂሎችም ምሶሶ እንደመሆኑ መጠን ተማሪዎች የሚቀርብላቸው የሚደመጡ ተግባራት በኣግባብ ከጨበጡ ያዳመጥቱን የመተርጎም፣የመተንተንና የመግለፅ ዕድል ይኖራቸዋል።ከዚያም

ተማሪዎች ካዳመጡት ይዘት ወይም ፍሬ ሐሳብ ስሌሳ ኣካል መግለፅ ወይም ማሰረዳት ከቻሉ በእግረ መንገዳቸውም የመናገር ክሂሳቸውን ያዳብራሉ። ከዚያም ከሌሳ ኣካል ሐሳብ ስመቀበል ኣይቸገሩም።

በኣጣቃሳይ ኣዳዲስ የማስተማርያ መንገዶች መጠቀም የሚናስተምረው ትምህርት ወይም ክሂል እንዲዳብርና እንዲበለፅግ ከማድረጉም ባሻገር የተማሪዎች ሞራል ከመጠበቅ ኣኳያ ከፍተኛ ድርሻ ይኖረዋል።ከዚያም ተማሪዎችን ብቁ ሆነው እንዲወጡ የሚያግዝ ኣካሄድ በመሆኑ ፣ስማዳመጥ ክሂል ብቻ ሳይሆን ስሌሎች ክሂሎችም ቢሆን ፣ስቀጣይ በኣዳዲስ የማስተማር ዘዴዎችን ስመጠቀም መጣር ነው።

## 2.6 የማዳመጥ ክሂል የማስተማሪያ የትምህርት ተግባራት

የማዳመጥ ክሂልበተሳካ ሁኔታ ስማስተማር ወይም ክሂሉን ስማዳበር የማስተማርያ ዘዴዎችና መመሪያዎች በሚደመጡይዘቶች በኣግባቡ ስመከወን ወይምስመተግበር ምን ምን መመሪያዎችና ምን ዓይነት የማስተማሪያዘዴዎችን ተጠቅመንየመማር ማስተማር ሂደቱ መተግበር ወይም መከወን እንዳስብን በሚገባ ማወቅ ተገቢ ነው።

በተጨማሪም የሚደመጠው ይዘት ኣቀራረብ ተማሪዎቹ የሚያከራክሩ ፣ የሚያነጋግሩና የሚወያዩ ከሆኑ በክፍል ውስጥ ጥሩ የሆነ የመማር ማስተማር ሂደት እንዲፈጠር ያግዛል።

### 2.6.1የማዳመጥ ክሂል ማስተማሪያ የትምህርት ተግባራት አመራረጥ

የማዳመጥ ክሂልን ስማዳበር የትምህርቱ ኣሰጣጥ በተቻስ መልኩ ስተማሪዎች የሚያሳትፍ፣ የሚያወያይ ቢሆን ይመረጣል። ከዚያም ዘመናዊ የማስተማሪያ ዘዴዎች መጠቀም ክሂሉን በተወሰነ ግዚ ማስጨበጥ ይቻላል። ከተስያዩ ሙሁራን ሐሳብ መረዳት እንደተቻስው ማዳመጥን ስማስተማር የተስያዩ መመርያዎችና ደረጃዎችን እንዳሉ ነው። እነሱም ቅድመ ማዳመጥ፣ የማዳመጥ ጊዜና ድህረ ማዳመጥ ናቸው ።

1 ቅድመ ማዳመጥ ተግባራት ፡-

Rost (1990፣39 ) እንደሚያብራሩት የቅድመ ማዳመጥ ተግባራት ተማሪዎችን ስዋናው ዳመጣ የሚዘጋጁ እና የሚያነቃቁ መሆን ኣስባቸው ። የዚህ የቅድመ ማዳመጥ ተግባራት ዋና ኣላማቸውም ተማሪዎቹን በማነሳሳት እና ስሜታቸውን በመቀስቀስ ንቁ ኣዳማጭ እንዲሆኑ ማድረግ ነው ። በቋንቋ መማሪያ መፅሓፍ ውስጥ የሚያቀርቡበት ቅድመ ማዳመጥ ተግባር በዚህ መልኩ መቃናት ይኖርባቸዋል። ከዚህ ሀሳብ ጋር በተያያዘ ማረው (1998፣137) በማዳመጥትምህርት ሂደት ውስጥ ተማሪው ቀጥሎ ምን እንደሚያዳምጥና ስምን እንደሚያዳምጥ በመንገር፣ወይም ዳግም እንዲገምት በማድረግ የትምህርቱን ኣቅጣጫ መጠቆም ይገባል።ይህም የሚሆነው መገመትን፣ዳራዊ ዕውቀትን መቀስቀስ እና ቁልፍ ቃላትን ማስተዋወቅ እና ከማዳመጥ ጋር የተገናኙ ተግባራትን ማከናወንን ኣካቶ ይይዛል።

Brown (2001፤6) ሁሉ ጊዜ የቅድመ ማዳመጥ ሥራን እንዲዘጋጁ ይመክራል። ይሀውም ሁሉት ዓይነት የቅድመ ማዳመጥ ሥራዎች ይጠቅሳሉ ። የመጀመርያዎች ሳይ እና ሁስተኛው ሳይ ማዳመጥ የኣድማጭ እይታን ስመረዳት በስዋስው እና በቃሳት ሳይ ማተኮርን ያመስክታል ታች ሳይ ያስው የቅድመ ማዳመጥ ተግባር ስኣድማጭ ፅሑፍ ማዕከላዊ የሆኑትን መዝገበ ቃላት ወይም ስዋስው ኣስቀድሞ ማስተማር ይሆናል ።

ሳይታች ማዳመጥ ዳግም የኣድማጭ ጹሑፍን ስመረዳት የቀድሞ ዕውቀትን ወይም የፅሑፍ መዋቀር መጠቀምን ያመስክታል። ስስዚህ ሳይ ታች ያስው የቅድመ ማዳመጥ እንቅስቃሴ ተማሪዎች ስስ ማዳመጥ ርዕስ የሚያቁትን

እንዲያስታውሱ መጠየቅ ያካትታል ። ለምሳሌ፡- የማዳመጥ ርዕስ ቡና መሸጥ ከሆነ ፣ ለዎች በቡና መሸጫ ውስጥ ምን እንደሚመለከቱ ተማሪዎችን መጠየቅ ይችላሉ። እነዚህም ተማሪዎች ለሰሙት ለስሚያስቡት የኣድማጭ ፅሑፍ ዓይነት የሚያቁት መጠየቅ ይችላሉ ።ወይም ምግብ ማብስያው ምግቡን እንዴት እንደሚሰራ የሚገልፅ ቪድዮ ከሆነ ፣ምግብ ማብስያ እያንዳንዱ የምግብ ኣዘገጃጀት መመሪያ ሲያብራራ (መጀመርያ፣ ከዚያ በኋላ ) ምን ቃላት ሲመጡ እንደሚችሉ ተማሪዎች እንደጠቀሙ መጠየቅ ። የቅድመ ማዳመጥ ደረጃውን በትክክል በኣጭር ማድረግ ኣስፈላጊ ነው። በኣማካኝ ኣንዳንድ ኣስተማሪዎች ከኣስር እስከ ኣስራ ኣምስት ደቂቃ የሚፈጀውን የቅድመ ማዳመጥ ሥራ እና የኣንድ ደቂቃ የማዳመጥ ፅሑፍ ተከትሉ እንደሚያሳልፉ ተናግሯል። ኣንድ ኣጭር ተግባርን መምረጥ እና ረጅም ጊዜ እንዲወሰድ ኣለማድረግ ።

በተጨማሪም ይህ ደረጃ ተማሪዎች ከሚቀርበው ንግግር ጋር ትውውቅ የሚያደርገበት ነው። እንዲሁም ተማሪዎችንየቅድመ እውቀት ሲጠየቁ የሚችሉ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ስለሚደመጠው ነገር እንዲገምቱ የሚያደርግበት ደረጃ ነው። Under Wood (1989) እንደሚገልፁት በዚህ የማዳመጥ ደረጃ መምህራን የተለያዩ ሃሳቦችን በማንሳት ተማሪዎች የመነቃቃት ስሜት እንዲፈጥሩ ማድረግ ፣ ከትምህርት ዙርያ ይነገራል ብለው የሚጠብቁትን ነገር በመጠየቅ እንዲገምቱ ማድረግ፣ ስትምህርት ይዘት በተገቢው መልኩ እንዲረዳ የኣዳዲስ ቃላት ፍቺ ስተማሪዎች ማሳወቅ ።

እንዲሰጡ ማድረግ ፣ በማዳመጥ ጊዜ ሲሠሯቸው የሚችሉትን ጥያቄዎችን በማዳመጥ ሂደት የሚከናወኑ ተግባራት እንዴት መሠረት እንዳለባቸው አጠር ያለ ማብራሪያ መስጠት ይኖርባቸዋል (Under Wood፣1989)።

በመጨረሻም ከመስማታቸው በፊት የማዳመጥ ሥራና ማዘጋጀት፡- ሥራውን በኣፍ መፈቻ ቋንቋ በአጭሩማብራራትና ኣስፈላጊ ከሆነ በቦርዱ ላይ መጻፍ። ዙሪያውን በፍጥነት መከታተልና ሁሉም ተማሪዎች በትክክለኛው ገጽ ላይ መሆናቸውን ማረጋገጥ ።

በዚህ ደረጃ የምንረዳው ተማሪዎች ጠቃሚ መረጃዎችን የሚያገኙበት ደረጃ እንደሆነ ፣ ከሚቀርበው ሥራዎችን የሚተገበሩበት ማለትም ከታች ወደ ላይ እና ላይታች ወደ ላይ ማደመጥ የኣዳማጭ እይታን በመረዳት በሰዋስውና በቃላት ትምህርት ላይ ማትኮርና ስለ ሚያዳምጡት ርዕስጉዳይ የሚገምቱበት ደረጃና እንደዚሁም ኣዳዲስ የቃላት ፍቺን የሚረዱበትና የሚተነብዩበት የማዳመጥ ደረጃ መሆኑን ያስረዳል።

2 የማዳመጥ ጊዜ

የማዳመጥ ጊዜ ተማሪዎች የሚያዳምጡበት እና አንድ ተግባር የሚያከናውንበት ነው ። ማዳመጥዋና ሃሳቦችን ማዳመጥ ግምታችን ማድረግ እና ማጠቃለያ የመሳሰሉ ተግባራትን ያሳያሉ። ኣንዳን ተግበራ መመደብ ተማሪዎች እንዲያተኩሩ እና ኣስፈላጊ የቋንቋ ትምህርት ስልቶችን እንዲያብሩ ይረዳል።

ስለ ኣንዳንድ የተለመዱ የማዳመጥ ተግባራት ትንሽ ተጨማሪ መረጃ ስለ ኣጭር ጊዜ ማዳመጥ፡- ዋናውን ሀሳብ ለማግኘት ማዳመጥ ማለት ነው ። ለምሳሌ ገንዘቡ ምን ያህል ነበር? ወይም ጭብጥ ለማግኘት መሞከር ኣለባቸው ። የተለየ መረጃ ለማግኘት ማዳመጥ ማለት ነው ። ለምሳሌ ገንዘብ ምን ያህል ነበር ? ወይም ኣውቶቡሱ ይሄድ ነበር?

ማመዛዘን ተማሪዎች በርዕሱ ሳይ በግልፅጽ ያልተገለፀ መረጃ ስማግኘት የሚያዳምጡበት ቦታ ይህ ነው ። ኣንድንድ ምሳሌዎች ፦ ሁለት ሰዎች ኣንዳቸው ስሌው ምን ይሰማዋል ? ወይም ሰውዬው ቀጥሎ ወዴት ይሄዳል ብለው ያሳካሉ ? በሓሳብ ደረጃ መምህሩ የማዳመጥ ርዕሱን ወይም ምንባቡን ወይም ጊዜ ማስደመጥ ኣለበት። በእያንዳንዱ ጊዜ የተለየ ተግባር ማዘጋጀት ብዙ ባለሞያዎች ሥራዎችን ደረጃ እንዲሰጡ ይጠቅማሉ። ይኸውም ከቀላል ወደ ከባድ ፣ ስምሳሌ በኣንድ ትልቅ ጥያቂ ከመጀመር ፣ ከ3 እስከ 5 ዝርዝር ጥያቄዎችን መጠየቅ በመቀጠል ፣ ከዚያም የማጣቀሻ ጥያቄን ማስከተል ።እንዲሁም ስራስ ኣንድ ተግባር መሰጠት ይገባል ።

ክፍሉን በመቆጣጠር ትኩረት እየሰጡ የተበሳጨ የሚመስል ካለ በክፍል ውስጥ ያለው ኣጠቃሳይ እንቅስቃሴ ምንድነው ? የሚሉትን ሁኔታዎች ሳይ ትኩረት ማድረግ ። እንዲሁም ተማሪዎች የሚዳመጠውን ርዕስ ነገር በጥልቀት የሚያዳምጡበትንና ተፈስጊ መረጃዎችን የሚሰበሰብበት ነው ። በመሆኑም ተማሪዎች የሚደመጠውን ፅሑፍ ወይም ንግግር በተመስጦ በመከታተል እና ማስተወሻ በመያዝ ልምምዱን በተገቢው ሁኔታ እንዲያካሄዱ የሚደረግበት ደረጃ ነው ። በዚህ የማዳመጥ ደረጃ መምህራን ተማሪዎች ስዕሎችን በትክክለኛ ቅደም ተከተላቸው እንዲያሰቀምጡ፣ ያልተሟሉ መረጃዎችንና እቅዶችን እንደያማሉ ፣ኣንድን ፅሑፍ (ንግግር) እያዳምጡ ቀጥሎ ምን ሲመጣ እንደሚችል እንዲገምቱ ፣ የሚነገረውን ነገር በቅደም ተከተል ማስታወሻ ደብተራቸው ሳይ እነድያሰፍሩ ፣እያያዥ ቃሳትን ትኩረት ሰጥተው እንዲያዳምጡ ማድረግ ይገባቸዋል። ምክንያቱም እንደዚህ ያሉ ቃሳት ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ሀሳቦች መካከል ያለውን የእርስበርስ ዝምድና ስለሚገልፁ ነው በድሉ (1998) ።

ከላይ የተዘረዘሩት የማዳመጥ ክህሎት ትምህርት የማስተማር መመሪያዎችና የማዳመጥ ደረጃዎች መልዕኮች መረዳት የሚቻለው የማዳመጥ ክህሎት ትምህርት በክፍል ውስጥ ሲተገበር ምን ምን ሂደቶችንና መመሪያዎችን መከወን እንደሚገባ በዝርዝር የሚያሰረዳና እንዲሁም የማዳመጥ ክንውን ደረጃዎች ምን ምን መተግበር እንደሚገባ እና ኣተገባበርም ግልፅና ቀላል እንዲሆን።ተማሪዎችም የሚደመጠውን ርዕሰ ጉዳይ በጥልቀት ማዳመጥ እንደሚገባቸው ፅሑፉን (ንግግር) እያዳመጡ ቀጥሎ ምን ሲመጣ እንዲሁም የቋንቋን ሥርዓትና ስዋስው ስመጠበቅ ኣያያዥ ቃሳትንና ሥርዓት ነጥቦችን በኣግባቡ ትኩረት ሰጥተው የሚያዳምጡበት መሆኑን ያስገነዝባል ።

3 ድህረ ማዳመጥ ተግባራት

ይህ ክፍል የማዳመጥ ትምህርት የመጨረሻው ደረጃ ነው ። ተማሪዎች ያዳመጡትን ነገር በትክክል መገዘባቸውን የሚገመግምበት ደረጃ ነው።በቅድመ ማዳመጥ ወቅት የተደረጉ ግመታዎችንማረጋገጥን፣የተጠቀሙ ዓሳማዎች ግብ መምታት ኣለመምታታቸውን የሚፈትሽበት ነው። እነዚህም በመማር ማስተማር ሂደት ሳይ የተገኘውን ተሞክሮ ለቀጣዩ ትምህርት ስመጠቀም የምንዘጋጅበት ደረጃ መሆኑ በጣም ጠቃሚ ሂደት ነው ።በተለይም በዚህ ክፍል የተማሪዎችን የመረዳት ክሂል ስማዳበር የሚዘጋጁ ተግባራት ውጤታማ እንዲሆኑ በተግባር መርጠው ወቅት ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። ይህንን እውን ስማድረግ ደግሞ ከተማሪዎች ከእስተ እስት ህወታቸው ጋር የተዛመዱ ተግባራትን ማዘጋጀት አስፈሳጊ ነው። ስስዚህከተማሪዎቹ ዕድሜ፣ችሎታና የክፍል ደረጃ ትኩረት ሲሰጣቸው የሚገባቸው ጉዳዮች ናቸው።

## 2.7 የማዳመጥ ክሂል ማስተማሪያ የትምህርት ይዘት

የማዳመጥ ክሂል ማስተማሪያ የትምህርት ይዘት ፦ የሚሉት ስኣማርኛ ቋንቋ ትምህርት ስማስተማር ሲገለገሉ የሚችሉ ልዩ ልዩ ትምህርታዊ ተግባራትና ክንውኖች ሲሆኑ ፣ እነዚያ ተግባራትና ክንውኖች ሲዘጋጁ ግን የተማሪዎችን ዝንባሌና ፍላጎት

መነሻ ያደረጉ መሆን ኣለባቸው።ምክንያቱምተማሪዎችየሚፈልጉትየራሳቸው ዝንባሌ የሚቀሰቅስ ከሆነ የሚሰጣቸው የመለማመጃ ተግባራትና ክንውናች የማይሰለችና ኣጓጊ ሲሆንላቸው ስለሚችል ተማሪዎችን እንዲነቃቁ ከፍተኛ ድርሻ አለው።

Andersenon and lynch (1991: 20) ኣገላለፅም ለተማሪዎቹ በመፅሐፍ ውስጥ የሚቀርቡ የማዳመጥ ትምህርት ይዘቶች ተማሪውን በተለያዩ የማዳመጥ ተግባራት የሚያለማምዱ መሆን ኣለባቸው ። የማዳመጥ ክሂልን ለማለማመድ ሂደት የትኛው ተግባር ይበልጥ ሲተኮርበት እና ብዙ ልምምድ ሲቀርብበት ያስፈልጋል የሚለው ጥያቄን ግን የተማሪዎችን ፍላጎት ማወቅ ይጠይቃል። በመፅሐፍ ውስጥ የሚዳመጥ ክሂል ለማስተማሪያ የሚለውን የትምህርት ይዘት ስንመርጥ የተማሪዎችን ፍላጎትና የክፍል ደረጃ ማጤን ይኖርበታል በማለት Will Son (2008:29) ይገልፃል።

### 2.7.1 የማዳመጥ ክሂል የትምህርት ይዘት አመራረጥ

የትምህርት ይዘት የሚመረጠው የተማሪዎችን የክፍል ደረጃ መስረት በማድረግ ሲሆን ፣ ይዘቱ ሲመረጥ ግን ለክፍል ደረጃው የሚመጥን መሆን ኣለበት። ስለሆነም በመፅሐፉ ውስጥ ያለው ይዘት ከተማሪው ፍላጎት የመነጨ መሆኑን ማረጋገግ ሌላው ተጨማሪ ሐሳብ ሲሆን፣ በትምህርቱ ከተከቱት ይዘቶች ውስጥ ኣንዱና ዋነኛው የሆነው የማዳመጥ ክሂል በመሆኑ በይዘቱ የተካተቱ መሆኑን ማገንዘብ ነው።

1. ዓላማን መለየት

አንዱ ትምህርት ለማስተማር ሲታሰብ ዓለማ ኣለው። ስለሆነም በማዳመጥ ክሂል ውስጥ መማር የተፈለገው ይዘት ምንድን ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች መነሻ በማድረግ የማዳመጥ ክሂል ይዘት ሲመረጡ ከዓላማዎች ጋር የሚጣጣሙ መሆን ተገቢ ነው። ስለሆነም ተማሪዎች መጀመሪያ ይዘቱ ከትምህርቱ ዓላማ ጋር መጣጣም ኣለበት ። የማዳመጥ ችሎታዎችንና የቋንቋ ኣጠቃቀም ወለና ማቅረብ ኣለብን ።

2. የተማሪዎችን ፍላጎት ያገናዘበ

የተማሪዎችን ፍላጎት ያገናዘበ ይዘት ከሁሉም በላይ በግምት ውስጥ መግባት ያለበት ጉዳይ ነው። ምክንያቱም ኣንድ የትምህርት ይዘት ሲመረጥ መሰረታዊ የሆነው የተማሪዎችን ፍላጎት መነሻ ማድረግ ተገቢ ነው ። ተማሪዎችን መሰረት ያመከለ ይዘት መምረጥ የሚሰጠውን መልመጃ ጥያቄ ወይም ይዘት በኣግባቡ እንዲተገበር ያግዛል ። ስለዚህ የተማሪዎች ፍላጎት ካለ የማይሰራ ነገር የለም ። ሁሉም ነገር ቀላል ይሆናል ማለት ነው። በሌላ ኣገላለፅ ሲዳብር የተፈለገው ትምህርት ወይም ክሂል በኣጭር ግዜ ይከናወናል ወይም ይተገበራል።

Cunning Worth (1995:59) እንደሚያስረዱት ኣንድ የቋንቋ ውስጥ ማስገባት ኣለበት። ይህን ሃሳብ በሌላ መልኩ Linson (2003: 162) እንደሚያስረዱ ኣንዱ የትምህርት ይዘት በመማሪያ መፅሓፍ ውስጥ በሚመረጥበት ወቅት የተማሪዎችን ፍላጎት ያማከሉ፣ተማሪዎች ሲማሩ ዘና የሚሉበትና፣ በራሳ የመተማመን ስሜታቸውን የሚያዳብርና የተግባቦት ክሂላቸውን የሚያሳድግ ሆኖ ሲመረጥ ይገባል።

3.የተማሪዎች የቋንቋ አቅም ያገናዘበ

የተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ለማዳመጥ ክሂል ማስተማሪያነት የሚውለው ቋንቋ ከተማሪዎች ከተማሪዎች ችሎታ ጋር ምንያህል እንደሚጣጣም መመርመር ያስፈልገዋል። ምክንያቱም ተማሪዎችን እንደሚታወቀው ኣማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው በመሆኑ ትንሽ ወጣያሉ ቃለት በሚደመጠው መለመማጃ ተግባራት ቢቀርብላቸው ለለሚደናበሩ የቀረበውን የሚዳመጥ ይዘት በኣግባቡ ለመዳመጥ ይቸገራሉ። ከዚያም ባሻገር ተማሪዎቹ ይዘት የሚገባቸውን ክሂል ሳይጨብጡ ክፍለ ጊዜው ሲባክን ይችላል። ስለዚህ መሆን የሚገባው ለማዳመጥ ክሂል የሚመረጡ ይዘቶች ከቃላት ኣጠቃቀማቸውና ከኣርፍተ ነገር ኣስተካከላቸው ረገድ ከተማሪዎች ችሎታ በላይ ወይም በታች እንዳይሆኑ መጠንቀቅ ያስፈልጋል ።

በዚህ መጠቀም ያለብን ቃላትም ይሁነ ዓ.ነገሮች ወቅት ያለፈባቸው፣ ልዩ ልዩ ሞያን የማይጠይቁ ቢሆኑ የተሻለ ኣቀራረብ ነው። ለምሴሌ ወቅታቸው ያለፈባቸው ቃላት ሲባል የድሮ ከሆኑ ተማሪዎች በኣሁኑ ወቅት ስለማይሰሟቸው ሊደናገሩ ስለሚችሉ ሊዳመጥ የተፈለገው ፍሬ ነገር ይስተጓጎላል ። በተጨማሪም ልዩ ልዩ ሞያን የማይጠይቁ ቃላት ዳግም መደበኛ ቃላት መጠቀም ማለት ነው ። የሞያ ቃላት የሚባሉት በመምህርነት ሞያ የምንጠቀማቸው ቃላት ለሉ። ለምሳሌ፡- ሮስተር የሚለው ለሁሉም ሰው ግልፅ ሲሆን ኣይችልም። ስለዚህ የሙያ ቃላት መጠቀም ለሁሉም ኣድማጭ ሊያግባቡ ስለማይችሉ በሚቀርቡ ይዘቶች ማካተት ተገቢነት የለውም።

በተጨማሪም በቋንቋ መዋቅርም ቢመሆን ከተማሪዎቹ ችሎታ ጋር ሊጣጣም ይገባል። በክሂሉ የሚቀርበው የቋንቋ መዋቅር ከተማሪዎች ችሎታ በታች ወይም በላይ ከሆነ የመማር ሂደቱ ይደናቀፋል ። ስለዚህ የማዳመጥ ክሂል ለማዳበር የይዘቱ ኣወቃቀር ቋንቋውን ከሚማሩት ተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ጋር ምን ያህል እንደሚያያዝ መመራመር ያስፈልጋል ።

4. ኣውድ፡-

ኣንድ የማዳመጥ ይዘት ሲቀርብ የተማሪዎችን ኣውድ መሠረት ያደረገ መሆን ኣለበት ። የተለያዩ የዓውድ ዓይነቶች ኣሉ። ከዚያም የተለያዩ ዓውዶች ውስጥ የትምህርት ዓውድ ሲሆን፣ ማዳመጥ ደግሞ በትምህርት ዓውድ ውስጥ የሚካተት ነው ። በዚህ የመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ለክሂሉ ማዳበር በምንና እንዴት ? ብናስተምር የተሻለ ውጤት ማምጣት ይቻላል የሚለውን ርዕሰ ጉዳይ ግምት ውስጥ ማግባት ካለባቸው ኣንዱ ዓውድ ነው። ዓውድ ማለት በኣንድ የተወሰነ ትምህርት ወይም ርዕሰ ጉዳይ በቦታው ወይም በጊዜ የሚሰጥ ነው። ስለዚህ በማዳመጥ ክሂል የሚቀርቡ የትምህርት ይዘቶች በተማሪዎቹ ዘንድ በቦታው የሚነገርና የሚተገበሩ ነገሮች መቅረብ ለመማር ማስተማር ሂደቱ ስኬታማ ያደርገዋል ።

5. መስህብነት

መስህብነት ሲባል ፡- በማዳመጥ ትምህርት ይዘት ውስጥ ሳቢነት ያላቸው ቃላት መጠቀም መቻል ነው። በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሳቢ የሆኑ ቃላትን ማካተት የሚቀርበውን ይዘት በሚገባ እንዲተገበርና እንደከውን ከማድረጉ ባሻገር የመማር ማስተማር ሂደቱ ኣጓጊና ማራኪ እንዲሆን ያደርገዋል ። በተጨማሪ በማዳማጥ ክሂል ይዘት ውስጥ መስህብነት ሲኖረው የሚችለው በፅሑፍ ይሁን በይዘቱ የገቡ ቃላት ከተማሪዎቹ ዕድሜ ፣ የዕውቀት ደረጃ ባህላቸውና ዘዴያቸውን ግምት ውስጥ ያስገባ ከሆነ ሳቢነት ይኖረዋል ማለት ነው። ከላይ የተገለፁት ነገሮች በይዘቱ ያካተተ ከሆነ መስህብነት ሳይኖረው ኣያቀርም። በዚህ ኣይነት የተዋቀረ ይዘት ደግሞ ምቹ የሆነ የመማር ማስተማር ሂደት ስለሚፈጥር የሚቀርበው ትምህርት ስኬታማ ይሆናል።

6. የክፍል ደረጃ መሰረት ያደረገ (ደረጃ መጣኝነት)

አንድ የትምህርት ይዘት ሲመረጥ ከተማሪዎቹ የክፍል ደረጃ ጋር ተመጣጣኝነት ባለው መልኩ ሲቀርብ ነው ። ምክንያቱም ካለው የክፍል ደረጃ ከፍ ወይም ዝቅ ሳይል ለደረጃ ክፍሉ የሚመጥን ይዘት መርጦ ማቅረቡ የመማር ማስተማር ሂደቱ እንዲሳካ ከማገዙ በተጨማሪ ተማሪዎች እንደኣቅማቸው እንዲሳተፉ እና እንዲነቃቁ ዕድል ይሰጣል።

ምክንያቱም፦ ተማሪዎች የሚሰጣቸው መልመማጃ ጥያቄ ይጨናነቁና በውስጣቸው ያለውን ቀምነገር ለመግለፅ ይቸገራሉ። ከተጨናነቁ ዳግም የመስራት ሞራላቸው ሲነካ ስለሚችል በተቻለ መጠን ከክፍል ደረጃቸው የሚመጣጠን ተግባር ወይም ስራ መስጠት ተገቢ ነው። ተማሪዎች ከኣቅማቸው ጋር የሚመጣጠን ተግባራ ቢሰጡ የበለጠ ለመስራት ይነቃቃሉ። ስለዚህ የሚመጥናቸው መልማመጃ በማቅረብ ተማሪዎች ንቁ ተሳታፊ ማድረግ ተገቢ ነው። ከዚያም ባለፈ ተማሪዎች የሚቀርብላቸው መለማመጃ ይዘት ከኣቅማቸው በታች እንዳይሆን መጠንቀቅ ኣለብን ። ምክንያቱም ከኣቅም በታች ሲሆንም ለመስራት ኣይነሳሱም። የሚቀርብላቸው መልማመጃ ጥያቄ ይንቁታል። ስለዚህ የሚቀርበውን ተግባር ሲያነቃቃ በሚችል መንገድ በማቅረብ ተማሪዎች ሊያዳብሩት የተፈለገው ክሂል እንዲያዳብሩ ማድረጉ ተማራጭ ይኖናል። ስለዚህም የሚቀርብላቸው ተግባራትን በመለማመድ የማዳመጥ ክሂልቸውን ከማዳበር ባሻገር ፣ በክፍል ውስጥ ምቹ የመማር ማስተማር ሂደት እንዲፈጠር ከማድረጉም በተጨማሪ ትምህርቱ ውጤታማ እንዲሆን ያደርጋሉ።

7. የተማሪዎች ዕድሜ

ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚመረጥ የማዳመጥ ይዘት ከተማሪዎቹ ከኣእምሮ ጋር ይሄዳል ወይ? የሚለው ጥያቄ ታሳቢ ማድረግ ተገቢ ነው። ምክንያቱም ተማሪዎቹ የሚቀርበው ይዘት በትክክል ሊሞክሩት የሚችሉትን መሆን ኣለበት። ካልሆነ ግን ከዕድሜያቸው በታች ወይም በላይ መሆን የለበትም።

ስለዚህ የመማር ማስተማር ሂደቱ ግቡ እንዲመታ በተቻለ መጠን ከተማሪዎቹ ዕድሜ ኣቻ ቢሆን ተማሪዎቹ እንደኣቅማቸው ተግባሩን ሲሰሩ ይችላሉ ማለት ነው ። የቀረበው ተግባር ከሰሩ ዳግም የታቀደውን የትምህርት ዕቅድ በመጨረሻ ስኬታማ ሲሆን ይችላል ። ስለዚህ የተማሪዎችን የዕድሜ ሁኔታ ለማዳመጥ የሚቀርበው ይዘቶ ጋር ሲጣጣም ይገበል ።

8. የተማሪዎችን ባህላዊ ዳራ

የተማሪዎችን ባህላዊ ዳራ ግምት ውስጥ ያስገባ ይዘት መምረጥ የሚታሰበውን ትምህርት እንዲፋጠን ያግዛል። ምክንያቱም በትምህርቱ ውስጥ የራሳቸውን ማህበራሰብ ባህል በመሆኑ ፣ በማዳመጥ ይዘት የሚተላለፈው መልእክት በፐፐት እንዲከታተሉት ስለሚያግዝ ክሂሉን በተፋጠነ ጊዜ እንደያቁና እንዲረዱ ከማገዝም በተጨማሪ በባህላቸው ውስጥ ያለውን ጠንካራና ደካማ ጎን ለይተው ጠንካራውን ጎን እንዲያደንቁ ደካማውን ጎን ደግም እንዲያሻሽሉ ያግዛል ።

ስለሆነም የመማር ማስተማር ሂደቱ እንዲቀላጠፍና ስኬታማ ትምህርት ለማካሄድ እንዲቻል ዘንድ የተማሪዎችን ባህላዊ ዳራ ኣውቆ ከባህላቸው ጋር የተጣጣመ ይዘት መምረጥ ይበጃል ። ካልሆነ ግን የትምህርቱን ይዘት ከተማሪዎቹ ባህል ጋር የራቀ ይዘት ለመረዳት ቀላል እንዳልሆነ መገንዘብ ተገቢ ይሆናል ።

9. አዲስ እና አዳምጠውት የማያውቁት፣

የማዳመጥ ክሂል በሚገባ ለማዳበር ኣዲስ ነገር ወይም ለሚተውት የማያቁት ይዘት ማቅረብ መልካም ነው ። ምክንያቱም የማዳመጥ መለማመጃ ይዘቶች ኣዲስ ሲሆኑ ተደማጭነትን ያተርፋሉ ። ስለዚህ ተማሪዎች ለሚቀርብላቸው መለማመጃ

ጥያቄ (ይዘት) እንደኣቅማቸው እንዲሳተፉ ዘንድ ኣዳዲስ ነገሮችን መርጦ በማምጣት የተማሪዎችን የማዳመጥ ፍላጎታቸውን ከፍ እንዲል ማድረግ ይቻላል ። በመሆኑም የተለመደውን ርዕሰ ጉዳይ ከማቅረብ ይልቅ ከላይ እንደተገለፀው ኣዳዲስ ይዘቶችን ለመለማመጃ የሚሆኑ መርጦ በማቅረብ በክፍል ውስጥ የተፋፋመ የማስተማር ሂደት እንዲፈጠር በማድረግ ጥሩ ኣዳማጭ ተማሪዎችን እንዲበራከቱ ኣወንታዊ ተፅእኖ ኣለው ።

## 2.8 የማዳመጥ ተግባራት ቅንብር

ማንኛውም ለትምህርት የሚቀርብ ተግባር ቅንብር በተመለከተ ተከታታይነትን፣ ተለጣጣቂነትን እና ኣንድነትን ጠብቆ ከቀላል ወደ ከባድ ፣ከግልፅ ወደ ውስብስብ እያደገ የሚሄድ በቅደም ተከተል መቅርብ ይኖርበታል ። በዚህም መሠረት ለተማሪው የሚቀርቡ የማዳመጥ ክሂሎትን የሚያዳብሩ ከግዜ ወደ ግዜ የበለጠ እያዳበሩ የሚሄዱ መሆን ኣለባቸው ። Underson and Lynch ማዳመጥ ቀላል ወይም ከባድ ከሚያደርጉት ምክንያቶች መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ ይላሉ ።

1‡ የሚደመጠው የቋንቋ ዓይነት

2‡ የሚደመጥበት ዓላማ ወይም ተግባር

3‡ የሚደመጥበት ኣውድ Underson and Lynch (1988:46)

የማዳመጥ ትምህርት ይዘት ኣቅርቦትን በተመለከተ ተማሪዎች በጣም ከባድና ውስብስብ ወደ ሆነ ልምምድ ከመግባታቸው በፊት ቀላል በሆነ ልምምዶች ጥሩ ውጤት ማምጣትና መበረታታት ይኖርባቸዋል ይላሉ Underson and Lynch (1988:44)። የሚደመጠውን ነገር የግልፅነት ደረጃ የይዘት ዓይነት ይመለከታል። የሚደመጠው የቋንቋ ዓይነት አዳምጦ የመረዳት ሁኔታን ከባድ ወይም ቀላል ያደርጋል።

በማዳመጥ የሚፈፀሙ ተግባርች ባህሪ ማዳመጥን ቀላል ወይም ከባድ ያደርገዋል ። ሲባል፣የተለያዩ ተግባሮች ለተማሪው የተለታዩ የክብደት ደረጃ ያላቸውን ልምዶች ይዘው እንደሚቀርቡ ያሳያል። ለምሳሌ ወድያውኑ ምላሽ የሚሹ ተግባሮች አዳምጦ መመለስ ወይም በቅደም ተከተል ማስቀመጥ ካዳመጡ በሃላ የተፈለገውን መረጃ መርጦ ከሚፈፀሙ ተግባሮች ምሳሌ ዋናውን ሐሳብ ኣሳጥሮ ማቅረብ ቀላል ናቸው። እነዚህ ደግሞ በተራቸው በስሜታዊና በተጨባጭ ኣስተያየቶች መካከል ያለው ልዩነት መገንዘብ ከሚጠይቅ የሚደመጥ ተግባር ይልቅ ቀላል ናቸው ። የሚደመጥበት ኣውድ ሁለት ዋና ዋና ነገሮችን ይይዛል። የሚዳመጠው ጉዳይ መረጃ ብዛትና የሚደመጥ ሂደት የሚፈጀው ጊዜ ናቸው። ማዳመጥን ቀላል ወይ ከባድ ሲያደርጉ የሚችሉ ፣ ምክንያቶችን ስንመረምር በይበልጥ ማተኮር ያለብን በሚደመጡ ጉዳዮች የቋንቋ ኣቅርቦት ባህሪና በማዳመጥ የሚፈፀሙ ተግባራት ባህሪ የክብደት ደረጃ ላይ ነው በማለት ኣክረው ያሳስባሉ(Underson and Lynch፤ 1988)።

ከላይ የማዳመጥ ይዘት ቅንብር በተመለከተ የሙሁራኑ ኣገላለፅ እንደተረዳሁት የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበርእንድቻል ይዘቶቹ ሲዋቀሩ ልዩ ትኩረት ይሻሉ። ይኸውም የይዘቶቹ ኣደረጃጀት ተከታታይነት ፣ ተለጣጣቂነትና ኣንድነትን ጠብቆ መዋቀር ተገቢ ነው ። ከዚያም ይዘቶቹ ከቀላል ወደ ከባድ ፣ ከግልፅ ወደ ውስብስብ እያደጉ መሄድ ለመማር ማስተማር ሂደቱ ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ያደርጋል ። ስለሆነም ከላይ የተዘረዘሩት ኣወቃቀሮች በኣግባቡ ደቅም ተከተላቸውን ጠብቀው ከተዘጋጁ የሚሰጠውን ትምህርት ቀላልና የማይሰለች ይሆናል ። በመሆኑም ተማሪዎች የሚቀርብላቸውን መለማመጃ እየተዝናኑ መሰራት ይችላሉ ።

ስለዚህ የማዳመጥ ይዘት ቅንብር ተስጣጣቂነትና ተከታታይነት በጠበቀ መልኩ የቀረበ ከሆነ የትምህርቱ ይዘት ሳይቆራረጥ ስለሚሰጥ ተማሪዎች የሚቀርብላቸውን ትምህርት በንቃት ይከታተላሉ።

## 2.9 የማዳመጥ ክሂል የማስተማርያ መሣሪያዎች

ከተለመደው የማስተማሪያ መሣሪዎች ወጣ ያሉ ዘመን ያፈራቸው ኣዳዲስ መሣሪያዎችን ተጠቅመን ብናስተምር ክሂሉ ለማዳበር ከፍተኛ ኣስዋፅኦ ይኖራቸዋል ። ኣዳዲስ የማስተማሪያ መሣሪያዎች ከምንጠቀማቸው እንደ ቪድዮ እና ቴፕ ሲሆን ፣ በነዚህ የቴክኖሎጂ ውጤቶች በማስተማር የተለያዩ ለማዳመጥ ክሂል ማዳበር ኣስተዋፅኦ ሲኖራቸው የሚችሉ ይዘቶችን መርጦ በድምፅ ቀድተን ወደ ክፍል ይዘን በመግባት የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ከፍ እንዲል ማድረግ ይቻላል ። ምክንያቱም ትምህርቱን በድምፅ ሲቀርብላቸው ከነበረው ኣቀራረብ ሳቢነት ስላለው የተማሪዎችን ሞራል ያነሳሳል ። ስለሆነም የተማሪዎችን ስሜት የሚማርክ መሆን ዳግሞ የመማር ማስተማር ሂደቱ ምቹ ስለሚሆን ፣ጥሩ ኣድማጭ ተማሪዎችን በክፍሉ ውስጥ እንደበረከቱ ኣስተዋጾ ኣለው። ከዚህ ቀጥሎ በተለያዩ ሙሁራን ስለ ማዳመጥ ክሂል ማስተማሪያ መሣሪያዎችን በተመለከተ ሐሳብ እንዝሯል።

Under Wood (1989) እንደሚገለፁት የማዳመጥ ክሂልን ለማስተማር ከሚረዱ ነገሮች መካከል የተቀረጹ ቀጥተኛ የትምህርት ገለፃዎች ፣ክስተቶች ፣የሥነ-ፅሑፍ ሥራዎች ፣ የምስል ቁሶች ፣ ቃለ ምልልሶች እና የስልክ ላይ ንግግሮች ይጠቀሳሉ። ተማሪዎች በእነዚህ የሚደረጉ ንግግሮችን እንዲያዳምጡና ካዳመጡት ነገር ተነስተው ልዩ ልዩ ትምህርታዊ ተግባራትን እንዲያከናውኑ በማድረግ ክሂሉን ማሰተማር ይቻላል ።እንደነዚህ ያሉ መሳሪያዎች የማዳማጥ ክሂሎችን ለማዳባር ፋይዳው የላቀመሆኑን ሙሁሩ ይገልፃሉ ።

### 2.9.1 በመቅረጸ ድምፅ የተዘጋጁ

የተቀረጹ ማስተማሪያ መሣሪያዎችን ለማዳመጥ ክህሎት ማስተማሪያነት መጠቀም ያለው ጠቀሜታ የጎላ መሆኑ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በመቅረፅ ድምፅ ሆኖ በተንቀሳቃሽ ምስል የተቀረጹ ማስተማሪያ መሳሪያዎችን ለማስተማርያነት መምረጡ ብዙ ጥቅም ኣለው Under Wood (1994:94) Rixon (1990፤11) በማለት ገልፀዋል።

እነዚህ መሣሪያዎች መጠቀም በተመለከተ Under Wood (1994:94) ። እንደሚያብራሩት በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተቀረፁ ድምፃችን ወደ ክፍል በማምጣት ማስተማር እየተለመደ መጥቷል ።ነገር ግን ዋናው ነገር እነዚህን የተቀረፁ ድምፃች መጀመርያውኑ ከመማሪያ መፅሐፉ ጋር ኣብረው የተዘጋጁ መሆን ኣለባቸው ። የተቀረጸው ከሴት በክፍል ውስጥ በሚሰማበት ጊዜ ተማሪዎቹ መማሪያ መፅሓፎቻቸው ላይ ሆነ ተብለው የተዘጋጁ ክንውኖችን እንዲሰሩ የሚያበረታታ መሆን ኣለባቸው ። በክፍል ከቀረበው ማዳመጥን በተቀረጹ ድምፃች የማስተማሪያ መሳሪያ በተጨማሪ እንደ Under Wood (1994:90) ። ኣገላለጽ ከተቻለ ቪድዮንም ለማዳመጥ ማስተማሪያነት መጠቀም ይቻላል። በእንደዚህ ኣይነት መሳሪያ ማዳመጥን ማስተማር በርካታ ጥቅሞች ያሉት ሲሆን ከነዚህ ጥቅሞች መካከል ኣንዱ ተማሪዎች የተናጋሪውን መልእክት እስከ ንበቱ በመከታተል መግለጽ ስለሚችሉ ነው።

### 2.9.2 ቀጥተኛ ቃላዊ ገለፃዎች

እንግዳችን ወደ ክፍል በመጋበዝ ወይም ተናጋሪው ወደ ሚገኝበት ኣከባቢ በመውሰድ እንዲያመጡ የሚደረግበት ሂደት ነው ። የዚህ ዓይነቱ ስልት ለተማሪዎቹ ቀጥተኛውን ቃላዊ ገለጻ ስለሚያቀርበ በርካታ ጥቅሞች ይኖሩታልUnder Wood (1994፤77)። ከእነዚህ ጥቅሞች ዋና ዋናዎቹን ብንመለከት ፦በሚያዳምጡት ጊዜ ልዩ ልዩ የድምጽ ቅላጼዎችንና

የፍጥነት ደረጃዎችን ማሰገንዘብ ፣ከሚቀርቡ ንግግሮች ተማሪዎች የንግግር ኣቅራረቢውን ማንነት፣እድሜ፣ስሜት፣ኣካላዊ ገለፃ ወዘተ በመገንዘብ ሲረዱና ስቀረቡላቸው ጥያቄዎች ምክንያታዊ የሆነ ምላሽ እንዲሰጡ ማስቻል ተናጋሪኣድማጩች ሲያዳምጡት የሚችሉት መጠን ስለሚናገር የተማሪዎችን የማዳመጥ ክህሊ ለማዳበር ተመራጭ መሆኑ ተጠቃሾች ናቸው ።

### 2.9.3 የስነ-ፅሑፋዊ ሥራዎች

የማዳመጥ ክሂል ለማስተማር የሰነ-ፅሑፍ ሥራዎችን መጠቀም የሚካሄደው ትምህርት ቀልጠፋና ምቹ እንዲሆን ያግዛል ። ምክንያቱም የስነ-ፅሑፍ ሥራዎች ከተማሪዎች ማህበራዊ ዳራ፣የሚነሳ ማለት በስነ-ፅሑፍ ሥራ ውስጥ የግሃዱ ዓለም ሰዎች እለታዊ እንቅስቃሴ ሁሉ በውስጡ አካቶ የሚይዝ በመሆኑ ተማሪዎች ዳግም የማህበረሰብ ኣካል በመሆናቸው፣ በማህበረሰባቸው ውስጥ ያለውን ነገር በትምህርት ውስጥ ሲካተት ደግሞ የሚቀርብላቸው መለማመጃ ይዘት በቀላል መንገድ እንዲረዱት ያግዛል ።ስለዚህ የሚሰጣቸውን መለማመጃ ጥያቄ ሳይጨናነቁ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያግዛል። ከዚያም ባሻገር የሚቀርበውን ትምህርት ለተማሪዎቹ ቅርብና ምቹ ከመሆኑ የተነሳ በክፍል ውስጥ ጥሩ የመማር ማስተማር ሂደት እንዲፈጠር ያደርጋል።ከዚያም በተጨማሪ የስነ-ፅሑፍ ሥራዎች የማዳመጥ ክሂል በማስተማሪያ መሣሪያነት መጠቀም በተመለከተ የሙሁራኑ ሓሳብ ይቀጥላል፣ በሥነ ፅሑፋዊ ሥራዎች ቋንቋን ማስተማር ተማሪዎች በእውነተኛ ኣውድ ላይ የተማረተ የተለያዩ ኣገባቦችን እንዲያጠኑ የተለያዩ የቋንቋ ኣጠቃቀሞችን በእውነተኛ ኣውዳቸው እንዲገኙ፣ የኣመለካከት መገለጫን እንዲለኩ እና ተጨባጭ በሆነ የሰዎች ሕይወት ኣውድነት ቋንቋን እንዲማሩ ያስችላል በድሉ(1996:3-4)።

Hammer (2001፤213) እንደገለጹት ለተማሪዎች ኣጫጭር ታሪኮችን (ልበወለዶችን) በክፍል ውስጥ በማቅረብ የማዳመጥ ክህሎታቸውን እንዲያዳብሩ ማድረግ ይቻላል።ምክንያቱም እንዲህ ያሉ ሥነ ፅሑፍ ሥራ ውስጥ ያሉትን የተለያዩ ገጸ ባህሪያትን ይለያሉ፤ የተሰማቸው ኣስታየት ይሰጣሉ፤ እያዳመጡ ማስታወሻ በመያዝ ታሪኩ ወዴት እየሄደና ፍፃሜውን ጭምር ይተነብያሉ።Andersoon Lynch(1991፤18) ይህን ሃሰብ በመደገፍ ማዳመጥ ለማስተማር በሚያመች መልኩ ኣጫጭር ፅሑፎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ ቢያቀርቡ መልካም እንዲሆን ይገልፃሉ።

ከላይ በሙሁራኑ የተሰነዘሩት ሓሳቦች እንደተረዳሁት /እንደተገነዘብኩት ስነ-ፅሑፍ በማዳመጥ ክሂል ለማስተማሪያነት በምንጠቀምበት ጊዜ የትምህርቱን ሂደቶቹ እንደሆን ያግዛል ።ምክንያቱም የስነ-ፅሑፍ ሥራዎች ከተማሪዎች ማህበራዊ ጋር የተያያዘ በመሆኑ፣ሥነ-ፅሑፍ በጋሃዱ ዓለም ሰዎች በእለታዊ እንቅስቃሴ ሁሉ በውስጡ ኣካቶ የሚይዝ የህይወት ገጠመኝ በመሆኑ፣ተማሪዎች ደግሞ የኣንድ ማህበረሰብ ኣካል በመሆናቸው ፣በማህበረሰባቸው ውስጥ ያለውን ነገር በምሰጠው ትምህርት ሥነ-ፅሑፍ ሥራ ሲካተት ደግሞ የሚቀርብላቸውን መለማመጃ ይዘት በቀላል መንገድ እንዲረዱት ያግዛል።ስለዚ የሚሰጠው ትምህርት ለተማሪዎቹ ምቹና ግልፅ ከመሆኑ የተነሳ በክፍል ውስጥ ጥሩ የመማር ማስተማር እንዲፈጠር ኣወንታዊ ተፅኖ ያሳድራል።

### 2.9.4 በስእል ካርታ ስንጠረዥ መጠቀም

ለተማሪዎች የተመረጡት ይዘቶች ርዕስ ነገሮች የዕለት እለት እንቅስቃሴ ልምምድ ጋር የሚሄድ ከሆነ በምሳሌ ኣስደግፎ ማዳመጥን ማስተማር የተሻለ እንደሆነ Under Wood (1994፤104) ገለጻዋል።እንደ Under Wood (1994፤) ኣገላለጽ ተማሪዎችን ማዳመጥ ለማስተማር በመማሪያ መፅሓፎቻቸው ውስጥ በተለያዩ መልኩ ማዳመጥ ለማሳተማር በመማሪያ መፅሓፎቻቸው ውስጥ በተለያዩ መልኩ ማዳመጥን ለማዳበር የሚቀርቡ ይዘቶችወይም ሌሎች ተጨማሪ ይዘቶን በምስል በማደገፍ ትምህርቱን መሰጠት ተማሪዎቹ በጥንቃቄ እንዲከታተሉና የሚጠይቁትም ጥያቄ በኣግባቡ እንዲመልሱ ያደርጋል

።እነዚህ ማዳመጥን ለማስተማር ሲያገለግሉ የሚችሉ ምስሎች ወይም መረጃ መሳሪያዎች ካርታ ፣ ስዕላስእል፤ሰንጠረዥ ወዘተ ፡፡፡ የመሳሰሉ ናቸው።

ስለዚህ የማዳመጥ ክህሎትን እንደያዳብሩ ታስበው የተዘጋጁ ይዘቶች ክንውኖች በዚህ መልክ ማዘጋጀቱና ኣለመዘጋጀቱን መማሪያ መፅሓፎች በሥራ ላይ ከሞሉ በሃላ በዚህ ኣንፃር ቢፈተሽ መልካም ነው ። ከዚህ ጋር ተያያዥነት ባለው መልኩም ማዳመጥን በተቀረጹ ቪድዮ ምስሎች ለማስተማር ቢሞከር ውጤታማ እንደሚሆን ይታመናል (Under Wood፤ 1994:104_108)።

## 2.10 ቀደምት ጥናቶች ቅኝት

ኣጥኚዋ ከምታጠናው ጥናት ጋር ተመሳሳይነት ወይም ተያያዥነት ያላቸው ቀደምት ፅሑፎች እንደሚከተለው ይቀርባሉ። በመጀመሪያ ደረጃ ቃኘው መኮነን (2012 ዓ.ም) በኣዲስ ኣበባ መስተዳድር ትምህርት ቢሮ በ2007 ዓ.ም በታተመው የ7ኛ የ8ኛ ክፍል ኣማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሃፍት ውስጥ የማዳመጥ ትምህርት ይዘት ኣደረጃጀትና ኣቀራረብ ግምገማ በሚል ሲሆን፣ በኮተቤ ዩኒቨርስቲ ለማስተርስ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የተጠና ጥናት ነው። የጥናቱ ዋና ኣላማ መማሪያ መፅሀፍት ውስጥ የቀረቡት የማዳመጥ ይዘቶችን ኣደረጃጀትና ኣቀራረብ ምን እንደሚመስል መገምገም ነው።በፅሑፍ ውስጥ ኣገላለፅ የመፃህፍቱ ኣደረጃጀት ጥሩ እንኳ ብሆኑ ለማዳመጥ ክሂል የተሰጠው ክፍለ ጊዜ ኣንድ ብቻ መሆኑን ተገቢነት የሌለው መሆኑን ለመግለፅ ተሞክሯል።

የቃኘው ጥናት ከኣጥኚዋ የሚያመሳስለው በማዳመጥ ክሂል ዙሪያ መሆኑን ነው። ከዚያም የቃኘው ጥናት በተማሪዎች መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ያሉት የማዳመጥ ክሂል የትምህርት ይዘቶች ከተገቢነት ኣንፃር ስለሚገመገም ተመሳሳይነት ኣላቸው።የቃኘው ጥናት ከኣጥኚዋ የሚለየው በ7ኛ እና በ8ኛ ክፍል የሚጠና ጥናት ሲሆን ፣ የኣጥኚዋ ግን በ10ኛ ክፍል ስለሆነ ይለያያሉ ። ከዚያም የቃኛው ጥናት ሁለት በኣንድ ላይ የሚጠና ጥናት ሲሆን የኣጥኚዋ ግን በኣንድ የክፍል ደረጃ ብቻ መሆኑን ይለያሉ ። ሌላው በሦስተኛ ደረጃ የሚታይ ልዩነት የቃኘው ጥናት በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ የቀረቡት ይዘቶችን ኣደረጃጀት እና ኣቀራረብ እንዲሁም ተከታታይነትና ከተገቢነት ኣንፃር መፃሕፍቶችን እንዴት እንደተዘጋጁና ያላቸውን ኣቀራረብ መገምገም ሲሆን ፣የኣጥኚዋ ግን በመማሪያ መፅሓፉ የቀረቡትን ተግባራትና ክንውኖች ለተማሪዎች ክሂል ለማዳበር ያላቸውን ተገቢነት መፈተሽ ነው። ስለዚህ የሁሉቱ ጥናት ይለያያል።

ሁለተኛው ለልማዝ (2006 ዓ.ም) ኣላማው በ9ኛ ክፍል ኣማርኛ መማሪያ መፅሓፍ ውስጥ የቀረቡት የማዳመጥ ክሂል ይዘቶች እና ክንውኖች የክፍል ውስጥ ኣተባበርና ሲሆን፣ የማዳመጥ ክሂሎት በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ ተገቢውን ትኩረት ሰጥተው መከወን ላይ ችግር እንዳለ ገልፀዋለች።

የለልማዝ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በኣማርኛ መማሪያ መፅሓፍ ውስጥ የቀረቡትን የማዳመጥ ይዘቶችን በክፍል ውስጥ ክንውኖችና በኣተገባበር ላይ ትኩረት ያደረገ ጥናት በመሆኑ፣ ተመሳሳይነት ኣላቸው ። ከዚያም ባሻገር ሁለቱም ጥናቶች በማዳመጥ ክሂል ዙሪያ ጥናት ማድረጋቸው ነው።

የለልማዝና የአጥኚዋ የተለያዩባቸው ነጥቦች የለልማዝ ጥናት በ9ኛ ክፍል ውስጥ እንዴት እንደሚከውኑና እንደሚተገበሩ መፈተሽ ሲሆን ፣የኣጥኚዋ ደግሞ በ10ኛ ክፍል መማሪያ መፅሓፍ ውስጥ የማዳመጥ ክሂል ይዘቶችን ተግባራትና ክንውኖችን ተማሪዎቹ ክሂሉን ከማጎልበት ኣኳያ ያላቸውን ተገቢነት መፈተሽ ስለሆነ ይለያያል። በሶስተኛ ደረጃ የሚታየው ልዩነት

የአልማዝ ጥናት በመማሪያ መፅሐፉ የቀረቡትን ይዘቶችን በክፍል ውስጥ ሲከውኑ ወይም ሲተገበሩ ከመርሃ ትምህርቱ ጋር ተያያዥነቱ ምን ይመስላል የሚለውን ነገር ማየትዋ ከኣጥኚዋ ጋር ይለያያሉ።

ሌላው ሦስተኛው እቴነሽ (1986 ዓ.ም) በ9ኛ ክፍል የኣማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶች ትንተናና ግምገማ በሚል ርዕስ ከኣዲስ ኣበባ ዩኒቨረስቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሑፍ ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የተጠና ጥናት ሲሆን ፣የጥናቱ ዓላማ ደግሞ የማዳመጥ ይዘቶቹ ከተማሪዎቹ ዝንባሌ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ምን እንደሚመስል መፈተሽ ወይም መመርመር ትኩረት ያደረገ ነው። በመርሃ ትምህርቱ የቀረቡት ይዘቶች  የተማሪዎችን ፍላጎት ምን እንደሚመስሰ ለመመርመር ተሞክራል። የእቴነሽ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ነገር ቢኖር ሁለቱም ጥናቶች በማዳመጥ ክሂል ይዘቶች ከተማሪዎችን ዓቅም ማጎልበት ያላቸውን ተገቢነት ዙርያ የሚያውጠነጥኑ መሆናቸውን ነው።

ከዚያም በተጨማሪ የቀረቡት ይዘቶችን ከተማሪዎች ዓቅም ከመገንባት ኣኳያ ምን እንደሚመስሉ መገምገምና መፈተሽ መቻላቸውን።የሚለያዩባቸው ነጥቦች ደግሞ የእቴነሽ ጥናት በ9ኛ ክፍል የሚጠና ጥናት ሲሆን፣የኣጥኚዋ ግን 10ኛ ክፍል መሆኑን ፣ሌላው ልዩነት ደግሞ የእቴነሽ በመርሃ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥ ክሂል የቀረቡ ይዘቶችን  መተንተን እና መገምገም ነው። የኣጥኚዋ ግን በተማሪው መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ያቀረቡትን ተግባራትና ክንውኖች ከተማሪዎች ዓቅም ከመገንባት ያላቸውን ተገቢነት መፈተሽ የሚለው በመሆኑ ልዩነት ኣላቸው ። ከዚያም በተጨማሪ የእቴነሽ ጥናት በመርሃ ትምህርቱ የቀረቡት ይዘቶች ከተማሪዎች ፍላጎት ያላቸውን ተገቢነት መመርመር ሲሆን፣የኣጥኚዋ ግን መማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የቀረቡት የማዳመጥ ተግባራትና ክንውኖች ተማሪዎች ክሂሉን ለማዳበር ያላቸውን ተገቢነት መፈተሻ ነው። ስለዚህ የእቴነሽ የተማሪዎች ፍላጎት ሲሆን የኣጥኚዋ ደግሞ ብቃትን መፈተሽ በመሆኑ ይለያያሉ።

ፍቅሩ ወልደኪዳን (2002 ዓ.ም) በሶዶ ከተማ በሁሉት የመንግስትና የግል 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል የኣማርኛ ቋንቋ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ ኣቀራረብ ንፅፅራዊ ግምገማ በሚል ርዕሰ በኣዲስ ኣበባ ዩኒቨረስቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሑፍ ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የተጠና ጥናት ነው ። የጥናቱ ርዕሰ የ9ኛ ክፍል የግልና የመንግስት ትምህርት ቤቶች የኣማርኛ ቋንቋ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት የመማሪያ ክፍል ውስጥ ኣቀራረብን በተመለከተ በማነፃፀር መገምገም ነው። የግምገማ ውጤት በመንግስትና በግል ትምህርት ቤት ውስጥ የማዳመጥ ክሂል በክፍል ውስጥ ያለው ኣቀራረብ እንዴት እንደሆነ በማነፃፀር ማጥናት ነው።

የፍቅሩ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በማዳመጥ ክሂል ኣካዋወን ዙርያ መሆኑን ነው ።የሚለያየው ደግሞ የፍቅሩ ጥናት በ9ኛ ክፍል ውስጥ ሲሆን የኣጥኚዋ ደግሞ የኣስረኛ ክፍል በመሆኑ ይለያያል። ከዚያም የፍቅሩ ጥናት በግልና መንግስት ትምህርት ቤቶች በማነፃፀር የተጠና ጥናት በመሆኑም ሌላው ልዩነት ነው። ምክንያቱ የኣጥኚዋ በኣንድ የመንግስት ትምህርት ቤት በቀረቡት መልመጃዎች (ይዘቶች) ተግባራትና ክንውኖች ከተማሪዎች ከማዳበር ኣኳያ ያለው ተገቢነት ፍተሻ የሚል ስለሆነ ይለያል። የፍቅሩ ደሞ የክፍል ውስጥ ኣቀራረብ በማነፃፀር መገምገም ነው። ስለዚህ የተማሪዎቹ ዓቅም ምን ደረጃ እንደሆነ መገምገምና የመንግስት ትምህርት ቤትና የግል ትምህርት ለማነፃፀር የቀረበ በመሆኑ ከኣጥኚዋ ይለያል።

የኣጥኚዋ ግን በኣንድ ትምህርት ቤት ውስጥ ሆኖ የቀረበው የማዳመጥ ተግባራትና ክንውኖች የተማሪዎችን  ዓቅም ከመገንባት ያለው ተገቢነት ምን ያክል እንደሆነ መፈተሽ ነው ። በዚህ ጥናት የሚያተኩረው በኣንድ የክፍል ደረጃ ሆኖ በት/ቤቱ ውሰጥ ያሉትን ተማሪዎችን የማዳመጥ ክሂል ብቃትን የሚያፈትሽ በመሆኑ ይለያያል።

## ምዕራፍ ሦስት

## የጥናቱ ንድፍና የአጠናን ዘዴ

### 3.1 የጥናቱንድፍ

ይህ ጥናት ገላጭ የዳሰሳ የምርምር ንድፍን (descriptive survey design) የተከተለ ሲሆን መጠናዊ (quantitative) እና ዓይነታዊ (qualitative) የምርምር ዘዴዎችን በመጠቀም በ2015 ዓ.ም በታተመው የ10ኛክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍና መርሃ ትምህርት ይዘቶች ለይቶ በማውጣት የቀረቡት ተግባራት ክንውኖች የተማሪው ክሂሎችን ከማዳበር ኣኳያ ያላቸውን ብቃት ለማጥናት መተንተን ወይም መፈተሽ ነበር።

Borginagal (1989) ከይዘት ትንተና ይዘት ዓላማዎች አንዱ ስለሚያጠና ጉዳዩ ገላጭ መረጃ መስጠት መሆኑን ይጠቁማል። ይህ ጥናት የተማሪው የማዳመጥ ክሂል ለማዳበር በመማሪያ መፅሐፍና በመርሃ ትምህርቱ የቀረቡት ይዘቶች ወይም ተግባራት በተመለከተ ገላጭ መረጃ በመስጠት ጥናቱን ለማጥናት የሞከራል። ስለዚህ በክሂሉ የቀረቡት ተግባራት ክንውኖች ለይቶ በማውጣት በመጠይቆችን ኣማካይነት ከተሰበሰበው መረጃ መነሻ በማድረግ ተግባራቱን መተንተንና መፈተሽ ሲሆን፣ በዚህ የጥናቱ ንድፍና የኣጠናን ዘዴ ውስጥ የመጠይቆችን ምላሽ ለመተንተን የገላጭ የምርምር ዘዴ ኣሰራርም በጥምር ጥቅም ላይ ማወል ይሆናል። ይህ ተግባራቱም ከመማሪያ መፅሓፉ ይሁን ከመርሃ ትምህርቱ ተለይተው የተመረጡ የማዳመጥ ክሂል ያዳብራሉ ተብለው የተዘጋጁ ተግባራት ላይ ትኩረት በማድረግ ጥናቱን ማካሄድ ይሆናል። በመማሪያ መፅሓፉ የቀረቡት የማዳመጥ ክሂል ተግባራት አምስት ምዕራፎች ለናሙና የተመረጡ ሲሆን፣የእያንዳንዱን ምዕራፍ የማዳመጥ ክሂል ተግባራት ክንውኖችን ለመፈተሽና ለመተንተን ይሞከራል።

### 3.2 የናሙና አመራረጥ ዘዴ

በማይጨው ከተማ ካሉት ሦስት 2ኛ ደረጃ ት/ቤት መካከል የ10ኛ ክፍል አማርኛ መምህራን በእጣ ናሙና አመራረጥ ዘዴ በመጠቀም ወንዶች ሦስት መምህራን ሴቶች ደግሞ ሦስት በአጠቃላይ ስድስት መምህራን እንደናሙና በመውሰድ የፅሑፍ መጠይቅ በማሰራጨት የተገኘው መረጃም በሚቀጥለው ምዕራፍ ተተንትነው በምዕራፍ በቅደም ተከተል ቀርበዋል። በመቀጠል እንደ ናሙና የመረጠቻቸው የ10ኛ ክፍል አማርኛ መምህራን በ2017ዓ.ም በማይጨው ከተማ በጥላሁን ይግዛው 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ፣ በመሰናዶና በቀይሕ ሳዕሪ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በማስተማር ላይ ያሉ መምህራን በመፅሓፉ የተካተቱት የማዳመጥ ክሂል ተግባራት ክንውኖች ጠንካራና ደካማ ጎኖችን ለይተው እንዲያወጡ ተደንል ቀጥሎ ደግሞ አጥኚዋ በመፅሓፉ ላይ የሰነድ ፍተሻ ለማካሄድ ከጊዜ እጥረት አንፃር ሁሉንም ምዕራፎች ማዳረስ ስለሚቻል የማዳመጥ ክሂልን ሊያስማምዱ የሚችሉ ምዕራፎችን በስልታዊ ናሙና አመራረጥ ለይቶ በማውጣት ማለት ምዕራፍ አንድ፣ ምዕራፍ ሦስት ፣ ምዕራፍ አምስት፣ ምዕራፍ ሰባት እና ምዕራፍ ዘጠኝ እንደናሙና በመውሰድ በመማሪያ መፅሐፉ ላይ የሚከተሉውን አጠርያስ የሰነድ ፍተሻ ለማካሄድ ሞክራለች።

### 3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

#### 3.3.1 የሰነድ ፍተሻ

በትምህርት ሚኒሰተር በ2015 ዓ.ም የታተመው የ10ኛ ክፍል የመማሪያ መፅሐፍ ላይ አጥኚዋ በምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳናት ላይ እንደ ዋቢ ከተጠቀመችባቸው በማዳመጥ ክሂል ተግባራትና ክንውኖች ዙሪያ የተለያዩ የምርምር ስራዎች

ከሰሩ ሙሁራን ሃሳብ ጨምቃ በማውጣት የሚከተሉትን የመገምገሚያ ማእቀፎች (Frameworks) አውጥታ በመፅሐፉ ላይ የሰነድ ፍተሻ (document analysis) አካሂዳለች፡፡ የመገምገሚያ ማእቀፎች በዋናነት የተወሰዱት ከሚከተሉት ምንጮች ናቸው፡- Grant 1989)፣ Under Wood (1989)፣ Rost (1990)፣ ማሪው(1989)፣ በድሉ (1998)፣ Anderson and Lynch (1991)፣ Cnning Worth (1995)፣ Linson (2003)። የተጠቀሰው የ10ኛ ክፍል የመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ አስር ምእራፎች ያሉ ሲሆን እያንዳንዱን ማእራፍ የመጀመሪያው ወይም ክፍለ ትምህርት አንድ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት ነው።

### 3.3.2 የፅሑፍ መጠይቅ

በሰነድ ፍተሻ ብቻ የተሰበሰበ መረጃ ተተንትኖ አስተማማኝ መረጃ ለማግኘት ስለማይቻል በፅሁፍ መጠይቅ አማካኝነት ተጨማሪ መረጃዎች በመሰብሰብና በማደራጀት የተገኘውን መረጃ ተንትኖ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ይቻላል። የፅሑፍ መጠይቁ ለተመረጡት ስድስት የ10ኛ ክፍል አማርኛ መምህራን ተሰጥቷል። በፅሑፍ መጠይቁ የተከተቱት ጥያቄዎች በተቻለ መጠን በመማሪያ መፅሓፉ የቀረቡት የማዳመጥ ክሂል ተግባራት ክንውኖች የተማሪዎችን ክሂል ከማዳበር አኳያ ያላቸውን ተገቢነት ምን ይመስላል የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ እንዲቻል ለመምህራን መጠይቆችን ተዘጋጅተው መረጃው መሰብሰብ ተሞክሯል።

### 3.3.3 የቡድን ውይይት መንገድ

አጥኚዋ በቡድን ውይይት መንገድ ከመምህራን የተሰበሰበው መረጃ በዓይነታዊ የምርምር ዘዴ ለመተንተን ሞክራለች። በትምህርት ሚንስቴር በ2015 ዓ.ም የታተመው የ10ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መፅሐፍ ላይ አጥኚዋ ከተለያዩ ትምህርት ቤቶች መምህራን በመጋበዝ በመማሪያ መፅሓፉ የተካተቱት የማዳመጥ ክሂል ተግባራት ክንውኖች ለተተኳሪው የክፍል ደረጃ የማዳመጥ ክሂላቸው ከማዳበር አኳያ ያላቸውን ተገቢነት የሚለውን መነሻ ጥያቄ ለመመለስ ሲባል ለመምህራኑ በቡድን ውይይት መንገድ የመፅሓፉ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ተለይተው ተተንትነው ቀርቧል። ከዚያም በቡድን ውይይት መንገድ ከመምራን የተሰበሰበው ዓይነታዊ መረጃ በዓይነታዊ የምርምር ዘዴ ለመተንተን ሞክራለች።

### 3.4 የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች

ከላይ በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች መረጃው ከተሰበሰበ በኋላ መረጃዎችን በተያለያዩ (በመጠናዊና በዓይነታዊ) መንገዶች ተተንትነው ቀርበዋል። በመጀመሪያ አጥኚዋ በመመሪያ መፅሐፉ ላይ የሰነድ ፍተኛ (document analysis) ያደረገች ሲሆን የተገኘው መረጃም በዓይነታዊ የምርምር ዘዴ ለመተንተን ሞክራለች። ከዚያም በተጨማሪ መጠናዊ መረጃ በፅሑፍ መጠይቅ አማካሪነት ከመምህራን ከተሰበሰቡት ቡኋላ በቁጥራዊ (ስታስቲካዊ) ዘዴዎች ተተንትነዋል። ከዚያም በቡድን ውይይት መንገድ ከተለያዩ ትምህርት ቤቶች በዓይነታዊ የምርምር ዘዴ ለመተንተን ተችላል። በአጠቃላይ የተገኙትን መረጃዎች በመጠናዊና በዓይነታዊ የምርምር ዘዴዎች ተተንትኖ ቀርበዋል።

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ

## መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ሥር አጥኚዎ በመማሪያ መፅሐፉ ላይ ከተለያዩ ሙሁራን የመገምገሚያ ማእቀፎች አውጥታ በመፅሐፉ ላይ አጭር የሰነድ ፍተሻ አካሂዳለች፡፡ ከዛም በተጨማሪ እንደ  ናሙና ከመረጠቻቸው ተማሪዎችና መምህራን የሰበሰበችው መረጃ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ በሴሳ አገላለፅ በማይጨው መሰናድኦ ትምህርት ቤት የሚገኙ ተማሪዎችና መምህራን መረጃ በመሰብሰብ የተገኙት መረጃዎችም የማዳመጥ ክሂል ተግባራትና ክንውኖች ጋር ካለቸው ፋይዳና እሴቶች አንፃር ተተንትነው ቀርቧል፡፡

### 4.1 የመረጃ ትንተና

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በ10ኛ ክፍል  አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍና መርሃ ትምርት ውስጥ የተካተቱ የማዳመጥ ክሂል ተግባራትና ክንውኖች ለተማሪዎች የማዳመጥ ክሂል ለማዳበር ያላቸውን  ተገቢነት መፈተሻ እንደሆነ ቀደም ሲል ተጠቅሷል፡፡ይህን ለማሳካት ጥናቱ ገላጭ (Descriptive) የምርምር ንድፍን የተከተለ ሲሆን መጠናዊ (quantitative)ና ዓይነታዊ (qualitative) የምርምር ስልቶችን በመጠቀም ውጤቱ የሚቀርብ እንደሆነም ቀደም ሲል ተጠቅሷል፡፡በዚህ መሰረትም እንደየ ዓይነታቸው በተሰበሰቡበት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

በመጀመሪያ አጥኚዋ በመማሪያ መፅሐፉ ላይ ከተለያዩ ሙሁራን የመገምገሚያ ማእቀፎች (Frameworks) አውጥታ በመፅሐፉ የሰነድ ፍተሻ (document analysis) አካሂዳለች፡፡ በመቀጠል ደግሞ የማዳመጥ ክሂል ተግባራትና ክንውኖች ጋር በተያያዘ ከአማረኛ መምህራን በተደረገ የቡድን ውይይት መንገድ (Focus Group Discussion)የተገኙ መረጃዎች ተተንትነው ቀርቧል፡፡ በመጨረሻም የማዳመጥ ክሂል ተግባራት ክንውኖች ለተማሪው የማዳመጥ ክሂል ለማዳበር ያላቸውን ተገቢነት በመለኪያ የጽሁፍ መጠይቅ ከመምህራን የተሰበሰቡ መረጃ ተተንትነው ቀርባዋል፡፡ አጥኚዋ በማይጨው ከተማ ከሉት ሦስት 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች መካከል ስድስት የ10ኛ ክፍል አማርኛ መምህራን እንደናሙና በመውሰድ ፅሑፋዊ መጠይቅ በማሰራጨት የተገኘው መረጃም ተተንትነው በቅደም ተከተል ቀርበዋል።

#### 4.1.1 የሰነድ ፍተሻ

በትምህርት ሚኒስተር በ2015 ዓ.ም የታተመው የ10ኛ ክፍል የመማሪያ መፅሐፍ ላይ አጥኚዋ በምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳናት ላይ እንደ ዋቢ ከተጠቀመችባቸው በማዳመፅጥ ክሂል ተግባራትና ክንውኖች ዙሪያ የተለያዩ የምርምር ስራዎች ሙሁራኑ ከሰሩት  ሃሳብ ጨምቃ በማውጣት የሚከተሉትን የመገምገሚያ ማእቀፎች (Frameworks) አውጥታ በመፅሐፉ ላይ የሰነድ ፍተሻ (document analysis) አካሂዳለች፡፡ የመገምገሚያ ማእቀፎች በዋናነት የተወሰዱት ከሚከተሉት ምንጮች ናቸው፡- Grant (1989)፣ Under Wood (1989)፣ Rost (1990)፣ማረው(1989)፣በድሉ (1998)፣ Anderson and Lynch (1991)፣ Cnning Worth (1995)፣ Linson (2003)። የተጠቀሰው የ10ኛ ክፍል የመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ አስር ምእራፎች ያሉ ሲሆን እያንዳንዱን ማእራፍ የመጀመሪያው ወይም ክፍለ ትምህርት አንድ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት ነው። አጥኚዋ ከጊዜ እጥረት አንፃር ሁሉንም አስር ምእራፎች ማዳረስ ስለማትችል ከምእራፍ አንድ በመጀመር አንድ አንድ ምእራፍ በመዝለል ማለትም በጎዶሎ ቁጥሮች የተሰየሙት አምስት ምእራፎች (1፣3፣5፣7፣9) እንደ ናሙና በመውሰድ በመማሪያ መፅሐፉ ላይ የሚከተለውን አጠር ያለ የሰነድ ፍተሻ (document analysis) ለማካሄድ ሞክራለች።

1.በቅድመ ማዳመጥ፣ በማዳመጥ ጊዜ፣ በድህረ ማዳመጥ ደረጃዎች የተጠቃለሉት መመሪያዎችና ይዘቶች ተማሪዎች የሚቀርብላቸውን የሚደመጥ ተግባራትና ክንውኖች ያዳመጡትን የመተርጎም፣የመተንተን፣ የመግለፅና የመወያየት ዕድል ከመስጠት አንፃር ሲታይ (ለተማሪዎች ክሂል ለማዳበር ያላቸዉ ተገቢነት ተተኳሪነት አንፃር ሲታይ )፡፡

ለመጀመር ያክል —ምርትና ምርታማነት“ የተሰኝ አብይ ርእስ የተሰጠው ምእራፍ አንድ ከስሩ ያለው ክፍለ ትምህርት አንድ —ሰነፍ ይከሰራል፤ሰራተኛ ይከበራል“ በሚል ርእሰ ጉዳይ ላይ ያተኮረ የማዳመጥ ክፍል ነው። በቅድመ ማዳመጥ ደረጀ ያሉትን ሁለት ጥያቄዎች ስናይ ተማሪዎች ምንም ዋቢ ነገር ሳይጠቀሙ ከራሳቸው የህይወት ተሞክሮ ተነስተው —የስኬት ሚስጢሮች የምትሏቸው ዘርዝሩ፤ በህይወት ውስጥ ውጤታማ ለመሆን ዕድለኛ ከመሆንና ጠንክሮ ከመስራት ወሳኙ የትኛው ነው፡፡“ (ገፅ፤2) የሚሉት ጥያቄዎች እንዲመልሱ በማድረግ የሚደመጠውን ነገር ከማዳመጣቸው በፊት የመወያየት፣ የመተንተን፣ የመግለፅ ዕድል ይኖራቸዋል ማለት ይቻላል፡፡

ከዛም በመቀጠል ተማሪዎች በአዳመጡት ምንባብ መሠረት በፅሑፍና በቃል እንዲመልሱ በሚያዙት የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች ውስጥ በመመሪያ ሦስት ሥር ካሉ የ8ኛ፤የ9ኛ፤10ኛጥያቄዎች ማለትም —8) የምንባቡ አጠቃላይ መልእክት ምንድ ነው 9) ፀሐፊው የተጠቀማቸው ነገር ግን በዕለት ተዕለት ተግባቦት ብዙም ግልጋሎት ላይ የማይስተዋሉ ቃላትን በመዘርዘር በፍችዎቻቸው ላይ ተወያዩባቸው፡፡ 10) በአካባቢያችሁ ጠንክረው በመስራታቸው ውጤታማ የሆኑ ሰዎችን በምሳሌነት በመጥቀስ የስራ ባህልና ስኬት ያላቸው ግንኙነት አብራሩ፡፡እንደ ናሙና በመውሰድ ተማሪዎቹ በማዳመጥ ጊዜ የተከታተሉትን ቁምነገር ተመልሰው እንዲያስታውሱና መልእክቱን አጠናክረው እንዲይዙት ማድረጋቸው በተጨማሪ የማዳመጥ ክሂላቸውን እንዲገለብት ከፍተኛ አስተዋፅዖ ይኖራቸዋል። ስለዚህ በዚህ ርዕስ ላይ ያሉት የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች ከተገቢነት አኳያ ሲታይ ጥሩ እንደሆነ አጥኚዋ ገልፃለች።

ከዛም በተጨማሪ —ሱስና አደንዛዥ ዕፅ“ በሚል ዓብይ ርእስ የተሰጠው ምዕራፍ ሦስት ሥር —የአደገኛ እፆች መዘዝ“ በሚል ርእሰ ጉዳይ ያጠነጠነ የማዳመጥ ክፍለ ትምህርት አንድ ነው፡፡ ገና ከጅምሩ በቅድመ ማዳመጥ ደረጃ ያሉ ሁለት ጥያቄዎች ስናይ አንደኛው ጥያቄ የሚጠይቀው ከርእሱ ተነስታችሁ ለማዳማጥ የተዘጋጀውን ዕሑፍ ይዘት ገምቱ የሚል ሲሆን ሁለተኛው ጥያቄ ደግሞ ከቅድመ እውቀታችሁ ተነስታችሁ አደገኛ እፆች የሚያስከትልዋቸው ጉዳቶች ዘርዝሩ የሚል ነው። (ገፅ፤35) እነዚህ ጥያቄዎች ስናይ ተማሪዎች ገና የሚያዳምጡትን በግልና በቡዱን በመሆን የመወያየት፣የመተርጎም፣ የመተንተን፣ የመግለፅ ዕድል ስለሚኖራቸው የንግግር ክሂል መለማመድ ዕድል ይኖራቸዋል በማለት አጥኚዋ ታክልበታለች፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ለማዳመጥ ጊዜ በተሰጠ ተግባራዊ መመሪያ አማካኝነት ተማሪዎች ፅሑፉ በሚነበብላቸው ወቅት ማስታወሻ እንዲይዙና ለድህረ ማዳማጥ ጥያቄዎች መልሰ እንዲሰጡ ታዘዋል፡፡ በድህረ ማዳመጥ ከተጠየቁት 5 ጥያቄዎች መካክል ሁለቱም ማለትም 2ኛ እና 5ኛ ጥያቄዎች እንደ ናሙና ብንወስድ፡- —2)ሱሰ የሚያሲዙ መድኃኒቶችና እፆች ከወንጀል መስራት ጋር ያላቸው ግንኙነት አብራሩ።“ እና —5)ያዳመጣችሁት ፅሑፍ ዋና ሀሳብ በአንድ አንቀፅ ፅፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንቡብላቸው።“(ገፅ፤36) ያዳምጡትን በግልና በቡዱን በመሆን የመወያየት፣ የመተርጎም፣ የመተንተን፣ የመግለፅ ዕድል ስለሚኖራቸው የፅሑፍና ንግግር ክሂል በአግረ መንገዳችው የመለማመድ ዕድል ይኖራቸዋል ብላ ታምናለች ።

ከዛም በመቀጠል —እንግዳ ተቀባይነት“ የተሰኝ አብይ ርእስ የተሰጠው ምእራፍ አምስት ሥር ያለው የማዳመጥ ትምህርት ክፍል —ኢትዮጲያዊው እንግዳ ተቀባይነት“ የሚል ንኡስ ርእስ ተሰጥቶታል። በቅድመ ማድመጥ ደረጃ ያሉ ሁለት ጥያቄዎች

ስናይ ተማሪዎችን የሚጠይቀት —ቤታችሁ እንግዳ መጥቶ ምን እንደተደረገለትና ወደ ሌላ አገር ሄደው ያውቁ እንደሆነና በሄዱበት ምን ተደረገላቸው ? (ገፅ፤64)፡፡ እርግጠኛ ሆኖ ለመናገር ተማሪዎች እነዚህ ሁለት ጥያቄዎች ለመመለስ ከዳራዊ እውቀታቸው ውጭ ሌላ ነገር እንደ ዋቢነት መጠቀም አይችሉም። ስለሆነም የሚደመጠውን ነገር ከማዳመጣቸው በፊት የመወያየት፣ የመተንተን፣ የመግለፅ ዕድል ይኖራቸዋል ማለት ይቻላል፡፡ ከዛ በመቀጠል ለማዳመጥ ጊዜ በተሰጠ ተግባራዊ መመሪያ አማካኝነት ተማሪዎች ፅሑፉ በሚነበብላቸው ወቅት ማስታወሻ እንዲይዙና ለድህረ ማዳማጥ ጥያቄዎች መልሰ እንዲሰጡ ታዘዋል፡፡ (ገፅ፤ 64) በድህረ ማዳመጥ ደረጃ ከተጠየቁት ጥያቄዎች መካከል በመመሪያ ሁለት ሥር 4ኛ እና 5ኛ ጥያቄዎች እንደ ናሙና ብንወስድ 4ኛው ጥያቄ —ካዳመጣችሁት ፅሑፍ የተርዳችሁት ዋና ሀሳብ ተናገሩ።“ የሚል ሲሆን 5ኛው ጥያቄ ደግሞ —ከኢትዮጲያዊነት እሴት አንዱ እንግዳ ተቀባይነት ነው ሲባል ምን ማለት እንደሆነ በጥንድ በጥንድ በመሆን ተወያዩ።“ የሚል ነው(ገፅ፤65)፡፡ ስለሆነም እዚህ ጋር ተማሪዎችን በግልና በጥንድ በመሆን የተጠየቁንን ለመመለስ ሲሉ ቋንቋውን በመጠቀመ የመወያየት፣ የመተርጎም፣ የመተንተን፣ የመግለፅ ዕድል እንደሚኖራቸው ያመላክታል።

ከዚህም በተያያዘ —አካቶ ትምህርት“ የተሰኘ አብይ ርእስ የተሰጠው ምእራፍ ሰባት ሥር ያለው የማዳመጥ ትምህርት ክፍል —ፈተና ወደ መልካም እድል መለወጥ“ በሚል ርእሰ ጉዳይ ያጠነጠነ ክፍለ ትምህርት ነው፡፡ በመጀመሪያ በቅድመ ማዳመጥ ደረጃ ያለ አንደኛ ጥያቄ ስናይ —በአካባቢያችሁ እናንተ የምታደንቅዋቸውና ውጤታማ ናቸው የምትልዋቸው አካል ጉዳተኞች ሰዎች ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡የሠርዋቸው ሥራዎቻቸውም በቃለ ተናገሩ“የሚል ነው(ገፅ፤89)። ይህ ጥያቄ በራሱ ተማሪዎችን ገና የሚያዳምጡትን ነገር በግላቸው የመተንተንና የመግለፅ ዕድል ስለሚኖራቸው በእግረ መንገዳችው የፅሑፍና ንግግር ክሂሎች ለመለማመድ ዕድል ይኖራቸዋል ማለት ይቻላል።

ከዛ በመቀጠል ለማዳመጥ ጊዜ በገፅ 90 በተሰጠ ተግባራዊ መመሪያ አማካኝነት ተማሪዎች —ፈተና ወደ መልካም እድል መለወጥ“ በሚል ርእሰ ጉዳይ ያጠነጠነ ፅሑፍ በሚነበብላቸው ወቅት ማስታወሻ እንዲይዙና ለድህረ ማዳማጥ ጥያቄዎች መልሰ እንዲሰጡ ይደረጋሉ፡፡ የሚነበብላቸው ፅሑፍ የአንዲት የትነበርሽ ንጉሴ የተባሉት ለመጥር ኢትዮጰያዊት አይነ ሰውር ህይወት ታሪክ ሲሆን ይህ አካል የጉዳተኝነታቸው ፈተና ግን ወደ ዕድል የቀየሩ ስኬታማ ሰው ናቸው፡፡ ፅሑፉ ከነበበላቸው በኋላ በድህረ ማድመጥ ጥያቄዎች ሥር መመሪያ አንድ ከቀረበው የህይወት ታሪክ መሠረት የቀረበው አንቀፅ ውስጥ ያሉ ክፍት ቦታዎችን እንዲሞሉ ይደረጋል፡፡እዚህ ጋር ተማሪዎችን በጥንድ በጥንድ በመሆን የተጠየቁንን ለመመለስ ሲሉ ቋንቋውን በመጠቀመ እየፃፉ የመወያየት ዕድል ስለሚኖራቸው የፅሑፍና የንግግር ክሂል በእግረ መንገዳችው ለማዳበር ዕድል ይኖራቸዋል ማለት ይቻላል።

ከዚህም በተጨማሪ በድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች በመመሪያ ሁለት 6ኛው ጥያቄ—አጠቃላይ የፅሑፉ መልእክት ምንድን ነው ? ጻፉና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡“ ሲል 7ኛው ጥያቄ ደግሞ —በአካባቢያችሁ ጎበዝ የሚባሉ አካል ጉዳተኛ ካሉ ከወ/ሮ የትነበርሽ ንጉሴ መማነፃፀር ተናገሩ፡፡“የሚል ነው(ገፅ፤90)፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች ስናይ ተማሪዎች ገና ያዳመጡትን የመወያየት ርእሰ ጉዳይ (ከአካባቢያቸው ጋር በማያያዝ)፣የመተርጎም፣የመተንተን፣የመግለፅ ዕድል ስለሚኖራቸው የፅሑፍና ንግግር ክሂሎች መለማመድ ዕድል ይኖራቸዋል ማለት ይቻላል።

በስተመጨረሻ —አንድነትና ብዝሃነት“ የተሰኘ አብይ ርእስ የተሰጠው ምእራፍ ዘጠኝ ሥር ያለው የማዳመጥ ትምህርት ክፍል —አንዱ ለሌላው ምኑ ነው?“ የሚል ስለ ሃገራዊ እሴት የሆነ ርእሰ ጉዳይ ያጠነጠነ ክፍለ ትምህርት ነው፡፡ ሁለቱም የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች በተማሪዎች እይታ አንድነትና ብዝሃነት ማለት ምን ማለት እንደሆነና የሚያውቁትን ለክፍል

ጓደኞቻቸውና መምህራቸው እንዲናገሩ ነው መመሪያው የሚያዘው(ገፅ፣111)፡፡ ከዛም በመቀጠልም ለማዳመጥ ጊዜ በገፅ 122 በተሰጠው ተግባራዊ መመሪያ —እንዱ ስሴሳው ምኑ ነው?" የሚል ፅሁፍ በሚነበብላቸው ወቅት ማስታወሻ እንዲይዙ ያዛል፡፡እነዚህ ተግባራት ለናይ ተማሪዎች የመተርጎም፣የመተንተን፣የመግለፅ ዕድል ስለሚኖራቸው የንግግር ክሂህል መለማመድ ዕድል ይኖራቸዋል ማለት ይቻላል። በተመመሳሳይ መልኩ በገፅ 122 በተሰጡት የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች ተማሪዎች የማዳመጥ ክሂል ብቻ ሳይሆን ሌሎቹ የቋንቋ ክሂሉች በአግረ መንገዳቸው ስማዳበር ይረዳቸዋል ማለት ይቻላል፡፡

1.የማደመጥ የትምህርት ርእሰ ጉዳዮችና ይዘቶች አመራረጥ የተማሪዎችን ፍሉጎት እና አቅም ከማጎልበት አንፃር ተገቢነቱ ሲታይ፡፡

የማደመጥ የትምህርት ይዘቶች አመራረጥ የተማሪዎችን ፍሉጎት እና አቅም ከማገናዘብ አንፃር ሲታይ ደግሞ ቀድም ሲል እንዳየነው በተመረጡት የ5ቱ ምዕራፎች የማዳመጥ ክፋላተ ትምህርት ከተሰጡት ርእሰ ጉዳዮችና ይዘቶች አንፃር እናየለን፡፡ የተማሪዎቹ ዕድሜ አጥኚዋ በፅሑፍ መጠይቅ እንዳረጋገጠችው አብዛኞቹ ማለትም 89 (71.2%) 16 ዓመታቸው የነበሩ ሲሆን የተቀሩት 36(28.8%) ደግሞ 17 ዓመታቸው የነበሩ ሲሆን ርእሰ ጉዳዮቹና ይዘቶቹ ከተማሪዎቹ ፍሉጎት እና አቅም የራቁ አይደሉም ማለት ይቻላል። በሌላ አገላለፅ ራስዋ አጥኚዋ መጽሐፉን በመጠቀም ያስተማረች ሲሆን እንደ ናሙና በተመረጡት የ5ቱ ምዕራፎች (እንደ ናሙና ያልመረጡት ምዕራፎችንም ጭምር ግምት ውስጥ በማስገባት) የማዳመጥ ትምህርት ክፍል ርእሰ ጉዳዮችና ይዘቶች ብዙም ከተማሪዎቹ ፍሉጎት እና አቅም የራቁ አይደሉም በማለት አጥኚዋ ተምንበታለች፡፡ ስለሆነም በ10ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍና መርሃ ትምርህት ከተማሪዎቹ ፍሉጎት እና አቅም የራቁ አይደሉም ማለት ይቻላል፡፡ስለሆነም ከዚህ አንፃር በመፅሐፍ ውስጥ የተካተቱ የማዳመጥ ክሂል ተግባራትና ክንውኖች ከያዙት ቁም ነገር አዘል ርእሰ ጉዳዮችና ይዘቶች አኳያ ሲታይ ስተማሪው ክሂል ስማዳበር ያላቸውን ተገቢነት ከፍ ያለ መሆኑ አጥኚዋ ታምንበታለች፡፡

2.የማዳመጥ የትምህርት ርእሰ ጉዳዮችና ይዘቶች አመራረጥ የተማሪዎችን ፍሉጎት እና አቅም ከማጎልበት አንፃር ተገቢነቱ ሲታይ ።

የማዳመጥ የትምህርት ይዘቶች አመራረጥ የተማሪዎችን ፍሉጎት እና አቅም ከማገናዘብ አንፃር ሲታይ ደግሞ ቀድም ሲል እንዳየነው በተመረጡት የ5ቱ ምዕራፎች የማዳመጥ ክፋላተ ትምህርት ከተሰጡት ርእሰ ጉዳዮችና ይዘቶች አንፃር እናየለን። የተማሪዎቹ ዕድሜ አጥኚዋ በፅሑፍ መጠይቅ እንዳረጋገጠችው አብዛኞቹ ማለትም 89 (71.2%) 16 ዓመታቸው የነበሩ ሲሆን የተቀሩት 36(28.8%) ደግሞ 17 ዓመታቸው የነበሩ ሲሆን ርእሰ ጉዳዮቹና ይዘቶቹ ከተማሪዎቹ ፍሉጎት እና አቅም የራቁ አይደሉም ማለት ይቻላል። በሌላ አገላለፅ ራስዋ አጥኚዋ መጽሐፉን በመጠቀም ያሰተማረች ሲሆን እንደ ናሙና በተመረጡት የ5ቱ ምዕራፎች (እንደ ናሙና ያልመረጡት ምዕራፎችንም ጭምር ግምት ውስጥ በማስገባት ) የማዳመጥ ትምህርት ክፍል ርእስ ጉዳዮችና ይዘቶች ብዙም ከተማሪዎቹ ፍሉጎት እና አቅም የራቁ አይደሉም በማለት አጥኚዋ ተምንበታለች። ምሳሌ፡- በምዕራፍ ሁለት ከገጽ 20 እስከ 21 የቀረቡት የማዳመጥ ክሂል ተግባራት ክንውኖች የይዘት አመራረጥ እንመልከት፡-

የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ፡-

1.መምህራችሁ የሚያቀርቡላችሁን በድምፅ የተቀረፀ የሀድስ አለማዮሁ የህይወት ታሪክ በጥማና አዳምጡ የሚል ጥያቄ የቀረበ ሲሆን ፣ ይህ የሚደመጥ ተግባር አዘገጃጀት የተማሪዎቹን ፍላጎት በሚያነሳሳ መልኩ የቀረበ ነው።ምክንያቱም

የሚደመጠውን ቁምነገር በድምፅ ቀረፃ ወደ ክፍል ይዞ በመግባት የሚከወን ተግባር ተማሪዎቹ ሳይሰለቹ በጥሞና እንዲያዳምጡ ዕድል ይከፍታል። ስለሆነም ተማሪዎች ለሚቀርብላቸው መስማመጃ ተግበራት በአግባቡ እንዲተገብሩ ስለሚያግዝ የማዳመጥ ክሂልን ለማጎልበት ተገቢነት ያለው አቀራረብ መሆኑን ነው። ሌላው በድህረ ማዳመጥ የቀረቡት መለማመጃ ተግባራት እናያለን ፦

1. ባለታሪኩ ማለት (ሀዲስ አለማዮህ ) በህዝብ ዘንድ እንዲታወቁ ካደረጋዋቸው ልበወለዶች መካከል ሁለቱን ጥቀሱ። ይህ የድህረ ማዳመጥ ጥያቄ የተማሪዎቹን የማዳመጥ ክሂል ከማጎልበት አኳያ ተገቢነት ያለው መለማመጃ ጥያቄ ነው ማለት ይቻላል። ምክንያቱ በድምፅ የተቀረፀ የማዳመጥ ቁምነገር የሀዲስ አለማዮህ ህይወት ታሪክ የሚገልፅ ሲሆን፣ ደራሲው ህይወት ታሪክ በሚደመጠው ይዘት ትውልድ ዘመኑ እስከ የመጨረሻው የህይወት ፍፃሜው የሚያትት ሲሆን፣ ተማሪዎቹ ደግሞ ከስመዱት አቀራረብ ወጣ ባለመልኩ በመቅረቡ የተሻሉ አቀራረብ መሆኑ ነው። ከዚያም በተጨማሪ በምዕራፍ 7 በገፅ 89 እና በ90 የቀረቡት የቅድመ ማዳመጥ እና የድህረ ማዳመጥ ተግባራት ክንውኖች ማቅረብ ሲሆን የዚህ ምዕራፍ ርዕስ ፈተና ወደ መልካም እድል መለወጥ የሚል ሲሆን፣ በዚህ ስር የቀረቡት የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ከቀረቡት የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች አንዱ ተራ ቁጥር አንድ እንመልከት።

1.በአካባቢያችሁ እናንተ የምታደንቋቸውንና ውጤታማ ናቸው የምትሏቸውን አካል ጉዳተኞች ለመምህራችሁ ንገሩ። የሠሯቸውንም ሥራዎች በቃል ተናገሩ የሚል ነው። በዚህ መለማመጃ ጥያቄ የተማሪዎችን ፍላጎትና አቅም ከማጎልበት አኳያ ተገቢነት አለው ማለት ይቻላል። ምክንያቱ ከላይ የተገለፀው የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄ ተማሪዎች በራሳቸው ፍቃድ ለጥያቄው መልስ የሚሆነው ማዘጋጀት ይችላል። ማለት ተማሪዎች በአከባቢያቸው አካል ጉዳተኞችን የሚሰሩት ሥራ በቅርበት የሚያዩት ስለሆነ ለዚህ የሚሆን መልስ አያጡም። ስለዚህ በዚህ ምዕራፍና በሌሎም ምዕራፎች የቀረቡት የቀረቡት የሚደመጡ ተግባራት ክንውኖች ተመሳሳይነት ስላላቸው ከተማሪዎቹ ፍላጎት የራቁ አይደሉም። ሌላም የምናየው ከተማሪዎች አቅም ከማጎልበት አኳያ ያላቸውን ተገቢነት ሲሆን በዚህ ምዕራፍ የቀረቡት የማዳመጥ ተግባራት ክንውኖች የተማሪዎችን አቅም ከማጎልበት አንፃር ሲታዩ መልካም ናቸው ለማለት ያስደፍራል። ለምሳሌ በገፅ 90 የቀረቡት የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች፦ 2ጥያቄ፦ ወ/ሮ የትነበርሽ የዓይናቸውን ብርሓን ያጡት በምን ምክንያት ነበር ?

3. ጥያቄ፦ ባለታሪኳ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በምን የትምህርት መስክ ነው?

4. ጥያቄ ፦ በአካባቢያችሁ ጎበዝ የሚባሉ አካል ጉዳተኛ ካሉ ከወ/ሮ የትነበርሽ ጋር በማነፃፀር ተናገሩ የሚሉ ናቸው። ሲናየው አካል ጉዳተኝነት በተለያዩ ምክንያቶች እንደሚከሰቱና ሰዎች ከጉዳት እንዴት መከላከል እንደሚችሉ የሚያሳተምር ፅሑፍ በመሆኑ የተማሪዎችን የማሰብና የማዳመጥ አቅም እንዲያጎለብቱ ከማገዝ አኳያ ተገቢነት ያለው የመለማመጃ ጥያቄ መሆኑን ነው ። ሌላው በ3 የቀረበው የድህረ ማዳመጥ ጥያቄ ነው። በዚህ ጥያቄ ተማሪዎችን አቅም ለማጎልበት ትልቅ ፋይዳ አለው። ምክንያቱም አካል ጉዳተኛ ሁነው ድግሪና ከዚያ በላይ መሆን እንደሚችሉ ፣ የሚያስተምር ርዕስ በመሆኑ ሰዎች በሚያጋጥማቸው ፈተና እንዳይበረከኩና ተስፋ ሳይቆርጡ ያግዛል። ፈተናን እንደመልካም አጋጣሚ ተጠቅመው በርትተው መስራት እንዳለባቸው ነው። ስለዚህ የተማሪዎችን ፍላጎትና አቅም ከፍ እንዲል ዕድል የሚከፍት ነው። ለማዳመጥ ክሂል ማዳበር ትልቅ ድርሻ ስላለው ተገቢነት ያለው ነው በማለት ጥናቱን ያመለክታል።

3.የቀረቡት የማዳመጥ ክሂል ተግባራት ክንዉኖች ከተማሪዉ እዉድ እና መስብነተ በተመለከተ ያለዉ ተገቢነት

የትምህርት ይዘቶች አመራረጥ የተማሪዎችን ትምህርታዊና ማህበራዊ ብሎም ለተማሪዎች ካለው መስህብነት ከተሰጡት ርእሰ ጉዳዮችና ይዘቶች አንፃር እናየለን፡፡ ቀደም ብሎ እንደተገለፀ ራስዋ አጥኚዋ መጽሐፉን በመጠቀም ያስተማረች ሲሆን እንደ ናሙና በተመረጡት የ5ቱ ምዕራፎች(ያልመረጡት ምዕራፎችንም ጭምር ግምት ውስጥ በማስገባት) የማዳመጥ ትምህርት ክፍል ርእሰ ጉዳዮችና ይዘቶች ብዙም ከተማሪዎቹ ትምህርታዊና ማህበራዊ ዓውድ የራቁ እንዳልሆኑ ራስዋ አጥኚዋ ሞያዊ ምስክነት ትሰጣለች፡፡ ከመስህብነት አንፃር ሲታይ ደግሞ ርእሰ ጉዳዮችና ይዘቶች በጣም ወቅታዊና የተማሪዎቹን ቀልብ በቀላሉ ሲስቡ የሚችሉ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ማስረጃ በገፅ 21 የቀረበው የደራሲ ኣዲስ አለማዮህ ፎቶግራፍ በመማሪያ መፅሐፉ ከላይ በተገለፀው ገፅ የቀረበ ሲሆን የቀረበው ስእላዊ መግለጫ የተማሪዎችን ቀልብ ለመያዝ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ኣለው። ስለሆነም አንድ የሚደመጥ ይዘት በስእል ተደግፎ ሲቀርብ የበለጠ የሚደመጠውን ቁምነገር እንዲጨበጥ እገዛ ያደርጋል ። ስለዚህ በገፅ 21 የቀረቡት የሚደመጡ ተግባራት የተማሪዎችን ቀልብ የመያዝ አቅም ስላላቸው ከመስህብነት አንፃር ሲታይ መልካም መሆኑን በጥናቱ ያመለክታል። ስለሆነም ለናሙና የተመረጡት ምዕራፎችና ሳልተመረጡት አምስት ምዕራፎች በተወሰኑት ምዕራፎች ስዕላዊ መግለጫ ተደግፎ መቅረባቸው በተወሰነ መልኩ የተማሪዎችን የማዳመጥ ክሂል ከማጎልበት አኳያ ተገቢነት አላቸው በማለት አጥኚዋ ሀሳብዋ ገልፃለች።

4.የቀረቡት የማዳመጥ ክሂል ተግባራት ክንውኖች የተማሪዎችን የክፍል ደረጃ (ደረጃ መጣኝነት)፣ ዕድሜ፣ ባህላዊ ዳራ አንፃር ተገቢነታቸው በተመለከተ ሲታይ፣

የቀረቡት የማዳመጥ ክሂል ተግባራት ክንውኖች የተማሪዎችን የክፍል ደረጃ (ደረጃ መጣኝነት)፣ዕድሜ፣ባህላዊ ዳራ ተገቢነታቸውን ምን እንደሚመስሉ ሲታይ ከተሰጡት ርእሰ ጉዳዮችና ይዘቶች አንፃር እናየለን፡፡ ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰ ራስዋ አጥኚዋ መጽሐፉን በመጠቀም ያስተማረች ሲሆን እንደ ናሙና በተመረጡት የ5ቱ ምዕራፎች (ያልመረጡት ምዕራፎችንም ጭምር ግምት ውስጥ በማስገባት) የማዳመጥ ትምህርት ክፍል ርእሰ ጉዳዮችና ይዘቶች ከተማሪዎቹ የክፍል ደረጃ (ደረጃ መጣኝነት)፣ዕድሜ፣ ባህላዊ ዳራየራቁ እንዳልሆኑ ጥናቱ ያመለክታል። በሴላ አገላለፅ የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ዘየዎች እና ባህል በአካባቢያቸው፣በመገናኛ ብዙሃን፣በማህበራዊ ሚዲያዎች የመከታተል ዕድል ስለሚኖራቸው የትምህርት ይዘቶች አመራረጥ ከተማሪዎቹ ባህላዊ ዳራ የራቁ እንዳልሆኑ ራስዋ አጥኚዋ ሞያዊ ምስክነት ትሰጣለች፡፡ ስለዚህ በመማሪያ መፅሐፉና መርሃ ትምርህት የተካተቱት ርእሰ ጉዳዮችና ይዘቶች የተማሪዎችን የክፍል ደረጃ (ደረጃ መጣኝነት)፣ ዕድሜ፣ ባህላዊ ዳራ የሚመጥኑ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ማስረጃ ፡- ምሳሌ በገፅ 2 የቀረበው የማዳመጥ ክሂል ተግባራት ክንውኖች ከተማሪዎቹ ባርላዊ ዳራ የራቀ አይደለም ። ምክንያቱም ሰነፍ ይከስራል ሰራተኛ ይከበራል የሚለው የቀረበው የሚደመጥ ክሂል ተማሪዎቹ ካላቸው የትምህርት ደረጃ ሲገነዘቡት የሚችል ጥያቄ ነው። ማለት በርትቶ የሚያጠና አካል ስኬታማ መሆን እንደሚችል እና ሰነፍ ሰው ደግሞ ውጣቱ ኪሳራ መሆኑን ለመረዳት አስቸጋሪ አይሆንም ። ስለዚህ በዚህ ይህ ጥያቄ ለክፍል ደረጃ ተመጥኖ የቀረበ መሆኑን ከዚያም በተጨማሪ የተማሪዎቹ እድሜ፣ ባህላዊ ዳራ የማይቃረን እና ተያያዥ ያለው መሆኑን ጥናቱ ያመለክታል ። ከዚያም በተጨማሪ በገፅ 37 የቀረቡት ጥያቄዎች እንመልከት

1.እቤታችሁ እንግዳ መጥቶ ያውቃል ? ምን እንደተረገለት ? የሚለውን ጥያቄ እያንዳንዱ ተማሪ በቤቱ ውስጥ የሚያየውና የሚተገበረው በመሆኑ ይህ የቅድመ መለማመጃ ጥያቄ ተማሪዎች ከቀድሞ እውቀታቸው በመነሳት ለመግለፅ የሚከብዳቸው ነገር አይሆንም። ምክንያቱም ከባህላዊ ደራቸው የተለየ አይደለም። እንደዚህ አይነት የመለማመጃ ተግባራት ተማሪዎችን እንዲለማመዱ በማድረግ የማዳመጥ ክሂልን ማዳበር ስለሚቻል ተገቢነት ያለው መሆኑን ነው።

5.የማዳመጥ ክሂል ተግባራት ክንውኖች ተማሪዎች አዳዲስና አዳምጠውት የማያውቁት ከመሆናቸው አንፃር ተገቢነታቸውን ሲታዩ ፡፡

ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰ ራስዋ አጥኚዋ መጽሐፉን በመጠቀም ያስተማረች ሲሆን እንደ ናሙና በተመረጡት የ5ቱ ምዕራፎች (ያልመረጡት ምዕራፎችንም ጭምር ግምት ውስጥ በማስገባት) የማዳመጥ ትምህርት ክፍል ርእሰ ጉዳዮችና ይዘቶች አዳዲ ስና ተማሪዎቹ አዳምጠውት የማያውቁት መሆናቸው ራስዋ አጥኚዋ ሞያዊ ምስክነት ትሰጣለች፡፡ ስለሆነም ከዚህ አንፃር በመፅሐፍ ውስጥ የተካተቱ የማዳመጥ ክሂል ተግባራትና ክንውኖች ከያዙት ቁም ነገር አዘል ርእሰ ጉዳዮችና ይዘቶች አኳያ ሲታይ ለተማሪው ክሂል ለማዳበር ያላቸውን ተገቢነት መልካም መሆኑ አጥኚዋ ታምንበታለች፡፡

### 4.1.2 በቡድን ውይይት መንገድ የተገኘ ውጤት

በትምህርት ሚኒስቴር በ2015 ዓ.ም የታተመው የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ላይ የተካተቱት የማዳመጥ ክሂል ተግባራት ክንውኖች የተማሪዎቹን የማዳመጥ ክሂል ከማጎልበት አኳያ ተገቢነታቸውን በተመለከተ ምን እንደሚመስሉና በመፅሐፉ ውስጥ ያሉት የማዳመጥ ክሂል መለማመጃ ጥያቄዎች ጠንካራና ደካማ ጎኖችን ምን እንደሚመስሉ በመምህራን የተገመገመ ቢሆንም አጥኚዋ ለዚህ ጥናት ዓላማ ሲባል ከተለያዩ ትምህርት ቤቶች የተውጣጡ ስድስት መምህራን በመሰብሰብ በሁለት ብድኖች የተከፈሉ ሲሆን፣ ለቡድኖቹ መወያያ ነጥብ ደግሞ በመማሪያ መፅሐፉ የተካተቱት የማዳመጥ ክሂል ማጎልበት ያላቸውን ተገቢነት በተመለከተ እንዲለዩና ከዚያም በተጨማሪ በመፅሓፉ ውስጥ ያሉትን የማዳመጥ ክሂል ተግባራት ክንውኖችን ጠንከራና ደካማ ጎኖችን እንዲገመግሙ ተደርጓል። በመጨረሻ መምህራኑ የመፅሓፉን ጠንካራና ደካማ ጎኖችን እንደሚከተለው በአጭሩ ቀርቧል።

#### 4.1.2.1 የማዳመጥ ትምህርት ክፍሎቹ ጠንካራ ጎኖች

- በአብዛኞቹ ምዕራፎች ለክፍሉ ደረጃው የሚመጥኑ የማዳመጥ ትምህርት ክፍል ይዘቶች መቅረባቸው፤
- በአስሩ ምዕራፎች የተለያዩ የማዳመጥ ዓበይት ክሂልና ንኡስን ክሂልን የተማሪዎችን አጠቃላይ የቋንቋ ክሂል እንዲያዳብሩ በሚረዱ መልክ የቀረቡ መሆናቸው፤
- ከዚያም በተጨማሪ የማዳመጥ ትምህርት ክፍል ይዘቶች የመፃፍ፣የንግግር ክሂሎችን፣ የስዋስው ክሂሎችን እንዲያዳብሩ መሰረት ተደርገው የቀረቡ መሆናቸውን፤
- በአባዛኞቹ ምዕራፎች ውስጥ ላይ ያሉት የማዳመጥ ትምህርት ክፍል ይዘቶች ግልፅ፣ አጭር ኣሳታፊ የሆነ የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን ይዘዋል፤
- ከምዕራፍ አንድ እስከ አስር ያሉት የክፍሉ ደረጃ የሚመጥን ባህልን መሰረት ያደረጉ አስደሳች የማዳመጥ ትምህርት ክፍል ይዘቶች ናቸው፤
- በእያንዳንዱ ምዕራፎች የቀረቡትን መልመጃዎች ገንቢና ተያያዥነት ያላቸው ናቸው፤
- አብዛኛውቹ መልመጃዎች በመምህር መምርያ መልስ መስጠታቸውን ሁሉም አስተማሪ እኩል የሆነ ምላሽ እንዲሰጥ ያደርጋል። በዚያው ልክም ተማሪዎችን ተመጣጣኝ ኣቅም እንዲያዳብሩ የሚያግዝ መሆኑን በጠንካራ ጎን የሚታይ ነው፤
- በማዳመጥ ትምህርት ክፍል ይዘቶችን የቀረቡት የተለያዩ ተግባራት አንድነት (Intergrity) እና ተከታታይነት (Continuty) ያላቸው ናቸው።

### 4.1.2.2 የማዳመጥ ትምህርት ክፍሎቹ ደካማ ጎኖች

- አብዛኞቹ ይዘቶች የእውቀት ክህሎት ላይ የተመሰረቱ በመሆናቸው እንደ ድክመት የተገመገመ ነው።
- በሁሉም ምዕራፎች እንደድክመት የታየው ወይም የተገመገመው በመምህሩ መመርያ ያለው የክፍለ ጊዜ በብዛትና በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ገብተህ የሚሰጠው ክፍለ ጊዜ በፍፁም የማይጣጣሙ ባለመሆናቸው ለቀጣይ ለዚህ መፍትሔ እንዳገኝ በአፅንዖት ሐሳባቸውን ገልፀዋል። ከዚያም ክሂሎች እንደሌላው ይዘቶች ለብቻቸው በቂ ክፍለ ጊዜ ተመድቦላቸው መስጠት እንደሚገባ መምህራኑን የራሳቸው አስተያየት ኣስቀምጠዋል።
- ሰንጠረዥ 4.13 የተጠኚ መምህራን አደረጃጀት መገለጫ

| ተ.ቁ | ትምህርት ቤት | መምህር | የመምህራን ዳራዊ መገለጫ | | | የተመረቀበት የት/ት ዓይነት | የኣገልግሎት ዘመን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ፆታ | እድሜ | የት/ት ደረጃ | | |
| 1 | ማይጨው መሰናዶ | መ/ር 1 | ወ | 45 | 2ኛ ዲግሪ | ኣማርኛ | 21 |
| | | መ/ር 2 | ሴ | 47 | 2ኛ ዲግሪ | ኣማርኛ | 20 |
| 2 | ሽምጣ 2ኛ ደረጃ | መ/ር 3 | ወ | 38 | ዲግሪ | ኣማርኛ | 13 |
| | | መ/ር 4 | ሴ | 27 | ዲግሪ | ኣማርኛ | 5 |
| 3 | ጥላሁን ይግዛው 2ኛ ደረጃ | መ/ር 5 | ወ | 42 | ዲግሪ | ኣማርኛ | 17 |
| | | መ/ር 6 | ሴ | 46 | 2ኛ ዲግሪ | ኣማርኛ | 20 |

በሰንጠረዡ ውስጥ የተገለፀው በናሙና የተመረጡት ስድስት ተጠኚ መምህራን የ10ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን የጥናቱ አካል የሆኑ ናቸው። ከተገለፁት ስድስት መምህራን ሶስት ወንዶች ሲሆኑ ሶስት ደግሞ ሴቶች መሆናቸውን ያስረዳል። ከዚያም በሰንጠረዡ ውስጥ በዕድሜ ፣ በትምህርት ደረጃቸውና በተመረቁበት የትምህርት ዓይነት የአገልግሎት ዘመንም ተገልፃል።

### 4.1.3. የመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ

በማይጨው ከተማ በሦስቱ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ከሚያስተምሩ የ10ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን መካከል በእጣ ናሙና ስድስት መምህራን የተመረጡ ሲሆን፣ ሦስት ሴቶች እና ሦስት ወንዶች እንደናሙና በመውሰድ ፅሑፋዊ መጠይቅ በማሰራጨት የተገኘው መረጃም በቅደም ተከተል ተተንትነው ቀርበዋል።

የፅሑፍ መጠይቁ 25 ጥያቄዎች የያዘሲሆን በቅድመ ማዳመጥ ፣ በማዳመጥ ጊዜ፣ በድህረ ማዳመጥ ደረጃ ያሉ ተግባራትና ክንውኖች ስተማሪው ህሂል ስማዳበር ያለቸው ተገቢነት መፈተሽ በሚችሉ መንገድ ነበር የተቀናጁት። በጽሁፍ መጠይቁ የተጠቃለሉት 25 ጥያቄዎች የመመሪያዎቹ 10 ጥያቄዎች (ከ1 እስከ10) በቅድመ ማዳመጥ ተግባራት ክንውናች ፣ከዚያም በመቀጠል ያሉ 10 ጥያቄዎች (ከ11 እስከ20) በማዳመጥ ጊዜ ተግባራትና ክንውኖች ፣ የመጨረሻውቹ ጥያቄዎች (ከ21 እስከ 25) በድህረ ማዳመጥ ደረጃ ያሉ ተግባራትና ክንውናች ላይ ያተኮሩ ናቸው አባሪ ስሥር ያስ የመምህራን የጽሁፍ መጠይቅ ይመልከቱ።

የጽሁፍ መጠይቁ 25 ጥያቄዎች የያዘ ሲሆን በቅድመ ማዳመጥ፣ በማድመጥ ጊዜ፣ በድህረ ማድመጥ ደረጃ ያሉ ተግባራትና ክንውኖች ስተማሪዉ ክሂል ስማዳበር ያሳቸዉ ተገቢነት መፈተሽበሚያችሉ መንገድ ነበር የተቀናጹት። በጽሁፍ መጠይቁ የተጠቃስሉት 25 ጥያቄዎች የመጀመሪያቹ 10 ጥያቄዎች (ከ1 እስከ 10) በቅድመ ማዳመጥ ተግባራትና ክንውኖች፣ ከዛ በመቀጠል ያሉ 10 ጥያቄዎች (ከ11 እስከ 20) በማድመጥ ጊዜተግባራትና ክንውኖች፣ የመጨረሻዎቹ 5 ጥያቄዎች (ከ21 እስከ 25) በድህረ ማድመጥ ደረጃ ያሉ ተግባራትና ክንውኖች ላይ ያተኮሩ ናቸው (ኣባሪ ስ ሥር ያስ የተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ ይመልከቱ)።

ኣጥኚዋ ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ስመተንተን ቁጥር፣መቶኛ (%)፣ ኣማካይ (mean)፣ መደበኛ ልይይት (standard deviation) የመሳሰሉት የእስታስቲክስ ሒሳብ ዜዴዎች በመጠቀም ሲሆን የተገኘው መጠናዊ (quantitative) መረጃም በሚከተሉት ሰንጠረዦች በቅደም ተከተል ተተንትነው ቀርቧል፡፡

#### 4.1.3.1 በቅድመ ማዳመጥ ያሉ ተግባራትና ክንዉኖች የተማሪዎችን ክሂል ስማዳበር ያሳቸዉ ተገቢነት

በጽሁፍ መጠይቁ ላይ ያሉት የመጀመሪያቹ 10 ጥያቄዎች (ከ1 እስከ 10) በቅድመ ማዳመጥ ተግባራትና ክንውኖች ላይ ያተኮሩ ሲሆኑ(አባሪ ስ ሥር ያስ የመምህራን የጽሁፍ መጠይቅ ይመልከቱ) የተማሪዎችን ክሂል ስማዳበር ያሳቸዉ ተገቢነት በተመስከተሲሆን የተገኘው መረጃም በሚከተሰው ሰንጠረዥ ኣንድ በቁጥር እና በመቶኛ (%) በማካተት ተተንትና የተገኘው ውጤትም በማብራሪያ ታጅቦ ቀርቧል፡፡ ኣጥኚዋ ስተማሪዎቹ ስስ ጽሁፍ መጠይቁ ማብራሪያ በመስጠት ነበር። ብዚህ መሰረት እያንዳንዱን ዓረፍተ ነገር በጥሞና አንብበው ከተጠቀሱት አምስት አማራጮች መካከል አንዱን ብቻ በመምረጥ ከምርጫው ፊት ስፊት ከሚገኘው ሳጥን ውስጥ የ€€√« ምልክት በማድረግ እዲመስሱ ነበር ያደረገችው፡፡ ስእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክል ወይም ስህተት የሚል መልስ እንደስሰውም ኣስረድታስች።

አማራጮቹና የሚወክልዋቸው ቁጥሮች የሚከተሉት ነበሩ፡-

5. በጣም እስማማስሁ
4. እስማማስሁ
3. አልፎ አልፎ እስማማስሁ
2. አልስማማም
1. በጣም አልስማማም

**ሰንጠረዥኣንድ÷በቅድመ ማዳመጥ ያሉ ተግባራትና ክንዉኖች የተማሪዎችንክሂልስማዳበርያሳቸዉተገቢነት**

| ጥያቄዎች | የተገኘው ውጤት በቁጥርና በመቶኛ (%)፤የናሙና መጠን=125 | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 5 | | 4 | | 3 | | 2 | | 1 | |
| ተ.ቁ | ቁጥር | % | ቁጥር | % | ቁጥር | % | ቁጥር | % | ቁጥር | % |
| 1 | 1 | 16.6 | 1 | 16.6 | 2 | 33.3 | 1 | 16.6 | 0 | 0 |
| 2 | 1 | 16.6 | 1 | 16.6 | 2 | 33.3 | 1 | 16.6 | 0 | 0 |
| 3 | 2 | 33 | 1 | 16.6 | 2 | 33.3 | 1 | 16.6 | 0 | 0 |
| 4 | 1 | 16.6 | 2 | 33.3 | 36 | 66.6 | 1 | 16.6 | 0 | 0 |
| 5 | 1 | 16.6 | 1 | 16.6 | 2 | 33.3 | 1 | 16.6 | 1 | 16.6 |

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **6** | 2 | 33.3 | 1 | 16.6 | 2 | 33.3 | 1 | 16.6 | 0 | 0 |
| **7** | 1 | 16.6 | 1 | 16.6 | 3 | 66.3 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| **8** | 2 | 33.3 | 1 | 16.6 | 2 | 33.3 | 1 | 16.6 | 1 | 16.6 |
| **9** | 1 | 16.6 | 2 | 33.3 | 2 | 33.3 | 1 | 16.6 | 0 | 0 |
| **10** | 2 | 33.3 | 1 | 16.6 | 2 | 33.3 | 1 | 16.6 | 0 | 0 |

**(ምንጭ ፥ የአጥኚዋ የዳሰሳ ጥናት ፥ 2017 ዓ.ም)**

ከሰንጠረዥ አንድ ቁጥራዊ መረጃ ማየት እንደተቻለው በጥያቄ ቁጥር አንድ ተማሪዎቹ በመፅሐፉ የተካተቱት የቅድመ ማዳመጥ ተግባራትና ክንውኖች ንቁ አድማጭ እንድሆን ስሜታቸውን በሚያነሳሳ መልኩ ቀርቧል ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄዎች ከስድስት መምህራን ውስጥ 1(16.6%) እና 1(16.6%) በተከታታይ በጣም እስማማሉህና እስማማሉህ ብለው ሲመልሱ 2(33.3%) ደግሞ ለተጠቀሰው ጥያቄ አልፎ አልፎ እስማማሉህ የሚል ምላሽ ሲሰጡ የተቀሩት 1(16.6%) አልስማማም የሚል ምላሽ መምህርትዋ ሰጥትዋል። ከዛም ቀጥሎ በጥያቄ ቁጥር ሁለት ተማሪዎቹ የቅድመ ማዳመጥ ተግባራቱ ቀጥሎ ምን እንደሚመጥን ስምን እንደሚደመጥ በሚጠቁም መልኩ ነው የቀረቡት ።ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ 1(16.6%) እና 1( 16.6%) በተከታታይ በጣም እስማማሉውና እስማማለው ብለው ሲመልሱ 2(33.3%) ደግሞ ለተጠቀሰው ጥያቄ አልፎ አልፎ እስማማሉህ የሚል ምላሽ ሲሰጡ 1(16.6%) ደግሞ አልሰማማም የሚል ምላሽ ተሰጥተዋል። በጥያቄ ቁጥር ሦስት የቅድመ ማዳመጥ ተግባራት ቀጥሎ ለሚደመጠው ንባብ ወይም ንግግር መገመት በሚያስችለቸው መንገድ ነው የቀረቡት ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ 2(33.3%) እና 1(16.6%) በተከታታይ በጣም እስማማለውና እስማማሉህ ብለው ሲመልሱ 2(33.3%) ደግሞ ለተጠቀሰው ጥያቄ አልፎ አልፎ እስማማሉህ የሚል ምላሽ ሲሰጡ የተቀረው 1(16.6%) መምህር ወይም መምህርት ደግሞ ኣልስማማም የሚል ምላሽ ቀርበዋል።

በተመሳሳይ መልኩ በጥያቄ ቁጥር አራት መምህራን በቅድመ ማዳመጥ ተግባራቱ የሚደመጠው የንባብ ወይም የንግግር ርእሰ ጉዳይ የተማሪዎቹን ዳራዊ ዕውቀት በሚቀሰቅስ ነው የቀረቡት ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ 1(16.6%) እና 2(33.3%) በተከታታይ በጣም እስማማሉህና እስማማሉህ ብለው ሲመልሱ 3(66.6%) ደግሞ ለተጠቀሰው ጥያቄ አልፎ አልፎ እስማማሉህ የሚል ምላሽ ሲሰጡ የቀረው 1(16.6%) ደግሞ አልስማማም የሚል ምላሽ ስጥቷል ። ከዚያም ቀጥም ያለው በጥያቄ ቁጥር አምስት መምህራኑ የቅድመ ማዳመጥ ተግባራቱ ቀጥሎ በሚደመጠው ርዕስ ጉዳይ ውስጥ የተካተቱት ቁልፍ ቃላትን ያስተዋውቃሉ የሚለው ለተጠየቁት ጥያቄ 1(16%) እና 1(16.6%) በተከታታይ በጣም እስማማሉህና እስማማሉህ የሚለው ምላሽ ስጡ 2(33.3%) ደግሞ ለተጠቀሰው ጥያቄ አልፎ አልፎ እስማማሉህ የሚል ምላሽ ሲሰጡ ለቀረው 1(16.6%) አልማማም የሚል ምላሽ ተስጥቷል። ከዚያም በጥያቄ ቁጥር ስድስት የቅድመ ማዳመጥ ተግባራቱ የአድማጩን እይታ በመሳብ ስዋስዋዊ ቃላት ያተኩራል ። ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ 2(33.3%) እና 1(16.6%) በተከታታይ በጣም እስማማሉህና እስማማሉህ ብለው ሲመልሱ 2(33.3%) ዳግሞ ለተጠቀሰው ጥያቄ አልፎ አልፎ እስማማሉህ የሚል ምላሽ ሲሰጡ ለቀረው አንድ መምህር ወይም መምህርት 1(16.6%) አልስማማም የሚለው ምላሽ ነበር የሰጠው/ የሰጠችው /። ከዚያም በተጨማሪ በጥያቄ ቁጥር ሰባት መምህራኑ የቅድመ ማዳመጥ ተግባራቱ የአድማጩን የማዳመጥ ክሂል በሚያዳብር መልኩ ነው የተደራጀው። ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ 1(16.6%) እና 1(16.6%) በተከታታይ በጣም እስማማሉህና እስማማሉህ ብለው ሲመልሱ 3 (66.6%) ዳግሞ ለተጠቀሰው ጥያቄ አልፎ አልፎ እስማማሉህ የሚል ምላሽ ነበር የሰጡት ። በጥያቄ ቁጥር ስምንት የቅደመ ማዳመጥ ተግባራቱ ቀጥሎ የሚደመጠውን ንባብ የፅሑፍ ዓይነት በሚጠይቅ መልኩ ነው። የቀረቡት ተብለው ለተጠየቁት 2(33.3%) እና 1(16.6%) በተከታታይ

በጣም እስማማሎህና እስማማሉህ ብለው ሲመልሱ 2(33.3%) ዳግሞ ስተጠቀሰው ጥያቄ አልፎ አልፎ እስማማምሉህ የሚል ምላሽ ሲሰጡ 1(16.6%) ደግሞ አልስማማም የሚል ምላሽ ሲሰጡ የተቀሩት 1 (16.6%) መምህራን ስተጠቀሰው ጥያቄ ኣልስማማም የሚል ምላሽ ነበር የሰጡት። ከዚህ በጥያቄ ቁጥር ዘጠኝ የቅድመ ማዳመጥ ተግባራቱ በትምህርት ይዘቱ ውስጥ ያሉት የአዳዲስ ቃላት ፍችዎችን በሚያሳውቅ መልኩ ነው የቀረቡት ተብለው ስተጠየቁት ጥያቄ 1(—16.6%) እና 2(33.3%) በተከታታይ በጣም እስማማሉህና እስማማሉህ ብለው ሲመልሱ 2(33.3%) ደግሞ ስተጠቀሰው ጥያቄ አልፎ አልፎ እስማማሉህ የሚል ምላሽ ሲሰጡ አልስማማም የሚለው ምላሽ 1(16.6%) ሲሆን ፣በጣም አልስማማም የሚል ምላሽ የሰጠ መምህር ወይም መምህርት ግን የለም። በመጨረሻ በጥያቄ ቁጥር አስር ቀጥሎ የሚነበብላቸው የትምህርት ይዘቶች በሚያዳምጧቸው በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንዲያብራሩ ያዝዛል ተብለው ስተጠየቁት ጥያቄ ስተጠየቁት ጥያቄ ከስድስት መምህራን ውስጥ 2(33.3%) እና 1(16.6%) በተከታታይ በጣም እስማማሉህና እስማማሉህ ብለው ሲመልሱ 2(33.3%) ደግሞ ስተጠቀሰው ጥያቄ አልፎ አልፎ እስማማሉህ የሚል ምላሽ ሲሰጡ አልስማማም የሚለው ምላሽ 1(16.6%) አንድ መምህር/ርት/ የሰጠ ሲሆን ፣ በጣም አልስማማም የሚል ምላሽ ግን የለም።

#### 4.1.3.2 በማዳመጥ ጊዜ ያሉ ተግባራትና ክንዉኖች የተማሪዎችን ክሂል ስማዳበር ያላቸዉ ተገቢነት

በጽሁፍ መጠይቁ ከመጀመሪያቹ 10 ጥያቄዎች በመቀጠል ያሉ 10 ጥያቄዎች (ከ11 እስከ 20) በማዳመጥ ጊዜተግባራትና ክንውናች ላይ ያተኮሩ ሲሆኑ (አባሪ ስ ሥር ያስ የመምህራን የጽሁፍ መጠይቅ ይመልከቱ) የተማሪዎችን ክሂል ስማዳበር ያላቸዉ ተገቢነት በተመስከተሲሆን የተገኘው መረጃም በሚከተሰው ሰንጠረዥ ሁስት በቁጥር እና በመቶኛ (%) በማካተት ተተንትኖ የተገኘው ውጤትም በማብራሪያ ታጅቦ ቀርቧል።

**ሰንጠረዥ ሁስት በማዳመጥ ጊዜ ያሉ ተግባራትና ክንዉኖች የተማሪዎችን ክሂል ስማዳበር ያላቸዉ ተገቢነት**

| ጥያቄዎች | የተገኘው ውጤት በቁጥርና በመቶኛ (%)፤ የናሙና መጠን=125 | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 5 | | 4 | | 3 | | 2 | | 1 | |
| ተ.ቁ | ቁጥር | % | ቁጥር | % | ቁጥር | % | ቁጥር | % | ቁጥር | % |
| 11 | 1 | 16.6 | 3 | 66.6 | 2 | 33.3 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 12 | 0 | 0 | 1 | 16.6 | 3 | 66.6 | 1 | 16.6 | 1 | 16.6 |
| 13 | 1 | 16.6 | 1 | 16.6 | 3 | 66.6 | 1 | 16.6 | 0 | 0 |
| 14 | 1 | 16.6 | 2 | 33.3 | 2 | 33.3 | 1 | 16.6 | 0 | 0 |
| 15 | 1 | 16.6 | 1 | 16.6 | 3 | 66.6 | 0 | 0 | 1 | 16.6 |
| 16 | 2 | 33 | 1 | 16.6 | 2 | 33.3 | 1 | 16.6 | 0 | 0 |
| 17 | 1 | 16.6 | 2 | 33.3 | 2 | 33.3 | 1 | 16.6 | 0 | 0 |
| 18 | 1 | 16.6 | 2 | 33.3 | 3 | 66.6 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 19 | 0 | 0 | 1 | 16.6 | 3 | 66.6 | 1 | 16.6 | 1 | 16.6 |
| 20 | 1 | 16.6 | 1 | 16.6 | 2 | 33.3 | 2 | 33.3 | 0 | 0 |

*(ምንጭ ፦ የአጥኚዋ የዳሰሳ ጥናት ፦ 2017 ዓ.ም)*

ከላይ ሰንጠረዥ ሁለት ቁጥራዊ መረጃ መረዳት እንደሚቻለው በጥያቄ ቁጥር አስራ አንድ  በማዳመጥ ጊዜ የቀረቡት የሚደመጡ ተግባራትና ክንውኖች ከቅድመ ማዳመጥ ጋር ተያያዥነት አላቸው ተብለው ሲጠየቁ 1(16.6%) እና 3(66.6%) በተከታታይ በጣም እስማማሉህና እስማማሉህ ብለው ሲመልሱ 2(33.3%) ዳግሞ አልፎ አልፎ እስማማሉህ የሚል ምላሽ ሲሰጡ የተቀሩት በጣም አልስማማምና አልስማማም የሚል ምላሽ ግን የለም። ቀጥሎ በጥያቄ ቁጥር ዓስራ ሁለት በመፅሐፉ የተካተቱት የማዳመጥ ጊዜ ተግባራትና ክንውኖችን ስመምህሩ /ዋ/ የመጣቀሻ ጥያቄዎች እንዲጠይቅ ወይም እንድትጠይቅ ያስችለዋል /ያስችላታል/ ተብለው ስተጠየቁት ጥያቄ 1(16.6%) እና 3(66.6%) በተከታታይ እስማማሉሁና አልፎ አልፎ እስማማሉህ የሚል መልስ ሲሰጡ 1(16.6%) እና 1(16.6%) በተከታታይ በጣም አልስማማምና አልስማማም የሚል ምላሽ ነበር የሰጡት ። በተመሳሳይ መልኩ በጥያቄ ቁጥር አስራ ሦስት በማዳመጥ ጊዜ ስሚቀርቡ ተግባራት ክንውኖች የሚጠናከሩ ስዕላዊ መግለጫዎች ይቀርባሉ። ተብለው ስተጠየቁት ጥያቄ 1(16.6%) እና 1(16.6%) በተከታታይ በጣም እስማማሉህና እስማማሉህ ብለው መልስ ሲሰጡ 3(66.6%) ደግሞ አልፎ አልፎ እስማማሉህ የሚለው  መልስ ሲሰጡ የተቀሩት 1(16.6%) አልስማማም የሚል መልስ ሲሰጥ /ሲትሰጥ/ በጣም አልስማማም የሚል ምላሽ ግን አልቀረበም።

በጥያቄ ቁጥር አስራ አራት ደግሞ በማዳመጥ ጊዜ የሚቀርቡ ተግባራት ተማሪዎችን በሚገባ ያስማምዳሉ ተብለው ስተጠየቁት ጥያቄ 1(16.6%) እና 2(33.3%) በተከታታይ በጣም እስማማሉና እስማማሉህ የሚል ምላሽ የሰጡ ሲሆን ፣ 2(33.3%) ደግሞ አልፎ አልፎ እስማማሉህ የሚል ምላሽ ሲሰጡ 1( 16.6%) አልስማማም የሚል መልስ የተሰጠ ሲሆን በጣም አልስማማም የሚል መልስ ግን አልተሰጠም። ቀጥሎ በጥያቄ ቁጥር አስራ አምስት በቅድመ ማዳመጥ ጊዜ የሚቀርቡ ተግባራትና ክንውኖች የተማሪዎችን ሞራል ያነሳሳሉ ተብለው የተጠየቁ ሲሆን ፣ 3(66.6%) አልፎ አልፎ እስማማሉህ የሚል መልስ ቀርቧል። ከዚያም በመቀጠል በጥያቄ ቁጥር አስራ ስድስት በማዳመጥ ጊዜ የሚቀርቡ መስማመጃ ጥያቄዎች ተማሪዎች አያያዥ ቃላትን ተጠቃሚውን እንዲሰሩ ያግዛሉ። ተብለው ስተጠየቁት ጥያቄ 2(33.3%) እና 1(16.6%) በተከታታይ በጣም እስማማሉህና እስማማሉህ የሚል መልስ የቀረቡ ሲሆን ፣ 3(66.6%) ደግሞ አልፎ አልፎ እስማማሉህ የሚለው ምላሽ ቀርቧል። 1(16.6%) አልስማማም የሚለው ምላሽ የቀረበ ሲሆን፣ በጣም አልስማማም የሚል ግን የለም። ሌላው በጥያቄ ቁጥር አስራ ሰባት በማዳመጥ ጊዜ የሚቀርቡ የመስማመጃ ተግባራት ክንውኖች የተማሪዎችን ቀልብ በመያዝ የማዳመጥ ክሂልን ስማጎልበት ይችላሉ ተብለው ሲጠየቁ የሰጡት ምላሽ 1 (16.6%) እና 2(33.3%) በተከታታይ በጣም እስማማሉህ እና እስማማሉህ የሚል መልስ የቀረበ ሲሆን፣2(33.3%) ደግሞ አልፎ አልፎ እስማማሉህ የሚለል ምላሽ ሰጥተዋል ። 1(16.6%) አልስማማም የሚለው መልስ ቀርበዋል። በጣም አልስማማም የሚል ምላሽ ግን አልቀረበም። በጥያቄ ቁጥር አስራ ስምንት የማዳመጥ ንባባን ወይም ንግግሩን በተገቢ መንገድ ከዳመጡ በኋላ የቋንቋውን ስዋስዋዊ ስርዓት ተከትለው የመስማመጀዎች ከቀላል ወደ ከባድ ነው የቀረቡት ተብለው የተጠየቁ ሲሆን፣ 1(16.6%) እና 2 (33.3%) በተከታታይ በጣም እስማማሉህና እስማማሉህ የሚለው ምላሽ ቀርቧዋል። 3(66.6%) ደግሞ አልፎ አልፎ እስማማሉህ የሚለው ምላሽ ሲሰጥ ቀጥሎ በጣም አልስማማምና አልስማማም የሚል መልስ ግን አልተሰጠም።

ቀጥሎ በጥያቄ ቁጥር አስራዘጠኝ በማዳመጥ ጊዜ የማዳመጥ ንባቡን ወይም ንግግሩን በተገቢ መንገድ  ካዳመጡት በኋላ የቋንቋውን ስዋስዋዊ ስርዓት ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ ያስችላል ተብለው ስተጠየቁት ጥያቄ በጣም እስማማሉህ የሚል መልስ አልተሰጠም። 1(16.6%) እና 3(66.6%) በተከታታይ እስማማሉህና አልፎ አልፎ እስማማሉህ የሚል ምላሽ የተሰጡ፣ የተቀሩት 1(16.6%)እና 1(16.6%) ደግሞ በጣም አልስማማምና አልስማማም የሚል ምላሽ ተሰጥቷል።

በመጠረሻ በጥያቄ ቁጥር ሃያ 1( 16.6%) እና 1(16.6%) በተከታታይ በጣም እስማማሉህና እስማማሉህ የሚል ምላሽ ሲሰጡ 2(33.3%) ደግሞ አልፎ አልፎ እስማማሉህ የሚል መልስ ተሰጥቷል። ቀጥሉ 2(33.3%) ደግሞ አልስማማም የሚል ምላሽ የተሰጠ ሲሆን ፣ በጣም አልስማማም የሚል ምላሽ ግን የለም።

**4.1.3.3 በድህረ ማዳመጥ ደረጃ ያሉ ተግባራትና ክንዉኖች የተማሪዎችን ክሂል ለማዳበር ያላቸዉ ተገቢነት**

በጽሁፍ መጠይቁ የመጨረሻዎቹ 5 ጥያቄዎች (ከ21 እስከ 25) በድህረ ማዳመጥ ደረጃ ያሉ ተግባራትና ክንውኖች ላይ ያተኮሩ ሲሆኑ የተማሪዎችን ክሂል ለማዳበር ያላቸዉ ተገቢነት በተመለከተሲሆን(አባሪ ለ ሥር ያለ የመምህራን የጽሁፍ መጠይቅ ይመልከቱ) የተገኘው መረጃም በሚከተለው ሰንጠረዥ ሦስት በቁጥር እና በመቶኛ (%) በማካተት ተተንትኖ የተገኘው ውጤትም በማብራሪያ ታጅቦ ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥሦስት፥በድህረ ማዳመጥ ያሉ ተግባራትና ክንዉኖች የተማሪዎችን ክሂል ለማዳበር ያላቸዉ ተገቢነት**

| ጥያቄዎች | የተገኘው ውጤት በቁጥርና በመቶኛ (%)፤ የናሙና መጠን=125 | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 5 | | 4 | | 3 | | 2 | | 1 | |
| ተ.ቁ | ቁጥር | % | ቁጥር | % | ቁጥር | % | ቁጥር | % | ቁጥር | % |
| 21 | 1 | 16.6 | 2 | 33.3 | 3 | 66.6 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 22 | 1 | 16.6 | 2 | 33.3 | 2 | 33.3 | 1 | 16.6 | 0 | 0 |
| 23 | 1 | 16.6 | 1 | 16.6 | 2 | 66.6 | 1 | 16.6 | 0 | 0 |
| 24 | 2 | 33.3 | 1 | 16.6 | 3 | 66.6 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 25 | 1 | 16.6 | 1 | 16.6 | 3 | 66.6 | 1 | 16.6 | 0 | 0 |

(ምንጭ፥ የአጥኚዋ የዳሰሳ ጥናት፥ 2017 ዓ.ም)

ከላይ ከሰንጠረዥ ሦስት ቁጥራዊ መረጃ መረዳት እንደሚቻለው በጥያቄ ቁጥር ሃያአንድ በድህረ ማዳመጥ ደረጃ ያሉ ጥያቄዎች ተማሪዎች ያደመጡትን ንባብ ወይም ንግግር በትክክል መገንዘባቸውን እንሰዲገመግሙ የሚያችሉ ናቸው ተብለው ስተጠየቁት ጥያቄ 1(16.6%) እና 2(33.3%) በተከታታይ በጣም እስማማለሁና እስማማለሁ ብለው ሲመልሱ 3(66.6%) ደግሞ ለተጠቀሰው ጥያቄ አልፎ አልፎ እስማማሉህ የሚል ምላሽ ነበር የሰጡት።

ከዚያም በተጨማሪ በጥያቄቁጥር ሃያ ሁለትበድህረ ማዳመጥ ደረጃ ያሉ ተግባራትና ክንውኖች በቅድመ ማዳመጥ ወቅት ያደረጓቸው ግምቶች ያረጋግጡሏችዋል ተብለው ስተጠየቁት ጥያቄ 1(16.%) እና 2(33.3%) በተከታታይ በጣም እስማማለሁና እስማማለሁ ብለው ሲመልሱ 2(33.3%) ደግሞ አልፎ አልፎ እስማማሉህ የሚል ምላሽ ሲሰጡ የተቀሩት 1(16.6%) አንድ መምህርት ወይም መምህር ለተጠቀሰው ጥያቄ አልስማማም የሚል ምላሽ ነበር የሰጡት። በጣም አልስማማም የሚል ምላሽ የለም።

በጥያቄ ቁጥርሃያ ሦስት መምህራኑ በድህረ ማዳመጥ ደረጃ ያሉ ተግባራትና ክንውኖች ኣዳምጦ የመረዳት ክሂሌን ከፍ በሚያደርጉ መልኩ ነው የተቀናጁት ተብለው ስተጠየቁት ጥያቄ 1(16.6%) እና 1(16.6%) በተከታታይ በጣም እስማማለሁና እስማማለሁ ብለው ሲመልሱ 3(66.6) ደግሞ ስተጠየቁት ጥያቄ አልፎ አልፎ እስማማሉህ የሚል ምላሽ ሲሰጡ የተቀሩት አንድ መምህር ወይም መምህርት 1 (16.6%) ለተጠቀሰው ጥያቄ አልስማማም የሚል ምላሽ ነበር

የሰጡት በጣም አልስማማም የሚል ምላሽ የለም ። ከዚያ በጥያቄ ቁጥር ሃያ አራት በድህረ ማድመጥ ደረጃ ያሉ ጥያቄዎች ያዳመጡትን ንባብ ወይም ንግግር ርእሰ ጉዳይ ከእለታዊ ህይወታቸውን ጋር እንዲዛመድ ያደርጋቸዋል። ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ 2(33.3%) እና 1 (16.6%) በተከታታይ በጣም እስማማለሁና እስማማለሁ የሚል ምላሽ የሰጡ ሲሆን 3(66.6%) ደግሞ ለተጠቀሰው ጥያቄ አልፎ አልፎ እስማማሉህ የሚል ምላሽ ነበር የሰጡት፡፡

በመጨረሻ በጥያቄ ቁጥር ሃያ አምስት በድህረ ማዳመጥ ደረጃ ያሉ ተግባራትና ክንውኖች የትምህርት ይዘቱን ዓላማዎች መምታታቸው ኣለመምታታቸው ያረጋግጡላቸዋል ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ1 (16.6%) እና 1(16.6%) በተከታታይ በጣም እስማማለሁና እስማማለሁ የሚል ምላሽ ሲሰጡ 3 (66.6%) አልፎ አልፎ እስማማሉህ የሚል ምላሽ ነበር የሰጡት። 1(16.6) ደግሞ አልስማማም የሚል ምላሽ ተሰጥቷል።

**4.1.3.4 ከመምህራኑ ፅሑፋዊ መጠይቅ የተገኘው አጠቃላይ ቁጥራዊ ውጤት**

በዚህ ንኡስ ርእስ አጥኚዋ ከመምህራኑ በጽሁፍ መጠይቅ አማካኝነት የተገኘ አጠቃለይ የመረጃ ወጤትና ማብራሪያ ስመስጠት አማካይ (mean) እና መደበኛ ልይይት (standard deviation) በጣም ጠቃሚ የሆኑትን የእስታስቲክስ (ሒሳብ) ዜዴዎች በመጠቀም ሲሆን የተገኘው መጠናዊመ (quantitative) መረጃም በሚከተለው ሰንጠረዥ ተተንትነው ቀርቧል፡፡ በጽሁፍ መጠይቁ የተሰጡት አማራጮችና የሚወክልዋቸው ቁጥሮች የሚከተሉት ነበሩ፡-5-በጣም እስማማለሁ፣4-እስማማለሁ፣3-አልገ አልፎ እስማማሉህ ፣ 2-አልስማማም፣1-በጣም አልስማማም፡፡

**ሰንጠረዥአራት:- ከመምህራን መጠይቅ የተገኘው አጠቃላይ ቁጥራዊ (ስታስቲካላዊ) ውጤት**

አጥኚዋ መምህራኑ ለእያንዳዱን በማዳመጥ ደረጃ ሥር ላሉት ዓረፍተ ነገሮች ከአምስቱም አማራጮች (5-በጣም እስማማለሁ፣ 4-እስማማለሁ ፣ 3-አልፎ አልፎ እስማማሉህ ፣ 2-አልስማማም፣ 1-በጣም አልስማማም) መካከል አንዱን ብቻ በመምረጥ ከምርጫው ፊት ለፊት ከሚገኘው ሳጥን ውስጥ የ€€√« ምልክት በማድረግ እዲመለሱ ነበር ያደረገችው፡፡ ከላይ ከሰንጠረዥ አራትቁጥራዊመረጃ መረዳት እንደሚቻለው የመምህራኑ ምላሾች በሂሳባዊ (ስታስቲካላዊ) ቋንቋ ሲገለፅ አብዛኛው መምህር 3ኛው አማራጭ (አልፎ አልፎ እስማማሉህ) የሚል ምላሽ ነው የሰጠው፡፡

ስለሆነም ከላይ ከሰንጠረዥ አራትለ3ኛውአማራጭ (3- አልፎ አልፎ እስማማሉህ )ብለው የመለሱ መምህራን አማካይ ብዛት ለናይ በሦስቱም በቅድመ ማዳመጥ፣በማዳመጥ ግዜ፣ በድህረ ማዳመጥ ደረጃዎች በተከታታይ 60፣65፣62 የሆኑት ከፍተኛ አማካይ ውጤቶች (ጥቅል አማካይ 61.8) ተመዝግበዋል፡፡ ይህ ማለት ከጠቅላላ 6 መምህራን አብዛሃዎቹ ማለትም በአማርኛ መመሪያ መፅሃፉ ውስጥ የተጠቃለሉት የማዳመጥ ክሂል ተግባራትና ክንውኖች የተማሪዎችን ክሂል ለማዳበር ያላቸዉ ተገቢነት በተመለከተ ተግባራቱ ሲከወኑ አብዛኛቹ ከተማሪዎቹ ዕድሜ፣ የክፍል ደረጃ ባህላዊ ዳራ የተመጣጠኑና የተማሪዎቹ የማዳመጥ ክሂል ለማዳበር በከፊል መልካም መሆናቸው ነው ከመምህራኑ የተገኘው መረጃ ያሳያል በሌላ አገላለፅ ከዚህ የበለጠ ለተማሪዎች የማዳመጥ ክሂል ለማዳበር በተሻለ መንገድ በድምፅ ቀርጾ ወደ ክፍል ይዞ በመግባት ከዚያም ከቀረቡት ለእሳዊ መግለጫ ተደግፈው ቢቀርቡ የተሻለ እንደሆነ ከጥናቱ መረዳት ይቻላል።

ምዕራፍ አምስት

ማጠቃለያ፣መደምደሚያ፣ አስተያየት

## 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በ10ኛ ክፍል ኣማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍና መርሃ ትምህርት ውስጥ የተካተቱ የማዳመጥ ክሂል ተግባራት ክንውኖች ለተማሪው ክሂል ለማዳበር ያላቸውን ተገቢነት መፈተሻ ሲሆን፣ከዚህ በታች ደግሞ ንዑሳን ዓላማዎችን ተዘርዝሯል፡-

- በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የቀረቡት የማዳመጥ ክሂል ተግባራት ክንውኖች ለተማሪው ክሂሉን ከመገንባት ኣኳያ ያላቸውን ተገቢነት ምን እንደሚመስል መዘርዘር።
- በመፅሓፉ ውስጥ የቀረቡት የማዳመጥ ክሂል ተግባራት ክንውኖች ለተማሪው የማዳመጥ ክሂሉን ለማዳበር እንዴት እንደሚያዙ ከመምህራን በቡዱን ውይይት አማካኝነት መዘርዘር፡፡
- በመማሪያ መፅሓፉ እና በመርሃ ትምህርቱ የቀረቡት የማዳመጥ ክሂል ተግባራት ክንውኖች በክፍል ውስጥ ሲተገበሩ ሦስቱ ደረጃዎችን ወይም መመሪያዎችን ጠብቀው ከመቅረብ ኣኳያ ምን እንደሚመስሉ በመምህራን ፅሑፍ መጠይቅ አማካኝነት መግለፅ፡፡

ከላይ የቀረቡትን ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት የምርምርን አካሄድ በመከተል የጥናቱ ተሳታፊዎች ተመርጠዋል፤የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች ተዘጋጅተዋል፤ተሰብስበዋል፤የመተንተኛ ዘዴዎች ተመርጠው መረጃዎቹ ተተንትነው ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

በትምህርት ሚኒስቴር በ2015 ዓ.ም የታተመው የ10ኛ ክፍል የመማሪያ መፅሐፍ ላይ አጥኚዋ በምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳናት ላይ እንደ ዋቢ ከተጠቀመችባቸው በማዳመፅጥ ክሂል ተግባራትና ክንውኖች ዙሪያ የተለያዩ የምርምር ስራዎች ከሰሩ ሙሁራን ሃሳብ ጨምቃ በማውጣት የሚከተሉትን የመገምገሚያ ማእቀፎች (Frameworks) አውጥታ በመፅሐፉ ላይ የሰነድ ፍተሻ (document analysis) አካሂዳለች፡፡ የመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ አስር ምእራፎች ያሉ ሲሆን እያንዳንዱን ማእራፍ የመጀመሪያው ወይም ክፍለ ትምህርት አንድ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት ነው። አጥኚዋ ከጊዜ እጥረት አንፃር ሁሉንም አስር ምእራፎች ማዳረስ ስለማትችል ከምእራፍ አንድ በመጀመር አንድ አንድ ምእራፍ በመዝለል ማለትም በጎዶሎ ቁጥሮች የተሰየሙት አምስት ምእራፎች (1፣3፣5፣7፣9) እንደ ናሙና በመውሰድ በመማሪያ መፅሐፉ ላይ የሚከተለውን አጠር ያለ የሰነድ ፍተሻ (document analysis) ለማካሄድ ሞክራለች።

በዚህ መሠረት እንደ ናሙና በመረጠቻቸውምዕራፎች ብንወስድ ተማሪዎቹ በግልና በቡዱን በመሆንየመወያየት፣ የመተርጎም፣የመተንተን፣የመግለፅዕድልየሚኖራቸው ሲሆን የተነበበውን ፅሑፈ ቁልፍ ቃላትና ፍችዎቻቸውን፣የስዋስው ሥርዓት፣ የፅሑፍ አወቃቀር የማወቅ፣ የፅሑፍ ክሂል መለማመድ ዕድል ይኖራቸዋል በማለት አጥኚዋ ባካሄደችው የሰነድ ፍተሻ (document analysis) አረጋግጣለች፡፡ አጥኚዋ በምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳናት ላይ እንደ ዋቢ ከተጠቀመችባቸው ሙሁራን ሃሳብ ጠቅለል አድርገን ስናይ የማዳመጥ ክሂል ደግሞ ለሌሎች ክሂሎችም ምሶሶ እንደመሆኑ መጠን ተማሪዎች የሚቀርብላቸው የሚደመጡ ተግባራት በኣግባብ ከጨበጡ ያዳመጥቱን የመተርጎም፣የመተንተንና የመግለፅ ዕድል ይኖራቸዋል።

ስለዚህ በመማሪያ መፅሐፉና መርሃ ትምርህት የተካተቱት የማዳመጥ ክሂል ርእሰ ጉዳዮችና ይዘቶች የተማሪዎችን ፍላጎት ያማከለ፣ የክፍል ደረጃ (ደረጃ መጣኝነት)፣ ዕድሜ፣ ባህላዊ ዳራ የሚመጥኑነ ብሎም አዳዲስና አዳምጥዋቸውመ የማያውቁ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ስለሆነም ከዚህ አንፃር በመፅሐፍ ውስጥ የተካተቱ የማዳመጥ ክሂል ተግባራትና ክንውኖች ከያዙት ቁም ነገር አዘል ርእሰ ጉዳዮችና ይዘቶች አኳያ ሲታይ ለተማሪው ክሂል ለማዳበር ያላቸውን ተገቢነት መልካም መሆኑ ጥናቱ ያመለክታል ፡፡

የተጠቀሰዉ የ10ኛ ክፍል የመማሪያ መፅሐፍ በተለያዩ ጊዚያት በመፅሓፉ አጠቃላይ አዘገጃጀትና አቀራረብ በተመለከተ በመምህራን የተገመገመ ቢሆንም አጥኚዋ ለዚህ ጥናት ዓላማ ሲባል የሞያ አጋርዎችዋ ከተለያዩ ትምህርት ቤቶች በመሰብሰብ በመፅሐፉ ውስጥ የተካተቱት የማዳመጥ ትምህርት ክፍል ርእሰ ጉዳዮችና ይዘቶች ደካማና ጠንካራ ጎኖች እንደሚከተለው በአጭሩ ቀርቧል፡፡

ከተጠቀሱት ጠንካራ ጎኖች፡- በአብዛኞቹ ምዕራፎች ለክፍሉ ደረጃው የሚመጥኑ የማዳመጥ ትምህርት ክፍል ይዘቶች መቅረባቸው፤ በአስሩ ምዕራፎች የተለያዩ የማዳመጥ ዓበይት ክሂልና ንኡስን ክሂልን የተማሪዎችን አጠቃላይ የቋንቋ ክሂል እንዲያዳብሩ በሚረዱ መልክ የቀረቡ መሆናቸው፤ የማዳመጥ ትምህርት ክፍል ይዘቶች የመፃፍ፣የንግግር ክሂሎችን፣ የስዋስው ክሂሎችን እንዲያዳብሩ መሰረት ተደርገው የቀረቡ መሆናቸውን፤ በአባዛኞቹ ምዕራፎች ውስጥ ላይ ያሉት የማዳመጥ ትምህርት ክፍል ይዘቶች ግልፅ፣ አጭር ኣሳታፊ የሆነ የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን ይዘዋል፤ ከምዕራፍ አንድ እስከ አስር ያሉት የክፍሉ ደረጃ የሚመጥን ባህልን መሰረት ያደረጉ አስደሳች የማዳመጥ ትምህርት ክፍል ይዘቶች ናቸው፤ በእያንዳንዱ ምዕራፎች የቀረቡትን መልመጃዎች ገንቢና ተያያዥነት ያላቸው ናቸው፤ አብዛኛውቹ መልመጃዎች በመምህር መምርያ መልስ መስጠታቸውን ሁሉም አስተማሪ እኩል የሆነ ምላሽ እንዲሰጥ ያደርጋል። በዚያው ልክም ተማሪዎችን

ተመጣጣኝ ኣቅም እንዲያዳብሩ የሚያግዝ መሆኑን በጠንካራ ጎን የሚታይ ነው፤ በማዳመጥ ትምህርት ክፍል ይዘቶችን የቀረቡት የተለያዩ ተግባራት አንድነት (Intergrity) እና ተከታታይነት (Continuty) ያላቸው ናቸው።

ከተጠቀሱት ደካማ ጎኖች ደግሞ አብዛኞቹ ይዘቶች የእውቀት ክህሎት ላይ የተመሰረቱ በመሆናቸው እንደ ድክመት የተገመገመ ነው። ከዛም በተጨማሪ በሁሉም ምዕራፎች እንደድክመት የታየው ወይም የተገመገመው በመምህሩ መመርያ ያለው የክፍለ ጊዜ በብዛትና በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ገብተህ የሚሰጠው ክፍለ ጊዜ በፍፁም የማይጣጣሙ ባለመሆናቸው ለቀጣይ ለዚህ መፍትሔ እንዳገኝ በአፅንኦት ሐሳባቸውን ገልፀዋል። ከዚያም ክሂሎች እንደሌላው ይዘቶች ለብቻቸው በቂ ክፍለ ጊዜ ተመድቦላቸው መስጠት እንደሚገባ መምህራኑን የራሳቸው አስተያየት አስቀምጠዋል።

በማይጨው ከተማ ካሉት ሦስት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል የ10ኛ ክፍል አማርኛ መምህራን የሆኑት ሦስት ወንዶችና ሦስት ሴቶች በጠቅላላ 6 መምህራን እንደናሙና በመውሰድ ፅሑፋዊ መጠይቁ በማሰራጨት የተገኘው መረጃም በቅድመ ተከተል ተተንትነው ቀርበዋል።

አጥኚዋ መምህራኑ ለእያንዳንዱን የማዳመጥ ደረጃ ሥር ሳሉት ዓ.ነገሮች ከአምስቱም አማራጮች (5 በጣም እስማማሉህ፣ 4 እስማማሉህ ፣3 አልፎ አልፎ እስማማሉህ ፣2 አልስማማም፣1 በጣም አልስማማም) መካከል አንድን ብቻ በመምረጥ ከምረጫው ፈትለፈት ከሚገኘው ሳጥን ውስጥ የ« » ምልክት በማድረግ እዲመልሱ ነበር ያዳረገችው። በምዕራፍ 4 ስንጠረዥ አራት ቁጥራዊ መረጃ መረዳት እንዲሚቻለው የመምህራኑ ምላሽ በሂሳባዊ (ስታስቲካዊ) ቋንቋ ሲገለፅ አብዛኛው መምህር 3ኛው አማራጭ (አልፎ አልፎእስማማሉህ ) የሚል ምላሽ ነበር የሰጠው።

–ስለሆነም ለ3ኛው አማራጭ (3 አልፎ አልፎ እስማማሉህ) ብለው የመለሱ መምህራን በሦስቱም በቅድመ ማዳመጥ፣ በማዳመጥ ጊዜና በድህረ ማዳመጥ ደረጃዎች በተከታታይ 61፣ 60፣ 61.4 የሆኑት ከፍተኛ አማካይ ውጤት ጥቅል (60.8) ተመዝግቧል። ይህ ማለት ከጠቅላላ 6 መምህራን አብዛኞቹ ማለትም 60.8 በመቶ በአማርኛ መማሪያ መፅሓፉ ውስጥ የተጠቃለሉት የማዳመጥ ክሂል ተግባራት ክንውኖች የተማሪዎቹን ክሂል ለማዳበር ያላቸው ተገቢነት በተመለከተ መካከለኛ እንደሆኑ ክጥናቱ መገንዘብ ይቻላል። በአጠቃላይ ስታይ ይህ ቁጥራዊ መረጃ የሚያመለክተው በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሓፍ ውስጥ ያሉት የማዳመጥ ክሂል ለማዳበር ያላቸው ተገቢነት ለክፉ የሚያደርግ ባይሆንም ለወደፊቱ መሻሻል ያለባቸው ነገሮች ግን በማዳመጥ ክሂል የሚቀርቡት ተግባራት በንባብ መልክ ከመቅረቡ ይልቅ በድምፅና በስዕል ተደግፈው መገመት ይቻላል። ተደግፈው ባለመቅረባቸው ምክንያት የተማሪዎቹን የማዳመጥ ክሂል እንዳይጎለብት አሉታዊ ተፅኖ ማሳደሩን ከጥናቱ መረዳት ተችሏል። በተጨማሪ መምህራን በመማሪያ መፅሓፉ የቀረቡት የሚደመጡ ተግባራት ትኩረት ስጥተው ባለማስተራቸው የተነሳ ተማሪዎቹ የማዳመጥ ክሂላቸውን ማዳበር እንዳልቻሉ ጥናቱ ያመለክታል።

አጥኚዋ ተማሪዎቹ ለእያንዳዱን የማዳመጥ ደረጃ ሥር ሳሉት ዓረፍተ ነገሮች ከአምስቱም አማራጮች (5-በጣም እስማማለሁ፣ 4-እስማማለሁ፣ 3-እርግጠኛ አይደለሁም፣2-አልስማማም፣ 1-በጣም አልስማማም) መካከል አንዱን ብቻ

በመምረጥ ከምርጫው ፊት ለፊት ከሚገኘው ሳጥን ውስጥ የ€€√« ምልክት በማድረግ እዲመለሱ ነበር ያደረገችው፡፡ በምእራፍ 4 ከከሰንጠረዥ አራት ቁጥራዊ መረጃ መረዳት እንደሚቻለው የተማሪዎቹ ምላሾች በሂሳባዊ (ስታስቲካላዊ) ቋንቋ ሲገለፅ አብዛኛው ተማሪ 3ኛው አማራጭ (እርግጠኛ አይደለሁም) የሚል ምላሽ ነበር የሰጠው፡፡

ስለሆነም ለ3ኛው አማራጭ (3- እርግጠኛ አይደለሁም) ብለው የመለሱ ተማሪዎች አማካይ ብዛት ስናይ በሦስቱም በቅድመ ማዳመጥ፣በማዳመጥ ግዜ፣ በድህረ ማዳመጥ ደረጃዎች በተከታታይ 85.5፣90፣90.6 የሆኑት ከፍተኛ አማካይ ውጤቶች (ጥቅል አማካይ 88.8) ተመዝግበዋል፡፡ይህ ማለት ከጠቅላላ 125 ተማሪዎች አብዛኛዎቹ ማለትም 71.04 በመቶ በአማርኛ መመሪያ መፅሃፉ ውስጥ የተጠቃለሉት የማዳመጥ ክሂል ተግባራትና ክንውኖች የተማሪዎችን ክሂል ለማዳበር ያላቸዉ ተገቢነት በተመለከተ የሚያውቁተ ነገር የለም ወይም ተግባራቱ ሲከወኑ አይተው አያውቁም ወይም በጊዜ እጥረት የተነሳ መምህራኖቹ አያሰራቸውም፡፡ በአጠቃላይ ስታይ ይህ ቁጥራዊ መረጃ የሚያመለክተው በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ያሉት የማዳመጥ ክሂል ተግባራትና ክንውኖች የተማሪዎችን ክህል ለማዳበር ያላቸው ተገቢነት በጣም ደካማ ከመሆኑ የተነሳ ተማሪዎችና መምህራኑ የክሂሉን መልመጃዎችና ተያያዥ ሂደቶች በሚገባ እንደማይተገብሯቸው ከቁጥራዊው መረጃ መረዳት ተችለዋል፡፡

## 5.2 መደምደሚያ

የጥናቱንውጤትትንተናናማብራሪያመሰረትበማድረግከሚከተሉትመደምደሚያዎችላይተደርሷል፡-

1. በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የቀረቡት በሦስቱም በቅድመ ማዳመጥ፣በማዳመጥ ግዜ፣በድህረ ማዳመጥ ደረጃዎች ያሉት ተግባራትና ክንውኖች በትክክል ከተተገበሩ ለተማሪዎችን የተሻለና ለአዳምጦ መረዳታቸው ደጋፊ ሲሆን የሚችል ነው፡፡በመሆኑም ተማሪዎች የማዳመጥ አቅማቸውን የማሳደግ ከፍተኛ እንደሚሆን በማሰብ መምህራን ተማሪዎች ያሉት የማዳመጥ ተግባራትና ክንውኖች እንዲጠቀሙ ማድረግ እንዳለባቸው ፍንጭ የሚሰጥ ነው፡፡
2. በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የቀረቡት በሦስቱም በቅድመ ማዳመጥ፣በማዳመጥ ግዜ፣በድህረማዳመጥ ደረጃዎች ተግባራትና ክንውኖች በትክክል ከተተገበሩ በተለይ ደግሞ መተንበይ፣ ለአዳዲስ ቃላት ትርጉም መስጠትና ማወዳደርን ተማሪዎች ከአእምሯዊ ብልሃት ንዑሳን ብልሃቶች ይጠቀማሉ፡፡ በመሆኑም መምህራን እነዚህን ንዑሳን የብልሃት አይነቶች ተጠቅመው ማስተማራቸው ለተማሪዎች አዳምጦ የመረዳት አቅማቸው የተሻለ እንዲሆን የማዳረግ አንድምታ ይኖረዋል፡፡

## 5.3 አስተያየት

ተማሪዎችን የማዳመጥ ክሂላቸው ለማሳደግ እና የአዳምጦ መረዳት ችሎታቸውን ለማጎልበት ከጥናቱ ውጤት በመነሳት የሚከተሉት አስተያየቶች ተጠቁመዋል፡-

ተማሪዎች በማዳመጥ ትምህርት ወቅት ከዚህ ቀደም ይጠቀሟቸው የነበሩ ዘዴዎችን በመለየት፣ በመገምገምና የማዳመጥ ክሂላቸው አጠቃቀማቸውን ቢያሳድጉ፤

የአማርኛ ቋንቋ መምህራንየሚያስተምሩትን የማዳመጥ ትምህርት ሲያቅዱ፣ ሲተገብሩምሆነ ሲገመግሙ የተማሪዎችን የማዳመጥ ተግባራትና ክንውኖች አጠቃቀም ከግምት ውስጥ ያስገባ ቢሆንናየሚሰጧቸው ተግባራትና መልመጃዎች የማዳመጥ ክሂላቸውለማዳበር የሚያስችሉ እንዲሆኑቢደረግ፤

በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የቀረቡት በሦስቱም በቅድመ ማዳመጥ፣በማዳመጥ ግዜ፣በድህረ ማዳመጥ ደረጃዎች ያሉት ተግባራትና ክንውናች በተማሪዎችና መምህራን በኩል ዝቅተኛና ደካማ አጠቃቀም እንዳለ ጥናቱ አሳይቷል፡፡ በመሆኑም የስርዓተ ትምህርት አዘጋጆች የቋንቋ መማሪያና ማስተማሪያ መሳሪያዎች ሲያዘጋጁ የተማሪዎችን አዳምጦ መረዳት ችሎታ ሲያዳብሩ የሚችሉ የማዳመጥ ክሂል ስልጠናዎችን እንደ አንድ ይዘት አካተው ቢያቀርቡ፡፡

ዋቢጽሁሮች

ማረው ዓለሙ ። (1998)። *የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ፡*አዲስ ኣበባ ብርሀንና ሰላም ማታሚያ ድርጅት።

በድሉ (1996) ። *በስነ-ፅሑፍ ቋንቋ ማስተማር፡፡*አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

አልማዝ (2006) *በዘጠነኛ ክፍል ኣማርኛ መማሪያ መፅሓፍ የውስዋ የቀረቡ የማዳመጥ ትምህርት ይዘቶችና ክንውኖች የክፍል ውስጥ ኣተገባበር ግምገም፡፡*

እቴነሽ ተገኝ። (1986)። *በ9ኛ ክፍል የኣማርኛ መርሃ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥ ክሂል ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶች ትንተናና ግምገማ፡፡* በኣዲስ ኣበባ ድህረ ምረቃ ትምህርት መርሃ ግብር። በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሑፍ ትምህርት ክፍል። ኣማርኛ ቋንቋን በማስተማር።

ቃኘው መኮነን (2012 ዓ.ም) *የ7ኛ የ8ኛ ክፍል ኣማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የማዳመጥ ትምህርት ይዘት ኣደረጃጀትና ኣቀራረብ ግምገማ፡፡* በኣዲስ ኣበባ መስተዳድር ትምህርት ቢሮ በ2007 ዓ.ም በታተመው የተካሄደው ጥናት።

ጎዱ ምንውዬ (2014 ዓ.ም) *በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪዎች የማዳመጥ ብልሀት አጠቃቀም ከአዳምጦ የመረዳት ችሎታቸው ጋር ያለው ተዛምዶ፤ በሰዴ ሙጃ ወረዳ በሙጃ ሮቢት አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ10ኛ ክፍል ተተኳሪነት፡፡* ጅማ ዩኒቨርሲቲ ማህበራዊ ሳይንስና ሰብአዊነት ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋ (ዎች) እና ስነ-ፅሁፍ አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ድህረምረቃ መርሀ ግብር።

ታደሰ ሲባሞ (2004 ዓ.ም).*አማርኛን የማስተማር ሰነ-ዘዴ.* አዲስ አበባ. ትምህርት ሚኒሰቴር፡፡

ትምህርት ሚኒስቴር፡፡ (2015 ዓ.ም)፡፡ *አማርኛ የመምህሩ መምሪያ አስርኛ ክፍል፡፡* ዱባይ፣ አል-ጎሬርአታሚ ድርጅት።

የትምህርት ፖሊስ ትንተና እና ስልታዊ ጥናት፣V16፣N4፣2021 © 2021 INASED 49፡፡

→ አየለች ጨቃሳ –( 2016) አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡ የማዳመጥ ክሂል ትምህርት ክንውኖች በክፍል ውስጥ አተገባበር ግምገማ ፣ በአርሲ ዶዶታ ወረዳ አርጊቲ ደነባ አንደኛ ደረጃ 2ኛ እርከን ትምህርት ቤት አዲስ አበባ ዩኒቨረስቲ የሂይማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት ፣የጆርናሊዝምና ኮምኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ፅሑፍና ፎክሰር ትምህርት ክፍል የሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ የቀረበ፣

→ ታዲዮስ ቦብሮ በ10ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መፅሐፍ ውስጥ የማዳመጥ ክሂልን የማስተማሪያ የትምህርት ይዘት አመራረጥና አቀራረብ መገምገም ፣ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት፣

Abdahamid, F. (2012).*Listing comprehension Strategies of Arabic- Speaking ESL*

*Learners.*Master's Dissertation, Department of English, Colorado.State university, Fort Collins, Colorado.

Anderson and Lynch.J (1983).*Listening.* Oxford: Oxford University Press

Brown, *H. D. (2001). Teaching by principles: An interactive approach to language pedagogy (2nd Ed.).* White plains, NY: Long man

Chamot, A. U. (2004). Issues in language learning strategy research and teaching.*Electronic Journal of foreign language teaching,* 1(1), 14-26.

Chamot, A. U. (2005). *Language learning strategy instruction: current issues and research.*Annual Review of Applied linguistics, 25, 112- 130.

Cunning Worth, A (1995). *Choosing Your Course Book*. Heine Mann.

Darweesh, A. D. (2014). The importance of teaching listening comprehension at the University level.*Acme intellects international Journal of Research in Management, Social sciences & Technology,* 8(8), 20- 27.

Grant, N. (1989). *Making The Most of Your Textbook*. London: Longman.

Gilakjani, A. P., & Ahamadi, M, R. (2011*). A study of factors affecting EFL learners' English listening comprehension and the strategies for improvement.Journal of language teaching and Research 215/1798- 4769*.

Gilakjani, A. P., & Sabouri, N. N. (2016).*Learners' listening comprehension difficulties in English language learning: A literature review.* English Language Teaching, 9(6), 123-133.

Lestari, D. (2017). *The Correlation between Self-efficacy Concerning Listening Skill and Listening Comprehension of the Eleventh grade students of SMA Negeril.* Pemulutanselata, Ranen Fatah Palembang, NIM. 12250029

Hamouda, A. (2013). An investigation of listening comprehension problems Encountered by Saudi students in the EL listening classroom.*InternationalJournal of academic research in progressive education and development, 2(2), 113- 115*

Islam, M, N. (2012). An analysis on how to improve tertiary EFL students' listening skill of English.*Journal of studies in education,* 2 (2), 21- 52

Nunan, D. (1998). *Approaches to Teaching Listening in the Language Classroom.*Paper presented at the Korea TESOL Conference, Seoul.

Nunan, D. (2002). *Listening in language learning.*In J. C. Richards, & W. A. language teaching (pp. 238- 41). Cambridge: Cambridge university press.

RenukadeviD. (2014).the role of listening in language acquistition; the challenges &strategies in teaching listening. *International Journal of Education and Information studies.*4 (1).59-63.

Richards, J. C., (2008). *Teaching listening and Speaking from theory to practice.* New York: Cambridge university press.

Rost, M. (2009).*Teacher development Interactive: Listening.*White Planings.NY; Pearson Longman.

Underwood, M.(1989).*Teaching Listening.* New York: Longman.

Wilson, J.J. (2008). *How to Teach Listening.* Harlow: Pearson Education Limited.

አባሪዎች

**ኣባሪ ሀ፥ ለሰነድ ፍተሻ ጥቅም ላይ የዋሉ ማዕቀፎች**

**መቐለ ዩኒቨርሲቲ**

**የሕብረተሰብ ሳይንስና ቋንቋዎች ኮሌጅ**

**የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነ-ፅሑፍ ትምህርት ክፍል (አማርኛ)**

**የድህረ ምረቃ መርሐ-ግብር**

1. በቅድመ ማዳመጥ፣በማዳመጥ ጊዜ፣በድህረማዳመጥ ደረጃዎች የተጠቃለሉት መመሪያዎችና ይዘቶች ተማሪዎች የሚቀርብላቸውን የሚደመጥ ተግባራትና ክንውኖች ያዳመጡትን የመተርጎም፣የመተንተን፣ የመግለፅና የመወያየት ዕድል ከመስጠት አንፃር ሲታይ (ለተማሪዎች ክሂል ለማዳበር ያላቸዉ ተገቢነት ተተኳሪነት አንፃር)፡፡
2. የትምህርት ይዘቶች አመራረጥ የተማሪዎችን ዓውድና ለተማሪዎች ካለው መስህብነት አንፃር ሲታይ፡፡
3. የማደመጥ የትምህርት ርእሰ-ጉዳዮችና ይዘቶች አመራረጥ የተማሪዎችን ፍሎጎት እና አቅም ከማገናዘብ አንፃርሲ ታይ፡፡
4. የትምህርት ይዘቶች አመራረጥ የተማሪዎችን የክፍል ደረጃ (ደረጃ መጣኝነት)፣ዕድሜ፣ባህላዊ ዳራ አንፃርሲ ታይ፡፡
5. የትምህርት ይዘቶች አመራረጥ ተማሪዎች አዳዲስና አዳምጠውት የማያውቁት ከመሆናቸው አንጠፃርሲ ታይ፡፡

**ኣባሪ ስ÷ የማዳመጥ ክሂል ተግባራትና ክንውኖች መስኪያ የጽሑፍ መጠይቅ**

**መቐለ ዩኒቨርሲቲ**

**የሕብረተሰብ ሳይንስና ቋንቋዎች ኮሌጅ**

**የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነ-ፅሑፍ ትምህርት ክፍል (አማርኛ)**

**የድህረ ምረቃ መርሐ-ግብር**

**በ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሞላ የጽሑፍ መጠይቅ**

ውድ ተማሪዎች፡- የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ *€€የማዳመጥ ክሂል ተግባራትና ክንዉኖች ለተማሪዉ ክሂል ለማዳበር ያላቸዉ ተገቢነት ፍተሻ ፣ (በ10ኛ ክፍል መማሪያ መፅሐፍ ተተኳሪነት)«* በሚል ጥናት በሚካሄደው መረጃ ለማግኘት ነው፡፡ በዚህ መጠይቅ አማካኝነት የተሰበሰበው መረጃ ለሌላ ዓላማ አይውልም፡፡ በመሆኑም መጠይቁን በምትሞሉበት ጊዜ ማንንም ሰው ሳታማክሩ በመመለስና ለምትሰጡት መልስ ታማኝ በመሆን ለጥናቱ ውጤት አስተማማኝነት የበኩላችሁን እንድታበረክቱ በአክብሮት እጠይቃለሁ፡፡

**ማሳሰቢያ፡-**

1. ስማችሁን መጻፍ አያስፈልግም፡፡

2. መጠይቁን በግላችሁ ልትሞሉ ይገባል፡፡

3. ለሁሉም ጥያቄዎች መልስ መስጠት ይጠበቅባችኋል፡፡

**ክፍል አንድ፡- የግል ሁኔታ**

1. ፆታ............ 2. ዕድሜ................

**ክፍል ሁለት፡- የጽሑፍ መጠይቁ መመሪያ**

ከዚህ በታች የማዳመጥ ክሂል ተግባራት ክንውኖች መስኪያ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ እያንዳንዱን ዓረፍተ ነገር በጥሞና አንብበሽ (ህ) ከተጠቀሱት አምስት አማራጮች መካከል አንዱን ብቻ በመምረጥ ከምርጫው ፊት ለፊት ከሚገኘው ሳጥን ውስጥ የ€€√« ምልክት በማድረግ መልሽ (ስ)፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክል ወይም ስህተት የሚል መልስ የለውም፡፡

**አማራጮቹና የሚወክልዋቸው ቁጥሮች፡-**

5.በጣም እስማማለሁ

4.እስማማለሁ

3.አልፎ አልፎ እስማማሉህ

2.አልስማማም

1.በጣም አልስማማም

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በመፅሐፉ የተካተቱት የቅድመ ማዳመጥ ተግባራትና ክንውኖች ተማሪዎቹን ንቁ አድማጭ እንድሆኑ ስሜታቸውን በሚያነሳሳ መልኩ ቀርቧል፡፡ | | | | | |
| 2 | የቅድመ ማዳመጥ ተግባራቱ ቀጥሎ ምን እንደሚደምጥና ስምን እንደሚደምጥ በሚጠቁም መልኩ ነው የቀረቡት፡፡ | | | | | |
| 3 | የቅድመ ማዳመጥ ተግባራቱ ለተማሪዎቹ ቀጥሎ ለሚደመጠው ንባብ ወይም ንግግር መገመት በሚያስችላቸው መንገድ ነው የቀረቡት፡፡ | | | | | |
| 4 | የቅድመ ማዳመጥ ተግባራቱ የሚደመጠው የንባብ ወይም የንግግር ርእስ ጉዳይ የተማሪዎቹን ዳራዊ ዕውቀት በሚቀሰቅስ ነው የቀረቡት፡፡ | | | | | |
| 5 | የቅድመ ማዳመጥ ተግባራቱ ቀጥሉ በሚደመጠው ርእስ ጉዳይ ውስጥ የተካተቱት ቁልፍ ቃላትን ያስተዋውቃሉ፡፡ | | | | | |
| 6 | የቅድመ ማዳመጥ ተግባራቱ የአድማጩን እይታ በመሳብ በስዋስውና ቃላት ያተኩራል፡፡ | | | | | |
| 7 | የቅድመ ማዳመጥ ተግባራቱ የአድማጩን የማዳመጥ ክሂል በሚያዳብር መልኩ ነው የተደራጀው። | | | | | |
| 8 | የቅድመ ማዳመጥ ተግባራቱ ቀጥሎ የሚደመጠውን ንባብ የፅሑፍ ዓይነት በሚጠይቅ መልኩ ነው የተደራጀው፡፡ | | | | | |
| 9 | የቅድመ ማዳመጥ ተግባራቱ በትምህት ይዘቱ ውስጥ ያሉት የአዳዲስ ቃላት ፍችዎችን በሚያሳውቅ መልኩ ነው ፡፡ | | | | | |
| 10 | በመጨረሻም ቀጥሎ የሚነበብላቸው የትምህርት ይዘቶች በሚያዳምጧቸው በአፍመፍቻ ቋንቋቸው እንዲያብራሩ ያዝዛል። ያብ | | | | | |
| 11 | በማድመጥ ጊዜ የቀረቡት የሚደመጡ ተግባራትና ክንውኖች ከቅድመ ማዳመጥ ጋር ተያያዥነት አላቸው ። | | | | | |
| 12 | በመፅሐፉ የተካተቱት የማዳመጥ ጊዜ ተግባራትና ክንውኖች ስመምህሩ/መምህርትዋ የማጣቀሻ ጥያቄዎች እንድትጠይቅ ወይም እንዲጠይቅ ያስችለዋል/ያስችላታል። | | | | | |
| 13 | በማድመጥ ጊዜ ለሚቀርቡ ተግባራት ክንውኖች የሚጠናክሩ ስዕላዊ መግለጫዎች | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ይቀርባሉ። | | | | | |
| 14 | በማድመጥ ጊዜ የሚቀርቡ ተግባራት ተማሪዎችን በሚገባ ያሳማምዳሉ። | | | | | |
| 15 | በማዳመጥ ጊዜ የሚቀርቡ ተግባራት ክንውኖች የተማሪዎችን ሞራል ያነሳሳሉ ። | | | | | |
| 16 | በማድመጥ ጊዜ የሚቀርቡ መስማጃ ጥያቄዎችን ተማሪዎች አያያዥ ቃላትን ተጠቃመው እንዲሰሩ ያግዛሉ። | | | | | |
| 17 | በማድመጥ ጊዜ የሚቀርቡ የመስማመጃ ተግባራት ክንውኖች የተማሪዎችን ቀልብ በመያዝ የማዳመጥ ክሂልን ለማጎልበት ይችላሉ። | | | | | |
| 18 | የማድመጥ ንባቡን ወይም ንግግሩን በተገቢ መንገድ ካዳመጥኩ በኋላ የመልመጃዎቹ ጥያቄዎች ከቀላል ወደ ከባድ ነው የቀረቡት። | | | | | |
| 19 | በማድመጥ ጊዜ የማድመጥ ንባቡን ወይም ንግግሩን በተገቢ መንገድ ካዳመጥኩ በኋላ የቋንቋውን ስዋስዋዊ ስርዓት ላይ ትኩረት እንዳደርግ ያስችላል። | | | | | |
| 20 | በመፅሐፉ የተካተቱት የማዳመጥ ጊዜ ተግባራትና ክንውኖች የማድመጥ ንባቡን ወይም ንግግርን ጭብጥ በተገቢ መንገድ እንድረዱ ያስችላል። | | | | | |
| 21 | በድህረ ማድመጥ ደረጃ ያሉ ጥያቄዎች ያደመጡትን ንባብ ወይም ንግግር በትክክል መገንዘባቸው እንዲገመግሙ የሚያስችሉ ናቸው። | | | | | |
| 22 | በድህረ ማድመጥ ደረጃ ያሉ ተግባራትና ክንውኖች በቅድመ ማዳመጥ ወቅት ያደረጓቸው ግምቶች ያረጋግጥላቸዋል። | | | | | |
| 23 | በድህረ ማድመጥ ደረጃ ያሉ ተግባራትና ክንውኖች ኣድምጦ የመረዳት ክሂል ከፍ በሚያደርግ መልኩ ነው የተቀናጁት። | | | | | |
| 24 | በድህረ ማድመጥ ደረጃ ያሉ ጥያቄዎች ያዳመጡትን ንባብ ወይም ንግግር ርእሰ ጉዳይ ከእለታዊ ህይወታቸውን ጋር እንዲዛመድ ያደርጋቸዋል። | | | | | |
| 25 | በድህረ ማድመጥ ደረጃ ያሉ ተግባራትና ክንውኖች የትምህርት ይዘቱን ዓላማዎች መምታታቸውና ኣለመምታታቸው ያረጋግጥላቸዋል። | | | | | |

**ለትብብራችሁ በጣም ኣመሰግናለሁ!**